# ዐምዕራፍ አንድ

## የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ

*ውድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ ሃይማኖት የሚለውን የቃሉን ትርጉም እና ሃይማኖት ለሥጋና ለነፍስ የሚሰጠውን ጥቅም እንመለከታለን፡፡*

### ፩.፩ የሃይማኖት ትርጉም

***ውድ ተማሪዎች ሃይማኖት ማለት ምን ማለት ይመስላችዋል?***

ሃይማኖት በአንድ ቃል ወይም ብያኔ እንዲህ ነው ብሎማስቀመጥ አይቻልም፡፡ ይኸውም ሊቃውንት በየተረዱበት መንገድ በልዩ ልዩ አገላለጽ አስቀምጠውታልና ነው፡፡

የሃይማኖትን ትርጉም በመጠኑ ለመቃኘት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው መዝገበ ቃላታዊ ፍቺ ሲሆን ሁለተኛውም ምስጢራዊ ፍቺ ነው፡፡

### ፩. መዝገበ ቃላታዊ ፍቺ

መዝገበ ቃላታዊ ፍቺውን ስንመለከት ለምሳሌ የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ሃይማኖትን በተለያዩ ቃላት ጠርቶታል ከነዚህም መካከል፡- ሃይማኖት ፣ ሀይመነ ፣ አሚን ፣ እምነት የሚሉት ይገኙበታል ፤ የቃላቱም ትርጉም ፡-

፩.፩. ሃይማኖት ማለት፡- ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ጽኑ ተስፋ፣ የአምልኮ በሕል፣ በልብ በረቂቅ የሚሣል ማለት ነው፣ እንዲሁም የሚያምኑት የሚያሳምኑት ነው፡፡

፩.፪ ሃይመነ ማለት ፡- አመነ ታመነ በሚል ይተረጎማል፡፡

፩.፫ አሚን ማለት፡-ማመን፣መቀበል፣ተስፋ ማድረግ፣አለመጠራጠር፣መናዘዝ እውነት መናገር፣መመስከር በማለት ገልጦታል፡፡

፩.፬ እምነት ማለት ፡- በቁሙ በመውሰድ ሃይማኖት ፣ማመን ፣መተማመን ማለት እንደሆነ ብርም ሰፍሮ ይገኛል፡፡

### ፪. ምስጢራዊ (ጽንሰ ሃሳባዊ ) (ሃማኖታዊ) ፍቺ

፪.፩ ሃይማኖት ማለት፡- በባሕርይው የማይታይና የማዳሰስ አምላክ አንድ እግዚአብሔር መኖሩን፣ እርሱም የዓለም ፈጣሪ ሠራኢ ዓለማት፣ መጋቢ ፍጡራን፣ አዳኝ መሆኑን እና በባህርየ መለኮቱ፣ በልዩ ሶስትነቱ እና አንድነቱ፣ በምልአተ አካሉ… በፍፁም እምነት በኅሊና እና በልቦና ተገንዝቦ ያለመጠራጠር እውነት ነው፣ እርግጥ ነው ብሎ መቀበል ማለት ነው፡፡ዕብ11÷1-3፣ ሮሜ 10÷10

፪.፪ ሃይማኖት ማለት፡- ከእግዚአብሔር ጋር ሚያገናኝ ረቂቅ መንገድ (ፍኖተ እግዚአብሔር) ማለት ነው፡፡ ኤር 6÷16

፪.፫ ሃይማኖት ማለት፡- ተስፋ የምናደርገውን የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው፡፡ ዕብ 11÷1

***ውድ ተማሪዎች በተጨማሪም የሚከተሉት ነጥቦች የሃይማኖትን ምንነት የሚገልጡ የሚያብራሩ ናቸው፡፡***

#### *ሀ. ሃይማኖት መሠረት ነው፡-*

«አሚንሰ መሠረት ይእቴ ወካልኣኒሃ ሕንጻ ወንድቅ እሙንቱ - እምነት መሠረት ናት ሌሎቹ ግን ሕንፃና ግንብ ናቸው» (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሕንፃና በግንብ መስሎ የተናገራቸውና ሌሎቹ ብሎ የጠቀሳቸው ምግባርንና ትሩፋትን ነው፡፡ እምነት/ሃይማኖት ግን የእነዚህ መሠረት ናት፡፡ ይህም ሕንፃን ከመገንባት በፊት ህልዎተ ፈጣሪን /የፈጣሪን መኖር/ ማመንና በሚሰሩት ምግባር ትሩፋት የሚያምኑት ፈጣሪ የማያልፍ የማይጠፋ ዋጋን እንደሚሰጥ በእምነት መቀበል ይቀድማል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ እንዳለ፡-

«ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጣቸው ሊያምን ይገባዋል፡፡»/ዕብ ፲፩÷፮/

በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፯ ÷ ፲፯ ላይ ዐለት በተባለው በቅዱስ ጴጥሮስ እምነትና ምሥክርነት ማመን (ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክ መሆኑን ማመን) የሁሉ መሠረት እንደሆነና ከዚህ በኋላ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን በፈተና ጸንቶ ለዋጋ የሚያበቃ ሥራን መሥራት እንደሚገባ እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡

*«መሠረቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ላይ በወርቅና በብር በከበረ ድንጋይ በእንጨት በሣርና በአገዳ የሚያንጽ ቢኖርም የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ እሳትም በፈተነው ጊዜ ቀኑ ይገልጠዋል፤ የእያንዳንዱም ሥራ እሳት ይፈትነዋል፡፡ ሥራው ጸንቶ የተገኘለት ሰው ዋጋውን የሚቀበል እርሱ ነው፡፡ ሥራው የተቃጠለበት ግን ዋጋውን ያጣል፡፡»/፩ኛ ቆሮ፫÷፲፩-፲፭/*

### ለ. ሃይማኖት ከዕውቀት በላይ ነው

ሰው በስሜት ሕዋሳቱ መርምሮ ያውቃል፡፡ ሻካራውን ከለስላሳው በእጁ ዳስሶ፣ ጨለማውን ከብሩሁ በዓይኑ አይቶ፣ ጣፋጩን ከመራራው በምላሱ ቀምሶ፣ መልካም መዓዛ ያለውን ከሌለው በአፍንጫው አሽትቶ ለይቶ ያውቃል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በርህቀት /ከእርሱ በመራቅ/ እና በርቀት /በረቂቅነት/ ያሉትን በስሜት ሕዋሳቱ መርምሮ በእውቀት ሊደርስባቸው አይችልም፡፡ ይህም ሰው ለእውቀቱ ድንበር ለአእምሮው ወሰን እንዳለ ያሳያል፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ወሰን የሌለው መንፈስ እንደመሆኑ ሰው በስሜት ሕዋሳቱ ሊረዳው ሊደርስበትም እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ ወሰን ያለው ሰው ወሰን የሌለውን እግዚአብሔርን የሚያውቀውና ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኘው በእምነት ከሆነ እምነት /ሃይማኖት/ ከእውቀት በላይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ጴጥሮስ ማመን ከማወቅ በፊት እንደሆነ የመሰከረው፡፡

«እኛስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ አንተ እንደሆንህ አምነናል፤ አውቀናልም» /ዮሐ. ፮፥፷፱/

### ሐ. ሃይማኖት ተስፋ የምናደርገውን የሚያስረግጥ ነው

«እምነትስ ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የምታረጋግጥ የማናየውንም ነገር የምታስረዳ ናት፡፡» /ዕብ. ፲፩፥፩/ ሰው በረቂቅነቱ ምክንያት በዓይነ ሥጋ የማያየውን የእግዚአብሔርን ህልውና የሚረዳው በእምነት ነው፡፡ እንደዚሁም ከእርሱ በመራቁ ምክንያት የማያያትን ነገር ግን ተስፋ የሚያደርጋትን መንግስተ ሰማያትን በእውነት ለባልዋ እንደ አጌጠች ሙሽራ ተዘጋጅታ እንዳለች የሚያረጋግጠው በእምነት ነው፡፡ /ራዕ. ፳፩፥፪/። ስለዚህ እምነት የማናየውን የምታስረዳ ተስፋ የምናደርገውን የምታስረግጥ ናት፡፡

## ፩.፪ የሚያምኑ  ፍጥረታትና የሃይማኖት አጀማመር

### የሚያምኑ ፍጥረታት

***ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታይ ተማሪዎች የሚያምኑ ፍጥረታት እነማን ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?***

እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት እያንዳንዱ ቢቆጠር ፍጡር ተናግሮ አይፈጽመውም፡፡ ነገር ግን ብዙውን አንድ እያሉ በየወገኑ ቢቆጥሩት 22 ፍጥረታት ይሆናል፡፡ ከእነዚህም ፍጥረታት መካከል ሁለቱ ማለትም ሰውና መላእክት የእግዚአብሔርን ስም ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ሲፈጠሩ ቀሪዎቹ ግን ለአንክሮ፣ ለተዘክሮ፣ ለምግበ ሥጋ፣ ለምግበ ነፍስ እንዲሆኑ ተፈጥረዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከ22 ፍጥረታት ሃይማኖት የሚያስፈልጋቸው ሰውና መላእክት ብቻ ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፡-

1. ሰውና መላእክት ሃይማኖት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ዕውቀት ስላላቸው
2. ሕያዋን ስለሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት እንደሌሎቹ ፍጥረታት ፈርሰው በስብሰው የማይቀሩ፣ ለዓላማ የተፈጠሩ በመሆናቸው ከፈጣሪያቸው ጋር እንዳይጣሉና ከክብሩ እንዳይለዩ ሃይማኖትን መያዝ ምግባርን ምሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

### የሃይማኖት አጀማመር

#### ❖ ሃይማኖት ከማን ለማን እንዴት ተሰጠች

ሃይማኖት ከእግዚአብሔር አክብሮ ለፈጠራቸው መላእክት እና ለሰው ባለማዳላት የተሰጠ ታላቅ ስጦታ ነው፡፡ ቅ/ ጳውሎስ ይህን ሲያመለክት በኤፌ 2፥8 "ፀጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለምና" በማለት ገልጾታል ፡፡

ከፍጥረታት ውስጥ ሃይማኖት ያላቸው መላእክት እና ሰዎች እንዲሁም አጋንንት ብቻ ናቸው፡፡ የአጋንንት እምነት ግን በስራ የማይገለጽ በመሆኑ ለድኅነት አያበቃቸውም ፡ስለ አጋንንት እምነትም ሐዋርያው ቅ/ያእቆብ በያዕ2፥19 "አጋንንት ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል" በማለት ገልጾታል፡፡

#### ፩. የሃይማኖት መሰጠት በዓለመ መላእክት

እግዚአብሔር መላእክት በእለተ እሁድ ልባውያን ነባብያን እና ኅያዋን አድርጎ ከሙሉ ነጻ ፈቃድ ጋር ከፈጠራቸው በኋላ ፈልገው ያግኙኝ በማለት ተሰወራቸው ፤ (ይኸውም ሃይማኖታቸው ይገለጥ ዘንድ ነው ፡፡) መላእክቱም የፈጠረን ማነው፣ ከየት መጣን ፣ በማለት እርስ በእርስ ተጠያየቁ፤ ይህች ሰዓት የመላእክትን አስተዋይነት እና አዋቂነት የሚፈትን እውነተኛ እምነታቸው በተግባር  የምትገለጽበት ሠዐት ነበረች፡፡

በዚህችም ሠዐት ከመቶው ነገድ የአንዱ ነገድ አለቃ የነበረው ሳጥናኤል የመላእክትን መታወክ ባየ ጊዜ የፈጠርኳችሁ እኔ ነኝ በማለት የመጀመሪያውን ክህደት ንግግርን አደረገ  በዚህም የሃሰት አባትነቱን ገለጠ፡፡ሳጥናኤል ቢያንስ ቢያንስ  ራሱን እንኳን እንዳልፈጠረ መረዳት ይችል ነበር በዚህ እንኳን ሊላ አስገኘ ፈጣሪ አምላክ እንዳለ መረዳት በቻለ ነበር እርሱ ግን ክብርን ፈልጎ ክህደትን አመነጨ፡፡

የሣጥናኤል ንግግርም በመላእክት ዘንድ የበለጠ መታወክን ፈጠረ ፤በእርሱ ነገድ ስር የነበረው ከአንዱ ነገድ ገሚሶቹ አዎ አንተ ፈጠርከን ሲሉ ገሚሶቹ ፈጥሮናል ወይስ አልፈጠረንም የሚል ጥርጥር  ውስጥ ወደቁ ገሚሶቹም አንተ ሳትሆን እኛ ፈጠርንህ አሉ፡፡ በዚህ ሰዐት የሃይማኖት አርበኛ ቅ/ገብርኤል እነርሱን የፈጠረ አምላክ እንዳለ በማመን እና በመረዳት « ንቁም በበኅላዌነ እስከንረክቦ ለአምላክነ / የፈጠረን አምላካችን እስኪገለጥልን ድረስ ፀንተን እንቁም፡፡» በማለት የሃይማኖት ቃል በመናገር የተቀሩት  ዘጠና ዘጠኙ ነገድ ባሉበት እንዲፀኑ ምክንያት ሆነ፡፡ በዚህም ጊዜ ሃይማኖት (እግዚአብሔር አለ )የሚለው እምነት ታወቀ ፤ ሃይማኖት በመላእክት ዘንድ ተገለጠች፡፡

የሚታመን ፈጣሪ እና አማንያን (የሚያምኑ) ፍጡራን ተለዩ፤ ያመኑትም መላእክት እግዚአብሔርን ሳያዩት ከምንም በላይ በባሕሪው ፍፁም ረቂቅ እና ጥልቅ የሆነ አምላክ እንደሆነ በእምነት ተቀበሉት፡፡ ይህንን እምነት እና ጽናታቸውን የተመለከተ እግዚአብሔር ራሱን ለመላእክቱ ገለጠላቸው፡፡ ያመኑት ቅዱሳን መላእክት ተባሉ ያላመኑትም ርኩሳን መላእክት ተብለው ከሃሰት አባታቸው ከሳጥናኤል ጋር ወደ እንጦሮጦስ ወርደትና ጉስቁልናል ተላብሰው ወረዱ፡፡

ሃይማኖት በእግዚአብሔር ማመን መታመን ስለሆነ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ያመኑ የታመኑ ቅዱሳን መላእክት ናቸው፡፡ ይህም ሃይማኖት የተጀመረው በዓለመ መላእክት በመጀመሪያዋ የሥነ-ፍጥረት ዕለት የመጀመሪያዎቹ አማኝ ፍጥረታት /መላእክት/ በተፈጠሩባት ጊዜ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም እንዴት እንደሆነ ሥነ-ፍጥረት በሚለው በሦስተኛው ምዕራፍ የምናየው ይሆናል፡፡

## ፪. ለሰው ልጆች የሃይማኖት መሠጠት

በሥላሴ በአርያው እና በአምሳሉ አዳምን በፈጠረው ጊዜ የህይወትን እስትንፋስንም እፍ ሲልበት በመንፈሱ አማካኝነት ሃይማኖትን ወይም እግዚአብሔርን የማመን ፀጋ አብሮ ሰጥቶታል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም እና ለሄዋን የሰጠው ሃይማኖት በመላእክት ዘንድ ያለችውን ነቅ የሌለባት አንዲቷን ሃይማኖት ናት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር እርሱን የማመን ዝንባሌ (ሃይማኖትን) በውስጣችን እንዳስቀመጠ ይህም የእርሱ ስጦታ እንደሆነ የሐ 17÷25- 27 «እርሱም (እግዚአብሔር) ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳችም እንደሚጎድለው በሰው ልጅ አይገለገልም፡፡ ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድርም ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰው ወገኖችን ሁሉ ከአንድ ፈጠረ ፡፡» በማለት ይመሰክርልናል፡፡

በጥቅሱ ውስጥ ፡- «እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ » እና « የሰው ወገኖችን ከአንድ ፈጠረ » የሚለው ሐረግ ሰው ሃይማኖታዊ ፍላጎት ያለው መሆኑን ይኸውም «ከአንድ ፈጠረ» በማለቱ ሃይማኖት ተፈጥሮአዊ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሃይማኖት መንገድነት ሰው እግዚአብሔርን ይፈልጋል እግዚአብሔርም ወደ ሰው ይቀርባል ራሱንም ይገልጥለታል፡፡ አዳም ኣባታችን ሕገ እግዚአብሔርን ጥብቆ በገነት ለሰባት አመታት በሃይማኖት ከቆየ በኋላ በዲያብሎስ አማካኝነት የቀረበለትን ፈታና በወደቀ ጊዚ እግዚአብሔርን ፈርቶ በገነት ዛፍ ሥር ከሄዋን ጋር ሲሸሸግ እግዚአብሔር አምላክ ማዕምሬ ህቡአት (የተሰወረውን የሚያውቅ ) ሁኖ ሳለ አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ በንስሃ ሊመልሰው አስቦ በሰኮና ብእሲ ዳናውን እያሰማ (የእርምጃ ድምጽ) እያሰማ በገነት እየተመላለሰ ይፈልገው ይጠራው ጀመር፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ፍለጋም « ዴሬክ የህዌ » (ፍኖተ እግዚአብሔር) ሃይማኖት በመባል ይታወቃል ፡፡ ሃይማኖት የሰው እግዚአብሔርን ፍለጋ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ፍለጋንም ያካትታል፡፡

በዓለመ መላእክት የተመሰረተች እና እግዚአብሔር በሰው ልቦናም ያሳደራት በሎም አዳም በበደለ ጊዜ በእግዚአብሔር አዳምን ፍለጋ ባደረገው ጉዞ (ዴሬክ ያህዌ) የተገለጠችው ሃይማኖት ከአዳምም በኋላ በተነሱ ደጋግ አባቶች በልቦና ታስባ በምግባር ስትገለጥ ቆይታለች፡፡ የተጻፈ ሕግ የሃማኖት መመሪያ ባልነበረበት ዘመን የሰው ልጅ በልቦናው በተጻፈ ህግ እና ዝንባሌ በመታገዝ በህሊናው ተጠቅሞ እግዚአብሔርን ያመልከው ነበር፡፡ ለዚህም ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያሉ ደጋግ አባቶች ምስክሮች ናቸው፡፡ ይህ ዘመንም ህገ ልቦና ብለን የምንጠራው ነው

<u>በዚህች ሃይማኖት፡-</u>

- ይህች ሃማኖት አዳም በንስሃ ከአምላኩ ታርቆባታል፣
- ይህች ሃማኖት አቤልን ከቃየል የጥፋት መንገድ ለይታዋለች
- ይህች ሃማኖት ኣባታችን ኖህን በአምላኩ እንዲታመን እና ከጥፋት ውሃ እንዲድን አስችላዋለች፣
- ይህች ሃማኖት አባታችን አብርሃምንም ከሀገሩ እንዲወጣ እና ወደተስፋይቱ ምድር ወደ ከነአን እንዲገባ ለበረከትም እንዲሆን አስችላዋለች፡፡...ወዘተ
- በዘመነ ብሉይም በተሰጠ ሕገ ኦሪት ሰዎች እየተመሩ በነቢያት መመህርነት እየታገዙ በአንዲቷ ሃይማኖት ፀንተው እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበረ ሲሆን ፤ በሃዲስ ኪዳንም በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና በሶስቱ አካላት መገለጥ ከበፊት ይልቅ ጎልታ ልትገለጥ ልትፀና ችላለች ፡፡ እስከ ፍጻሜ ዓለምም በሰዎች ልቡና እየታሰበች መከፈል መለወጥ ሳኖረርባት በስራ እየተገለጠች ትኖራለች፡፡ ለክብር ለመንግስተ ሰማየት እና ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት እና ለመኖር አማራጭ የሌላት አንዲት እና ብቸኛ የድኅነት መንገድ ሆና ትኖራለች፡፡

## <u>፩.፫ የሃይማኖት አስፈላጊነት (በነፍስ በስጋ)</u>

ውድ ተማሪዎች ሃይማኖት ለሥጋም ለነፍስም አያሌ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ ሁሉን ዘርዝሮ መፈጸም ባይቻልም የሚከተሉትን ዐበይት ጥቅሞች እንመለከታለን፡፡

### *ሀ. ሃይማኖት ለሥጋዊ ሕይወት የሚሰጠው ጥቅም*

### <u>፩ኛ. ሰላምን ያሰጣል</u>

ሰላም ፍጹም የሆነ ውስጣዊ ዕረፍት ነው፡፡ ሰው በሃይማኖት ከኖረ ውስጣዊ ሰላሙን የሚያደፈረሱ ፈተናዎችን፣ አእምሮ የሚያልፉ ጭንቀቶችን ሁሉ በተአምኖ እግዚአብሔር ድል ስለሚያደርግ ዕረፍት የሚያሳጡ ኃጢአቶችንም በንስሐ ስለሚያስወግድ ዘወትር ሰላም አይለየውም፡፡ ይህ ደግሞ ለሥጋዊ ሕይወት መሠረታዊ ጥቅም አለው፡፡ ምክንያቱም ሰው በሥጋዊ ሕይወቱ ውጤታማ የሚሆነው ተማሪውም ተምሮ መመረቅ፣ ነጋዴው ነግዶ ማትረፍ፣ ሙያተኛው ሠርቶ ራስንና ወገንን መደገፍ የሚቻለው እያንዳንዱ ውስጣዊ ሰላም ሲኖረው ነው፡፡ ሰላም የሌለው ሰው ግን ዘወትር ከራሱ ጋር ስለሚያጋጭና ስለሚጣላ በማኛኛውም ቦታ የተሰጠውን ኃላፊነት የሚጣበት አቅም አይኖረውም፡፡ በሃይማኖት የሚኖር ሰው ሁሉን ማድረግ የሚቻለው በእግዚአብሔር በመደገፍ እውነተኛውን ሰላም ያገኛል፤ ልቡናውም ከጭንቀት ይጠበቃል፡፡ የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ይህንን ያስረዳሉ፡፡

«ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜንም እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም፤ ልባችሁ አይደንግጥ አትፍሩም፡፡» /ዮሐ. ፲፬፥፳፯/

«ሁሉ የሚገኝባት ከልቡናና ከአሳብ ሁሉ በላይ የምትሆን የእግዚአብሔር ሰላም በኢየሱስ ክርስቶስ ልባችሁንና አሳባችሁን ታጽናው» /ፊል. ፬፥፯/

«በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ የምትደገፍ ነፍስን ፈጽመህ በሰላም ትጠበቃለህ»/ኢሳ. ፳፮፥፫/

## ፪ኛ. መንፈስ ጠንካራ ያደርጋል


ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ብዙ ተግባራት አሉት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ እጅግ አድካሚ፣ እልህ አስጨራሽና ተስፋ አስቆራጭ የሆኑ መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በሃይማኖት /በአሚነ እግዚአብሔር/ የማይኖረው የሚታመነው ስለሌለው ተመርሮና ተስፋ ቆርጦ ሲተዋቸው በሃይማኖት የሚኖረው ግን «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» ብሎ በጠንካራ መንፈስ ሊወጣቸው ይቻለዋል፡፡ /ፊል. ፬፥፲፫/

የከነዓን ምድር እንዲሰልሉ ከተላኩት ጉበኞች /ሰላዮች/ የምንረዳው ይህንኑ ነው፡፡ የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ በተላኩበት ጊዜ ፲፪ቱም ሰላዮች ምድሪቱ መልካም እንደሆነች ነገር ግን በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ኃያላን እጅግም ግዙፋን መሆናቸውን አይተዋል፡፡ ነገር ግን ፲ሩ ተአምኖ እግዚአብሔር የጎደላቸው በመሆናቸው ተስፋ ቆርጠዋል፤ ፈተናውን ማለፍ ተስኗቸዋል፡፡ ሕዝቡንም በአመጡት ወሬ አሸብረዋል፡፡ ሕዝቡም የተስፋይቱን ምድር መውረስ ዓላማ አድርገው ብዙውን መከራ ተቀብለው በበረሃ አልፈው መጥተው ጥቂት መንገድ ሲቀራቸው «ኑ አለቃ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ » የሚሉ ሆነዋል፡፡ /ዘኍ. ፲፬፥፬/፡፡ በእምነት ጽኑአን የነበሩት መንፈስ ጠንካሮቹ ኢያሱና ካሌብ ግን «አይደለም ማሸነፍን እንችላለንና እንውጣ እንውረሳት » /ዘኍ ፲፫፥፴/ ብለዋል፡፡

በሃይማኖት የሚኖር ሰው ኃያሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን ስለሚያምን ምንም ያህል ከባድ ፈተና ቢገጥመው ያጋጠመውን ፈተና አግዝፎ፣ ራሱን እንደ አንበጣ አሳንሶ አይመለከትም፡፡ /ዘኍ. ፲፫፥፴፪/ ከዚህ ይልቅ ፈተናውን ከማለፍ በኋላ ያለውን መልካም ነገር ስለሚያይ በፈተናው ውስጥ በብርቱ መንፈስ ሆኖ ያልፋል፡፡

## ፫ኛ. ታማኝና ተወዳጅ ያደርጋል

በሃይማኖት የሚኖር መንፈሳዊ ሰው በሁሉ ነገር በሰው ፊት ይታመናል፡፡ ይህም በሁሉ ፊት ሞገስ እንዲያገኝ ስለሚያደርገው የሚቃወመው፤ ጉዳት ሊያደርስበት የሚፈልግ፣ የሚጠላው ሰው አይኖርም፡፡ ሰይጣን በቅንዓት አንዳንዶችን በክፋት ቢያስነሳባት እንኳን በፈተናው ስለሚጸና ፈተናውን ሲያልፍ ከፊት ይልቅ የሚበልጥ ታማኝነትንና ተወዳጅነት ያተርፋል፡፡ ይህንንም ከቅዱስ ዮሴፍ ሕይወት መማር ይቻላል፡፡ ለባርነት በተሸጠበት በባዕድ ሀገር ሀገርን እስከ መምራት ድረስ ታማኝነትንና ተወዳጅነትን ያገኘው ፈሪሃ እግዚአብሔር፣ አሚነ እግዚአብሔር ስለነበረው ነው፡፡ /ዘፍ. ፴፱/፡፡



## ፬ኛ. ትዕግስተኛ ያደርጋል

በሃይማኖት የሚኖር ሰው ሁሉ በፈቃደ እግዚአብሔር የሚከናወን መሆኑን ስለሚያምን በሥጋዊ ሕይወቱ ድንገተኛ ችግሮች ቢያጋጥሙት (ሀብት ንብረት ቢወድም፣አካል ቢጎድል፣...) ይታገሳል እንጂ መድኃኒት ጠጥቼ፣ ገደል ገብቼ ልሙት አይልም፡፡ ይልቁንም እንደ ጻድቁ ኢዮብ « እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ፣ እግዚአብሔርም እንደ ፈቀደ ሆነ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» እያለ እግዚአብሔርን ከማመስገን አይቦዝንም፡፡ /ኢዮ. ፩፥፳፪/፡፡ በሌላ መልኩ በሃይማኖት የሚኖር ሰው ከሰዎች የሚሰነዘሩበትን ፈተናዎች ሁሉ በትዕግስት ይቋቋማል፡፡ ክፉውን ሁሉ በመልካም /በትዕግስት/ ያሸንፋል እንጂ በክፉ ስለማይሸነፍ ለበቀልም ስለማይነሣሣ ወንጀል ፈጽሞ በሥጋው ላይ መከራን አይመጣም፡፡ /ሮሜ. ፲፪፥፳፩/፡፡

## ፭ኛ. ከመከራ ሥጋ ያድናል ይሰውራል

በሃይማኖት የሚኖር ሰው በሥጋ መከራ ቢደርስበት የሚያምነው አምላኩ በክንፈ ረድኤቱ ከመከራ ይሰውረዋል፡፡ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ክብርን፣ ዐስበ ሰማዕታትን /የሰማዕታት ዋጋ/ ያገኝ ዘንድ ፈቅዶ ካልተወው በቀር እሳቱን፣ ሰይፈ ስለቱን ሁሉ ያርቅለታል፡፡

- ዳንኤልን ከተራቡ አናብስት አፍ እንዳዳነው /ዳን. ፮፥፲-፳፫/
- ሠለስቱ ደቂቅን ከሚነድ እሳት እንደታገዳቸው /ዳን. ፫፥፰-፴/
- ሶስናን በድጋይ ተወግራ በእሳት ተቃጥላ ከመሞት እንዳዳናት /ዳን. ፲፫፥፴/

## ፮ኛ. በረከተ ሥጋን ያስጣል

በሃይማኖት የሚኖር ሰው እግዚአብሔርን በማመኑ በሥጋዊ ሕይወቱ ያሉት ነገሮች ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ፡፡ በተቀደሰ ጋብቻ ኖሮ የተባረከ ልጅ ይወልዳል፤ አሥራቱን አውጥቶ ሀብቱ ንብረቱ የተባረከ ይሆናል፤ ጥቂቱ ይበዛለታል ጉዶሎው ይሞላለታል፡፡

- አብርሃም በቅዱስ ጋብቻ ኑሮ ዘሩ የተባረከ እንደሆነ /ዕብ. ፲፮፥፰/
- የሰራፕታዋ ሴት በእግዚአብሔር አምና የነብዩ የኤልያስን ቃል ስምታ እንደተባለችው ስላደረገች ቤቷ በበረከት እንደተሞላ /1ኛ ነገ. ፲፯፥፲-፲፮/
- የዶኪማስ የሠርጉ ቤት በጌታ ተአምራት ሥራ፣ በእመቤታችን ምልጃ በበረከት እንደተጎበኘ /ዮሐ. ፪፥፲፮/

ስዕል ፩፡ዳንኤል ከተራቡ አናብስት አፍ እንደዳነ

## ፯ኛ. ድኅነተ ሥጋን ያሠጣል

ሰው በተለያየ ምክንያት የሥጋ ሕመም /ደዌ/ ሊያገኘው ይችላል፡፡ በሃይማኖት የሚኖር ከሆነ ግን በአምነቱ ብቻ ፍጹም ፈውስን ሊያገኝ ይችላል፡፡ ሃይማኖት ለደዌ ነፍስ /ኃጢአት/ በንስሐ ፈውስን እንደምትሰጥ ለደዌ ሥጋም በተአምር ፈውስን ታስገኛለች፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ብዙዎችን በእምነታቸው ምክንያት ከተለያየ ደዌ ሥጋ እንደ ፈወሳቸው በወንጌል ተጽፎ እናነባለን፡፡ /ማር. ፪፥፩፤ ሉቃ. ፲፯፥፲፱፤ ማቴ. ፱፥፳፪፤ ማቴ. ፰፥፲፫/

## ለ. ሃይማኖት ለነፍስ የሚሰጠው ጥቅም

ሃይማኖት ለሥጋ ያለውን ጥቅም ስናነሳ ሥጋን የሚጠቅሙ ነገሮች ነፍስንም የሚጠቅሙ፣ ሥጋን የሚጎዱም ነገሮች ነፍስን የሚጎዱ መሆናቸው ሊስተዋል ይገባል፡፡ ነፍስ ያለ ሥጋ አትቆምምና፡፡ በሥጋዊ ሕይወቱ ውስጣዊ ደስታ የሌለው ሰላም የተሞላበትና ስኬታማ ኑሮን መምራት

ያልቻለ ሰው ስለነፍሱ ደኅነት የማይጨነቅ ለመንፈሳዊ ሕይወት ግድ የለሽ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን በሃይማኖት የሚኖር ሰው በነፍሱ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛል፡፡

### ፩ኛ. በነፍሱ ደኅነትን ያገኛል

ሰው በነፍሱ ደኅነትን አገኘ የምንለው ከዘለዓለም ፍርድ አምልጦ ገነት መንግስተ ሰማያትን መውረስ ሲችል ነው፡፡ ለዚህ ደኅነት ነፍስ ለመብቃትም ርቱዕ ሃይማኖትን መያዝ በጐ ምግባር መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ያለ ሃይማኖት ደኅነተ ነፋስን ማግኘት የለም፡፡ «በእርሱ ያመነ አይፈረድበትም፤ በእርሱ ያላመነ ግን ፈጽሞ ተፈርዶበታል»/ዮሐ ፫፥፲፰/

እምነት ወደ ደኅንነት ለመድረስ ለሚደረገው የሕይወት ሙሉ ጉዞ የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ሮማዊውን የእስር ቤቱን ዘበኛ እንዲህ ያሉት፡- «በጌታችን በኢየሱስ ክርሰቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ»/ሐዋ. ፲፮፥፴፩/

### ፪ኛ. በነፍሱ ዘላለማዊ ዋጋን ያገኛል

ሰው ሃይማኖትን ጠብቆ በምግባር ጸንቶ በነፍሱ ድኅነት ሲያገኝ ነፍሱ የማይጠፋ ዘላለማዊ ሽልማትን ትቀዳጃለች፡፡ ይህም የነፍስ ሰማያዊ ዋጋዋ ነው፡፡ ይህ ዋጋ፡-

- የሕይወት አክሊል ነው

«መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ፡፡ እንግዲህ የጽድቅ አክሊል ይቆየኛል ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባሉ፡፡ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም፡፡» /፪ጢሞ ፬፥፯-፲/

- የክርስቶስ መለኮታዊ ክብር ተካፋዮች መሆን ነው ይህም ክርስቶስን መምሰል ነው

«እኛስ ሀገራችን በሰማይ ያለችው ናት፤ ከዚያም እርሱን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርሰቶስን እንጠባበቃለን፡፡ እርሱም እንደ ከኃሊነቱ ረዳትነት መጠን የተዋረደውን ሥጋችንን የሚያድሰው ክቡር ሥጋውንም እንዲመስል የሚያደርገው፣ የሚያስመስለውም ሁሉም የሚዛለት ነው፡፡»/ፊል ፫፥፳ እና ፳፩/

- እግዚአብሔር መንግስት መውረስ ነው

ሰው በቀናው ሃይማኖቱና በበጐ ምግባሩ ሐዘን፣ ጩኸት፣ ሕማም፣ መከራ፣ ሞት የሌለባትን የእግዚአብሔር ክብር የሞላበትን መንግስቱን ይወርሳል፡፡ /ራዕ. ፳፩፥፩-፳፯/

፩.፬ ስለ ሃይማኖት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተላልፈው መልእክት

## በአንዲቷ ሃይማኖት እስከመጨረሻው መጽናት

ሃይማኖታችንን እስከመጨረሻው አጽንተን ልንጠብቃው የሚገባ ቁም ነገር ነው፡፡ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስም « የመጀመሪያ እምነታችንን እስከመጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና፡፡ » ዕብ 3፥14 እንዲሁም ቅ/ጳውሎስ እረፍቱ (ሞቱ) በተቃረበ ጊዜም « ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል » በማለት በሃይማኖታችን መጽናት እንደሚገባ በቃሉም በህይወቱም ያስተምረናል፡፡
በሃይማኖታችን እስከመጨረሻው ድረስ መጽናት በመጽሐፍ ቅዱስ ገድላቸው በክብር በፈፀሙ አባቶች እና እናቶች የህይወት ጉዞ የምንረዳው ሲሆን እኛም በአምነታችን ብንፀና ድህነትን እንደምናገኝ መድኅኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ « እስከ መጨረሻ የሚፀና እርሱ ይድናል » ማቴ 24፥13 በማለት አባታዊ ምክሩን ሰጥቶናል፡፡ እኛም በ፤ኛ ቆሮ 16፥13 « ንቁ በሃይማኖት ቁሙ » የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርትን በማሰብ በየትኛውም መንገድ የሚመጣውን ፈተና እየታገስን ድል በመንሳት በሃይማኖታችን ፀንተን ልንቆም ይገባል፡፡

## ሃይማኖት በሥራ የምትገለጽ መሆን አለባት

በመልካም ስራ የማትገለጥ ሃይማኖት በራሷ የሞተች ጥቅምም የሌላት ናት፤ በቅ/ያእቆብ መለእክት ያዕ2፥18-19 « ወንድሞች ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን » በማለት እምነት ያለስራ ከንቱ የሆነ ነገር እንደሆነ ይመክረናል፡፡ በስራ ያማይገለጥ ሃይማኖት ከአጋንንት እምነት ጋር ልንመስለው እንችላለን፡፡ ያዕ 2፥19 « አጋንንት ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል » እንዲል፡፡
አባታችን ቅ/ያዕቆብ ሊያጸድቅ ሚችለው እምነትም እንደ አባታችን አብርሃም ያለ በስራ የተገለጠ እምነት እንደሆነ የአብርሃምን ታሪክ እያስተወሰ ያስተምረናል፡፡ ያዕ2፥2-26 « ኣባታችን አብርሃም ልጁን በመሰዊያው ባቀረበ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን ; » እንዲል፡፡
እምነት ያለ ምግባር ምውት እንደሆነ ሁሉ ስራም ያለእምነት ( ሃይማኖት ) ከንቱ ነው ፡፡ እግዚአብሔርን ደስ ልናሰኘው የምንችለው ሁለቱን አዋህደን መኖር ስንችል ብቻ ነው፡፡

## ሃይማኖት የተጋድሎ ሕይወት ነው

ሃይማኖትና ተጋድሎ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ አንድ ሰው በሃይማኖት ውስጥ አለ የሚባለው ዘወትር በሃይማኖቱ የሚመጣበትን ፈተና በተጋድሎ (በድል) ሲወጣ ነው፡፡ የዚህን ዓለም ምኞት፣ ከራስ የሚመነጭ ፈተና፣ ከዲያብሎስ የሚሰነዘርን የኃጢአት ጦር የምንዋጋው (እስከመጨረሻው የምንጋደለው) ድል የምንነሳው በተሰጠን አንዲት ሃይማኖት ሆነን ስንኖር ብቻ ነው፡፡
መጽሐፍ ቅዱስም በልዩ ልዩ መልኩ እንዲህ ያስተምረናል፡-
1ኛ ጢሞ 6፥12 ፡- « መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል የተጠራህለትንም በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የተመንህለትን የዘላለም ሕይወት ያዝ »
ይሁ 1፥3 ፡- «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠች ሃማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኳችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ »

ንዘብን ከመውደድ እና ከሃሰተኛ መናፍቅ መምህራን የሃሰት ትምህርትም ልንጠነቀቅ የሚገባ ነገርም እንደሆነ ማስተዋል የተገባ ነው ፡፡ ብዙዎች ገንዘብን ከመውደድ እና በአጋንንት እና በመናፍቃን ትምህርት በመታለል ከሃይማኖት ከደው ወጥተዋል መጽሐፍ ቅዱስም ይህን ይመሰክራል፡፡

1ኛ ጢሞ 6÷10 ፡- « ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶች ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ » እንዲል፡፡

1ኛ ጢሞ 4÷2 ፡- «በውሸተኞት ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖት ይክዳሉ»

ስለሆነም በዚህ ዓለም ስንመላለስ በሃይማኖት ሆነን የሃጢአትን ሥራ ልንቃወም እና ልንታገል ኃይለ እግዚአብሔርንም ተላብሰን የፅድቅ ጦር እቃ እምነቱን፣ ፀሎቱን፣ ስግደቱን የንስሃ ህይወቱን በሥጋ ወደሙ ታትሞ የመኖርን ዝግጅት ገንዘብ አድርገን ድል ልንነሳ ይገባናል፡፡

ኤፌ 6÷16 ፡- «በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን ክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ ምትችሉበትን ጋሻ አንሱ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም እግዚአብሔር ቃል ነው፡፡» ይህንን ማድረግ ስንችል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኛ ለማስተማር ስለ ራሱ ሲናገር 2ኛ ጢሞ 4÷7 « መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫየን ጨርሻለው ሃማኖቴን ጠብቄአለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል » እንዳለ እኛም የተጋድሎአችንን ዋጋ የጽድቅን አክሊል በመንግስተ ሰማያት ከጌታችን ዘንድ እንቀበላለን ፡፡

## ፩.፰ የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ሃይማኖት ማመን እና መታመን በሚሉ ሁለት ቃላት ይተረጎማል፡፡ ማመን ስንል የተማሩትን በልብ መቀበል ሲሆን መታመን ማለት ደግሞ እውነት ነው ብለው የተቀበሉትን በአፍ መመስከር በተግባር መግለጥ ነው፡፡
- ሃይማኖት የምግባር፣ የትሩፋት መሠረት ነው፤ ምግባር ትሩፋት ከመሥራት በፊት ሃይማኖትን መያዝ ይገባልና፡፡ ሃይማኖት ከእውቀት በላይ ነው፤ በስሜት ሕዋሳት መርምረው የማይደርሱባቸውን ያስረዳልና፡፡ ሃይማኖት ከዚህ በተጨማሪ ተስፋን የሚያረጋግጥ ነው፡፡
- እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል ሃይማኖት የሚያስፈልጋቸው ሰውና መላእክት ብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሃይማኖት እንዲኖራቸው የሚያደርግ እውቀት ስላላቸውና ሕያዋን ፍጥረታት ስለሆኑ ነው፡፡
- በእግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ያመኑ ቅዱሳን መላእክት ናቸው፡፡ ለዚህም ሃይማኖት የተጀመረው በዓለመ መላእክት ነው፡፡ በተጨማሪም ሃይማኖት ለነፍስም ለሥጋም በረካታ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ህልወተ ፈጣሪ - የፈጣሪ መኖር

***ውድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ የፈጣሪን መኖር ማመን የሃይማኖት መሠረት ስለመሆኑ፣ የፈጣሪን መኖር ስለሚያስገነዝቡ አስረጂዎች፤ ስለእግዚአብሔር ባሕርያትና ስሞች እንመለከታለን፡፡ መልካም ቆይታ!***

## ፪.፩ የሃይማኖት መሠረት - ፈጣሪን ማመን

***ውድ ተማሪዎች ህልወተ ፈጣሪ/የፈጣሪ መኖር/ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?***

ሃይማኖት ማለት የ፳፪ቱ ሥነ-ፍጥረት አስገኚ፣ የሚታየውና የማይታየውን ዓለም መጋቢ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል ረቂቅ ምሉዕ ሰፉሕ፣ ሕያው ባሕርይ የሆነ እግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን ነው፡፡ የዚህ እምነት መሠረቱ የፈጣሪ መኖር /ህልዎተ ፈጣሪ/ ነው፡፡ የፈጣሪ መኖር ስንል ግን ለአኗኗር ጥንት ወይም ፍጻሜ አለው ማለት ሳይሆን ዘመኑ የማይለካ ከጥንት በፊት የነበረ ጥንት ከመጨረሻም በኋላ የሚኖር መጨረሻ ብለን ለመናገር መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ሃይማኖትን ያጸኑ ኦርቶዶክሳውያን አባቶች በጸሎተ ሃይማኖት እንዲህ ብለዋል፡፡

«ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውን» /ሰለስቱ ምዕት/

በመሠረቱ ዓለም ያለ አስገኚ የተገኘ፣ ከተገኘም በኋላ ያለ መጋቢ በራሱ የሚኖር አይደለም፡፡ ሸክላ ያለ ሰሪ፣ ቡቃያ ያለ መሬት፣ ልጅ ያለ እናት አባት እንደማይገኙ ሁሉ ዓለምም ያለ አስገኚ የተገኘ አይደለም፡፡ ለተፈጥሮው አስገኚ፣ ለኑሮው ሠራዒ መጋቢ፣ ለጉዞው መነሻና መድረሻ አለው እንጂ፡፡ ይህንንም በልቡና መርምረን በቃለ እግዚአብሔር ምስክርነት በእምነት እናውቃለን፡፡ “ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ፣ የሚታየው ነገር ከማይታይ እንደሆነ በእምነት እናውቃለን” /ዕብ. ፲፩÷፫/

***ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች ከዚህ ቀጥሎም የፈጣሪን መኖር የሚያስረዱ ነገሮችን እንመለከታለን***

## ፪-፪ የፈጣሪ መኖር የሚያስረዱ ነገሮች

### ሀ. ሥነ-ፍጥረት

የማይታይና የማይዳሰሰው አምላክ በሚታይና በሚዳሰሰው ሥራው /ሥነ-ፍጥረት/ ራሱን ስለገለጠ ሥነ-ፍጥረት ለፈጣሪ መኖር አንድ አስረጂ ነው፡፡ ሥነ ፍጥረት የፈጣሪ መኖር የሚያስረዳው በሁለት ወገን ነው፡፡ እነሱም፡-

፩. ከፍጥረታት መካከል በራሱ የተፈጠረ በራሱም ላይ ብቻውን ሙሉ ሥልጣን ያለው ፍጥረት አለመኖሩ፡፡ ይህም ለተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ አስገኚ ፈጣሪ በተፈጠረውም ፍጥረት ላይ ሥልጣን ያለው ኃይል እንዳለ ያሳየናል፡፡

፪. በተፈጠረው ፍጥረት መካከል ያለው አብሮ የመኖር ስምምነት ለምሳሌ፡- ከእንስሳት የሚወጣውን የተቃጠለ አየር በመጠቀም በምትኩ ለእንስሳት በሕይወት መኖር የሚያስፈልገውን አየር ተክሎች መለገሳቸው፣ በዚህም በከባቢ አየር ውስጥ ለሁሉም በሕይወት

ለመኖር የሚያስፈልጉ አየራት መጠናቸው ሳይዛባ የሚኖር መሆኑ በቂ አስረጂ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን እንስሶችም ተክሎችም ፈልገው አስበውት የሚያደርጉት አለመሆኑ ፍጥረታትን ፈጥሮ በሥርዓት የሚያስተዳድር ኃይል /አምላክ/ እንዳለ ያስረዳል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍትም በሥነ-ፍጥረት የፈጣሪ ህልውና የሚታወቅ መሆኑ ይመሰራክሉ

«የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉና ጌትነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብና በመመርመር ይታወቃል፡፡» /ሮሜ. ፩፥፳/

«አሁን ግን እንስሶችን ጠይቅ ያስተማሩህማል፣ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩህማል፣ ለምድር ንግራት እርሷም ትተረጉምልሃለች፣ የባህርም ዓሳዎች ያስረዱሃል፣ የእግዚአብሔር እጁ ይህን ሁሉ እንዳደረገ» /ኢዮ. ፲፪፥፯-፲/

«ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል»/መዝ. ፲፰፥፩/

ሌላው ግዕዛን /አእምሮ/ የሌላቸው ወቅቶች ጊዜያቸውን ጠብቀው መፈራረቃቸው በዚህም ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ በምድር ላይ ምግበ ሥጋን አግኝቶ መኖር መቻሉ ወቅቶችን የሚያፈራርቅ ኃይል መኖሩን የሚያስረዳ ምስክር ነው፡፡

«ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራን እየሠራ ከሰማይ ዝናምን፣ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም፡፡» /ሐዋ. ፲፬፥፲፯/

## ለ. የሕሊና ምስክርነት

ሰው የተጻፈ ሕግ ባይኖረውም እንኳ መጽሐፍትንም ባያነብ አዋቂ ፍጥረት በመሆኑ መልካምና ክፉውን በሕሊናው አመዛዝኖ መለየት ይቻለዋል፡፡

«ሕግ የሌላቸው አሕዛብስ እንኳ ለራሳቸው ሕግ ይሠራሉ. . .በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ፣ ከሥራቸውም የተነሳ ይታወቃል ሕሊናቸውም ይመሰክርባቸዋል ይፈርድባቸዋልም፡፡» /ሮሜ. ፪፥፲፬ ና ፲፭/

ሰው የሁሉ ፈጣሪና ገዥ መኖሩን አምኖ ከሞት በኋላ ያለውንም ሕይወት ተስፋ አድርጎ ሲኖር በሕሊናው ፍጹም ሰላምን ያገኛል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኝ ሥራ ሲሠራ /ሲገድል፣ ሲሰርቅ. . . ./ ሠሪው የሃይማኖት ሕግ ባይኖረውም እንኳ የተፈጥሮ ዳኛ ሕሊናው ስለሚፈርድበት በጭንቀት ይኖራል፡፡ ይህም ማለት ሰው በሕሊናው አንድ ቅንና እውነተኛ ፈራጅ መኖሩን ያውቃል ማለት ነው፡፡

## ሐ. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ባደረገው ንግግር

እግዚአብሔር ከሰው ጋር በራዕይ በሕልምና በገሃድ ቃል በቃል ያደረገው ንግግር ህልውናውን ያረጋግጣል፡፡

«እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበረ፡፡» /ዘፀ. ፴፫፥፲፩/

«የሙሴ እህት ማርያምንና አሮንንም በዐምደ ደመና ተገልጦ እንዳነጋገራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል፡፡» /ዘኍ. ፲፪፥፩-፲/ቀደምት አበው ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የእግዚአብሔርን መኖር በስፋት እና በጥልቀት አስተምረዋል ፣ ትንቢት ተናግረዋል ትንቢታቸውም በጊዜው ፍጻሜን አግኝቶም አልፏል፡፡

## መ. የሰው ልጅ ሃይማኖታዊ ዝንባሌ

ከጥንት ጀምሮ ያለውን የሰው ልጅ ታሪክ ስንመለከት ወይ በእግዚአብሔር ሲያምን አልያም የእግዚአብሔር የእጁ ሥራዎች በሆኑ በፀሐይ፣ በጨረቃ...ወዘተ ሲያምን ወይም ደግሞ በራሱ በእጁ አለዝቦ፣ ጠርቦ ቀርጾ ያዘጋጃቸውን ጣኦታቱን ሲያመልክ መኖሩን እንገነዘባለን፡፡ ይህም የሰው ልጅ ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ የተፈጥሮ ፍላጐቶች ባልተለየ ሁኔታ የእምነት ዝንባሌና ስሜት እንዳለው ያሳያል፡፡ ሰው እንዲህ በተፈጥሮው በራሱ ምሉዕ አለመሆኑ፣ የማይሸነፍ ብርቱ ረዳት መፈለጉ ሁሉን ቻይ፣ ጸባዖት /አሸናፊ/ አምላክ መኖሩን ያሳያል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የሰውን የማመን ዝንባሌ ተጠቅሞ በአቴና ከተማ «ለማይታወቅ አምላክ» የሚል ጽሑፍን መነሻ አድርጎ በአቴና ከሚኖሩት አንዳንዶችን ወደ አምልኮ እግዚአብሔር አምጥቷቸዋል፡፡ /ሐዋ. ፲፯፥፳፪-፴፬/

ከላይ የተዘረዘሩትን አስረጂዎች ተገንዝቦ ፈጣሪ እንዳለ ማወቅ አእምሮ ለተሰጠው ልጁ ስውር አይደለም፡፡ ሆኖም ይህን አለማስተዋልና የእግዚአብሔር ህልውና መጠራጠር ግን ስንፍና ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ይህንኑ ያስረዳል፡፡

«ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል»/መዝ. ፲፫፥፩/

«እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልቦናቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና፤ በሚታዩ መልካም ነገሮች ያለውን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው፤ ሥራውንም እያዩ ሠሪውን አላወቁትም፡፡»/ጥበ. ፲፫፥፩/

## ፪-፫ የአምላክ ስሞች /አስማተ አምላክ/

ሀለወተ ፈጣሪን ተረድቶ በሃይማኖት የሚኖር ሰው የሚያምነውን አምላኩን እሱነቱንና ስሙን አእምሮው በሚፈቅድለት መጠንና ፈጣሪውንም እሱነቱን በአስታወቀለት መጠን ሊያውቀው ሊረዳው ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር ባሕርዩና ግብሩን የሚገልጸው ስሙ ለሰው ልጅ የታወቀለት በራሱ በእግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር ከሙሴ በፊት ለነበሩት አበው እሱነቱን ሲገልጥላቸው ስሙ "ኤልሻዳይ" እንደሆነ በመንገር እንጂ ስሙ እግዚአብሔር መሆኑን አልገለጠላቸውም ነበረ፡፡ የዚህም ስም ትርጉም ሁሉን ቻይ ማለት ነው፡፡ ለሰው ልጅ በቅድሚያ ስለ እግዚአብሔር ግልጥ የሆነው ከሀሊነቱ /ሁሉን ቻይ መሆኑ/ ነውና፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በሊቀ ነብያት ሙሴ ስሙ ማን እንደሆነ ተጠይቆ ሲመልስ "ያለና የሚኖር" ዳግመኛም የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ የሚለው ለዘለዓለም ስሙ እንደሆነ ገልጧል፡፡ /ዘፀ. ፫፥፲፬/

ከዚህ በመቀጠልም በእስራኤላውያን ቋንቋ “ይሆዋ” ወይም “ያህዌ” በሚል ስም እንደሚጠራ ግልጽ አድርጓል፡፡ ይህም ወደ ግዕዝ ሲመለስ “እግዚአብሔር” በሚል ቃል ተተክቷል፡፡

«እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ ለአብርሃምም ለይስሐቅም በያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል /አልሻዳይ/ አምላክ ተገለጥሁ፡፡ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም ነበረ፡፡» እንዲል/ዘፀ. ፮፥፫/

ለነብዩ ለኢሳይያስም ይህንን ስሙን ገልጾለታል፡፡

«እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ፣ ስሜ ይህ ነው፣ ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጸ ምስሎች አልሰጥም»/ኢሳ. ፵፪፥፰/

ይህም እግዚአብሔር የሚለው ስም የሁሉ ፈጣሪ፣ አስገኚና መጋቢ ከነባሕርዩና ግብሩ እሱነቱን በጠቅላላ የሚገልጽ ስም በመሆኑ ክቡር ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላካዊ ግብሩን የሚገልጡ ስያሜዎች *« አምላክ፣ ፈጣሪ፣ ጌታ፣ ከሃሊ፣ መጋቢ፣ አዳኝ፣. . . ወዘተ»* ተብሎ ይጠራል፡፡ አምላካዊ ባሕርዩንም በሚገልጡ *« ሕያው፣ ዘላለማዊ፣ ያለና የሚኖር፣ መሐሪ፣...»* በሚሉ ስያሜዎች ይጠራል፡፡ እግዚአብሔር የሚለው ስያሜ ግን እርሱነቱን ከነባሕርይውና ግብሩ የሚገልጽ በመሆኑ ይህ ስም ለፈጣሪ የመጨረሻው /የመጠሪያ ስም/ ነው፡፡ በዚህም ስም አምልኮታችንን እንፈጽማለን፡፡ ይህም ስለሆነ ከዐሥርቱ ሕግጋት አሪት አንዱ ይህንን ቅዱስና ክቡር ስም በከንቱ መጥራትን ይከለክላል፡፡

«የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ አምላክህ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና»/ዘፀ. ፳፥፯/

“ያሆዋ” ወይም “ያህዌ” የሚለው ስም በአይሁድ ዘንድ በዓመት ውስጥ በተወሰነ ጊዜ ያውም በሊቀ ካህናቱ ብቻ ካልሆነ በቀር በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ሰው በግልም ይሁን በማኅበር ጸሎት ላይ አይነሣም፡፡ በዚህ ፋንታ ግን ኤሎሄ/ኤሌሂም /አምላክ/አምላኬ/፣ አዶን/አዶኒ/አዶናይ /ጌታ/ጌታዬ/ ኢሊዮን/ኤል /ልዑል/ በሚል የተጸውዖ ስም እግዚአብሔርን ይጠሩታል፡፡ እነዚህንም የተጸውዖ ስሞች እግዚአብሔር/ያህዌ ከሚለው ጋር እያጣመሩ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ

«ጌታ እግዚአብሔር» /ሕዝ. ፪፥፬/

«ልዑል እግዚአብሔር» /ዘፍ. ፲፬፥፲፰/

«እግዚአብሔር አምላክ»

በዚህም መሠረት ለልጅም ይሁን ለድርጅት ስያሜ ሲያወጡ ይህንን ቅዱስ ስም በቀጥታ መጠቀም ተገቢ እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡

## ፪.፬ የእግዚአብሔር ባሕርያት /ባሕርያቱ ለእግዚአብሔር/

በዚህ ርዕስ ሥር የምንመለከተው እግዚአብሔር ስለ ባሕርይው የሰው ልጅ እንዲያውቀው በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል ከተገለጠው ጥቂቱን ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ግን ሰው የፈጣሪውን ባሕርይ መርምሮ የሚደርስበት አእምሮ የሚገልጽበትም ቋንቋ አይኖረውም፡፡ ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን የእግዚአብሔር ባሕርያት ናቸው ስንል ከሌላ ከማንም ያላገኛቸው ማንም ደግሞ ከእርሱ ሊወስዳቸው የማይቻለው የራሱ ገንዘቦቹ ናቸው ማለታችን ነው፡፡ ከዚህ ከባሕርይ ገንዘቡም ለፍጡር ቢሰጥ አንዲት ሻማ ብርሃንን ለሌሎች ሻማዎች ብትሰጥ የራሷ ብርሃን እንደማያልቅባት የእርሱም ገንዘቡ የማያልቅበት ነው፡፡

*እግዚአብሔር በባሕርዩ፡-*

### ፩. ዘላለማዊ /ሕያው/ ነው

እግዚአብሔር የሌለበት ጊዜ የለም፡፡ ፍጥረታትን ከመፈጠሩ በፊት በባሕርዩ የኖረ ነው፡፡ የሚታዩትና የማይታዩት ፍጥረታት ከእርሱ ተገኙ እንጂ እርሱን የፈጠረ/ያስገኘ ማስገኘትም የሚቻለው ሌላ ኃይል የለም፡፡እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ነበረ፡፡ የጊዜና የዘመን ፈጣሪንና ባለቤት እንጂ ዕለትና ጊዜ እርሱን አይቀድሙትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ ምስክር ነው፡-

«ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ መቼም መች አንተ ነህ» /መዝ. ፹፱፥፪/

እግዚአብሔር በራሱ የነበረ ያለና የሚኖር ስለሆነ በጊዜ አይወሰንም ጊዜም እርሱን አይወስነውም፡፡ በባሕርይውም እርጅናና መለወጥ የለበትም፡፡

«አቤቱ አንተ አስቀድመህ ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፡፡ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፡፡ ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጡማል፡፡ አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዓመትህም ከቶ አያልቅም»/መዝ. ፻፩፥፳፭-፳፯/

ከእግዚአብሔር በፊት የነበረ መጀመሪያ አልነበረም፡፡ ከእርሱም በኋላ የሚኖር መጨረሻ አይኖርም፡፡ እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ ፊተኛና ኋለኛ ነው፡፡

«የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር የሚቤዥም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔ ኋለኛ ነኝ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም፡፡» /ኢሳ. ፵፬፥፮/

በተጨማሪም የሚከተሉት ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ይገልጣሉ፡፡ /ራዕይ. ፩፥፲፰፤ ፩፰/፣ ጢሞ.፩፥፲፯፣ ዘፀ. ፫፥ ፲፬/

### ፪ኛ. ምሉዕ ነው

እግዚአብሔር የሌለበት/የማይኖርበት ቦታ የለም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በጊዜ እንደማይወሰን ሁሉ በቦታም አይወሰንም፤ በሁሉም ቦታ እርሱ አለ፡፡ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ሙሉ እንደሆነ ልበ አምላክ ዳዊት እንደዚህ ገልጾታል፡፡

«ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፡፡ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ፡፡ እንደ ንስር ክንፍን ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበር በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ታኖረኛለች»/መዝ. ፻፴፰-፯-፲/

በነብዩ ኤርምያስም አድሮ እግዚአብሔር ምሉዓ ባሕርይነቱን ገልጧል፡፡

«እኔ ቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ ሩቅ አምላክ አይደለሁም ይላል እግዚአብሔር ሰው በስውር ቦታ ቢሸሽግ እኔ አላየውምን? ሰማይና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን ይላይ እግዚአብሔር» /ኤር. ፳፫፥፳፫ እና ፳፬/

በተጨማሪም የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመልከት፡፡ /ኢሳ. ፷፥፩፤ መዝ. ፻፪፥፲፱፤ ኢሳ. ፮፥፫/

### ፫ኛ.ሁሉን ማድረግ የሚቻለው /ከሀሌ ኩሉ ነው/

እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚቻለው የሚሳነው የሌለ ነው፡፡ የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ የሚታየውም የማይታየውም ዓለም የችሎታው ውጤት ነው፡፡ ከተፈጠረው ፍጥረት አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ የሆነ የለምና፡፡ /ዮሐ. ፩፥፫/ እግዚአብሔር ሁሉን ያለአማካሪና ረዳት ያስገኘ ስለሆነም ሁሉ በእጁ የተያዘ ነው፣ ሁሉም በሥልጣኑ ሥር ነው፣ ሁሉን የመወሰን ስልጣን ያለውም እርሱ በቻ ነው፡፡ /ኢሳ. ፵፥፲፪-፲፯፣ ፵፫፥፲፫፤ ፵፬፥፯/

እርሱ ራሱ እግዚአብሔርም ከሣራ ጋር በአደረገው የቃል በቃል ንግግር ሁሉን ቻይነቱን ገልጧል፡፡ «በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን» /ዘፍ. ፲፰፥፲፬

*ጻድቁ ኢዮብም፡-*

«ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ የሚሳንህም እንደሌለ አወቅሁ» ብሏል፡፡/ኢዮ. ፵፪፥፪/ ተጨማሪ ጥቅሶች፡- /ሉቃ. ፲፰፥፳፯፤ ፩፥፴፯፤ መዝ. ፻፴፬፥፮/

### ፬ኛ. ቅዱስ ነው

እግዚአብሔር በባሕርይው ልዩ ክቡር ነው፡፡ ርኩሰት የማይስማማውም ፍጽም ንጽሕ ነው፡፡ እግዚብሔር የባሕርይ ገንዘቡ በሆነ በዚህ ቅድስናው ከማንም ጋር የማይነጻጸር የሚመስለውም የሌለ ነዉ፡፡

«አቤቱ፡- በአማልክት መካከል አንተን የሚመስል ማነው በቅዱሳንም ዘንድ እንደ አንተ የከበረ ማን ነው ?»እንዲል፡፡ዘፀ ፲፭÷፲፩

የሳሙኤል እናት ሐናም ይህን የእግዚአብሔርን ልዩ ቅድስና እንዲህ ትገልጸዋለች፡፡ «እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና» /፩ኛ ሳሙ. ፪፥፪/

ቅዱሳን መላእክትም ይህን የእግዚብሔርን ዘላለማዊ ቅዱስና በመግለጥ ያለማቋረጥ እንዲህ እያሉ ያመግኑታል፡፡ «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ» /ራዕ. ፬፥፰/

ለዚህም ነው ቅዱስና ገናና ንጹሐ ባሕርይ እግዚአብሔር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው በንጽሐ ባሕርይ ለክብር ስለፈጠረዉ የሰው ልጅ ከማንኛውም ርኩሰት ራሱን እንዲያነጻና በቅድስና እንዲኖር የታዘዘው፡፡ «የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እንዲሁ እናንተም በአካሄዳችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁሉ፡፡» /፩ኛ ጴጥ. ፩፥፲፭/

ለግንዛቤ ያህል ከላይ ያሉትን ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት አነሳን እንጂ የእግዚአብሔር ባሕርያት እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡ አስቀድመን እንደተመለከትነው ፍጡር የፈጣሪውን ባሕርይ ሰፍሮ ቆጠሮ ዘርዝሮ የሚጨርሰው አይደለምና፡፡

### ፭ኛ. እግዚአብሔርን ማየትና ሙሉ ለሙሉ ማወቅ አለመቻሉ፡-

እግዚአብሔር በባህርይው ፍፁም መንፈስ ስለሆነ ሊታይና ሙሉ ለሙሉ ሊታወቅ አይችልም፡፡ እግዚአብሔርን የሚመስል ከቶ ምንም ነገር የለም፡፡

ሐዋ 17÷29 "አምላክን በሰው ብልኀትና ሐሣብ የተቀረፀውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባም፡፡" ተብሎ እንደተፃፈ እግዚአብሔርን ማንም ያየው ሰው እንደሌለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦአል፡፡ ሉቃ 10÷22 "ውሱን የሆነው የሰው ዐይን ውሱንነት የሌለውን እግዚአብሔርን ማየት አይቻለውም፡፡ ፀሐይን እንኳ ትኩር ብለን በዐይናችን ለማየት የማንችል ከሆነ እንዴት አድርገን በባህሪው ፍፁም ረቂቁና ምሉዕ የሆነውን መለኮት ልናየው እንችላለን? መላዕክት እንኳን ከሰው በበለጠው ረቂቃን ሆነው ቢገኙም ረቂቁን (በባሕርዩ) የሆነው እግዚአብሔርን አይተውት አያውቁም፡፡ ነገር ግን ሰው እና መላዕክት እግዚአብሔርን በባሕርየ መለኮቱ አይተውት ባያውቁም አቅማቸው ሁኔታቸው የሚፈቅድላቸውን ያህልና ሊረዱት በሚችሉበት ሁኔታ እግዚአብሔር ራሱን በዘፈቀደ በልዩ ልዩ ምሣሌዎች ይገልጽላቸዋል፡፡

ለምሣሌ ፡- ኢሣ 6÷2 "ሱራፌል ፊትህን ማየት አይቻለንም ብለው በክንፋቸው ፊታቸውን እንደሚሸፍኑ ተገልጿል፡፡"

ለሙሴ በእሳት ነበልባል መልክ ዘፀ 3

ለኢሳያስ በዘፍን ላይ ባለ ንጉሥ አምሳል ኢሳ 6

ለዳንኤል በራዕይ በሽማግሌ ዳን 7÷13-14

ለብርሃም በሦሥትነት እና አንድነት እንደ ሰው በሽማግሌ አምሳል ዘፍ 1÷9፡18 በመሆን ተገልጦላቸዋል፡፡

ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ በሀዲስ ኪዳን ባሕርየ መለኮትን ከባሕርየ ሰብእ አካለ መለኮቱን ከአካለ ሰብእ ጋር በተዋህዶ አንድ እስካረገበት ጊዜ ድረስ አካለ መለኮትን ያየው አንድስ እንኳን የለም በተዋህዶ አየነው እንጂ፡፡

በተዋሕዶ አምላክ ሰው በመሆኑ ሰውና መላእክት እግዝአብሔርን አዩት፡፡

### ፮ኛ. የእግዚአብሔር በራሱ መኖር፡-

ይህ ባህሪ (ጠባይ) በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ እንጂ ለማንኛውም ፍጡር የሌለው የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው፡፡

የእግዚአብሔር በራሱ መኖር ስንል ለአኗኗሩ ምንም ምን ምክንያት ያለው ሲሆን ለመኖሩ ምንም ምክንያት የሌለው ለራሱ የሚኖር ነው፡፡ እርሱ በራሱ የሚኖር ሲሆን ፍጥረታት ግን በእግዚአብሔር አስገኝነት የሚኖሩ ናቸው፡፡

ጌታችን መድኅነ ዓለም እየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 5÷26 ላይ አብና ወልድ በእነርሱም ህልው ሆኖ ያለው መንፈስ ቅዱስ በራሳቸው እንደሚኖሩ ወይም በራሳቸው ሕይወት እንዳላቸው የገለጠው በማያሻማ ቃል ነው፡፡

ዮሐ. 5÷26 "አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና" በማለት አስተምሮናል፡፡

### ፯ኛ. የማንም ዕርዳታ የማያስፈልገው መሆኑ፡-

እግዚአብሔር አምላክ ለሀሣቡ አማካሪ ለድርጊቱ አጋዥ የማይሻ ሁሉን እንዳሠበ እንደወደደ ያለከልካይ ያለ አማካሪ ያለረዳት መፈፀም የሚቻለው ሁሉን በራሱ ፈቃድ፣ኃይል፣ሥልጣን ያለ እንከን እና ጉድለት የሚያከናውን ነው፡፡

ቅዱሳን መጽሐፍም የእግዚአብሔርን ያለማንም አጋዥነት ሁሉን አድራጊ መሆን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡-

ሐዋሥ 17÷25 "ሕይወትና እስትንፋስን ÷ሌሎችንም ነገሮች ለሰው ሁሉ የሚሰጥ እርሱ ስለሆነ ምንም ነገር አይጐድለውም ÷ የሰውም እርዳታ አያስፈልገውም"

ሮሜ 11÷34 "የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያውቅ ማንም የለም የእርሱ አማካሪ የሚሆን የለም» ኢሳ 40÷13-14 "የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ወይም አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ ወይስ ማን መከረው? የፍርድንም መንግድ ማን አስተማረው? ዕውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?"

### ፰ኛ.የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት፡-

- እግዚአብሔር ከዘመን በላይ የሆነ ዘላለማዊ በመሆኑ ያለፈውን የአሁነንና የወደፊቱን በግልጥ የሚያውቅ የሚሆነው ነገር ከመሆኑ አስቀድሞ የሚያውቅ በፊቱ አንዳች የሚሰወር ነገር የሌለ ኃያል አዋቂ አምላክ ነው፡፡ አንድን ነገር ከመታሠቡ በፊት አስቀድሞ የሚያውቅ አዋቂ ነው፡፡
- እግዚአብሔር የሚሆነውን አስቀድሞ በጐውንም ክፉውንም ያውቀዋል ሲባል የሰውን ልጅ ነፃ ፈቃድና ፍላጐት አይገድበውም፡፡ የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ ደግሞ እርሱ ወደሚፈልገው አቅጣጫ ይመራዋል ማለት አይደለም ወይም ሰው ሁሉ እግዚአብሔር የወሰነለትን እንጂ ሌላ ነገር ለማድረግ ነፃነት የለውም ማለት አይደለም፡፡
- በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው የባሕርይ እውቀት እጅግ ፍፁምና ከፍጹምነት በላይ የሆነ ነው፡፡ በእርሱም በባሕር ያለውን አዋቂነት ቅዱሣት መጽሐፍት እንዲህ ሁሉ አዋቂነቱን በፊቱም የሚሸሸግ የሌለ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

1ኛ ዜና 28÷9 "እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራል፤የነፍስንም ሀሳብ ሁሉ ያውቃል፡፡"
መዝ 139÷15-16 "አጥንቶቼ በመሠራት ላይ እንዳሉ በእናቴም ማሕፀን በጥንቃቄ በመገጣጠም ላይ እንዳሉ፤ እዚያም በስውር በማድግበት ጊዜ በዚያ መሆኔን አንተ ታውቅ ነበረ ከመወለዴ በፊት አየኸኝ ለእኔ የተወሰኑልኝ ቀኖቼ ገና ከመጀመራቸው በፊት በመዝገብ ሠፍረዋል፡፡"
ኤር 23÷24 "ሰው በስውር ቢሸሸግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን፣ ይላል እግዚአብሔር፡፡"
ዕብ 4÷13 "ከእግዚአብሔር ፊት የሚሰወር ምንም ፍጥረት የለም ለእርሱ ፊት ሁሉ ነገር ግልጥና እርቃኑን ሆኖ የሚታይ ነው፡፡"
ኤር 17÷10 "እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ እንድመራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኩላሊትንም እፈትናለሁ፡፡"

### ፪.፰ የምዕራፉ ማጠቃለያ

- የሃይማኖት መሠረት የፈጣሪ መኖር ነው፡፡ ሃይማኖት ማለት የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም የፈጠረ እግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን ነው፡፡
- ፈጣሪ በባህርዩ በፍጥረታት የማይመረመር ቢሆንም ራሱን ግን ያለምስክር አልተወም፤ ማለትም ህልውናውን የሚያስረዱ ምስክሮችን ሰጥቷል፡፡ ከነዚህም ውስጠ ሥነ-ፍጥረት፣ የሰው ልጅ የሕሊና ምስክርነት፣ ፈጣሪ ከሰው ጋር ያደረገው ንግግርና የሰው ልጅ ሃይማኖታዊ ዝንባሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡
 እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የገለጠው ህልውናውን ብቻ ሳይሆን ባሕርይውን /ሕያውነቱን፣ ምሉዕነቱን፣ ቅዱስነቱን፣…/ እና ግብሩን /ፈጣሪነቱን፣ ከሃሊቱን፣ መጋቢነቱን፣ አዳኝነቱን፣…/ እሱነቱን በጠቅላላ የሚገልጥ ስሙንም ነው፡፡ ይህም ስም በእስራኤላውያን ቋንቋ "ያህዌ" ሲሆን በግዕዝ "እግዚአብሔር" በሚለው ተተክቷል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ሥነ-ፍጥረት

***ውድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ የፍጥረት መገኛና ባለቤት እግዚአብሔር ፍጥረታቱን የፈጠረበትን ዓላማ፣ እንዴት አድርጎ እንደ ፈጠራቸው /ፍጥረታቱን ያስገኘበት ሁኔታ/ እና መቼ እንደፈጠራቸው እንመለከታለን፡፡***

### ፫.፩ የሥነ-ፍጥረት ትርጉም

***ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች ሥነ ፍጥረት ምን ማለት ይመስላችዋል?***

***ሥነ ፍጥረት*** የሁለት ቃላት ጥምረት ነው፡፡ "ሥነ" ያለው "ሠነየ" መልካም ሆነ፣ አማረ፣ ተዋበ፣ በጀ ካለው የግዕዝ ግሰ የተወሰደ ሲሆን መልካምነት፣ መበጀት፣ ውበት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሥነ-ፍጥረት የሚለው ጣምራ ቃል በሁለት መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡፡

፩ኛ. በተናባቢ ሲፈታ የፍጥረት መበጀት፣ የፍጥረት ማማር ማለት ይሆናል

፪ኛ. በቅጽል ሲፈታ /ሥነ የሚለው ቃል ፍጥረት ለሚለው ቃል ገላጭ ሲሆን/ የበጀ ፍጥረት ያማረ ፍጥረት ማለት ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር በከሃሊነቱ፣ ወሰን ድንበር በሌለው ዕውቀቱ የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ የበጀ በየሁኔታውም ብቁ ያማረ ፍጥረት ነውና ሥነ-ፍጥረት ተብሏል፡፡ «እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆነ አየ» እንዲል፡- /ዘፍ. ፩፥፴፩/

***ውድ ተማሪዎች የፍጥረት መገኛ የሆኑት ፬ቱ ባህርያት እነማን ናቸው?***

*ሥነ-ፍጥረት ስንዐ ፍጥረት የፍጥረት መስማማት፣ የተስማማ ፍጥረት ተብሎም ይተረጎማል፡፡ ይህም የፍጥረት መገኛ የሆኑት ፬ቱ ባሕርያት /እሳት፣ ውኃ፣መሬትና ነፋስ/ የማይስማሙ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ተስማምተው ስለሚኖሩ ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለነዚህ ባሕርያት መስማማት እንዲህ ብሏል፡፡*

*«ወአስተነዓዎሙ በበይናቲሆሙ እንዘ ዘዘዚአሁ ግእዘ ጠባይዒሆሙ - የየጠባያቸው ሥራ የተለያየ ሲሆን እርስ በእርሳቸው አስማምቷቸዋል» /ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን ፪/*

**እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለምን ፈጠረ?**

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊት በቅድምና የነበረ ነው፡፡ በቅድምናም ሲኖር ፍጥረትን ከመፍጠሩ በፊት አንዳች የጎደለበት ነገር አልነበረም፡፡ በገዛ ባሕርይውም ይመሰገን ነበረ፡፡ ይህም ፍጥረትን የፈጠረው የጎደለበት ኖሮ ፍጥረት እንዲሞላለት አለመሆኑን ያስረዳል፡፡

«እምቅድመ ይፈጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ዘተጸረዐ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፤ መላእክትን ለምስጋና ከመፍጠሩም በፊት የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ምስጋናቸው የተቋረጠ አይደለም» /ቅዳሴ ዘሰለስቱ ምዕት/

በመጽሐፈ ቀሌምንጦስም እንዲህ የሚል ተጽፏል፡፡ «ይቅርታዬንና ክብሬን አሰጣቸው ዘንድ ነው እንጂ ከነሱ እጠቀም ብዬ አልፈጠርኳቸውም» /ቀሌምንጦስ/

እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ኛ.ሰውና መልእክት ስሙን እንዲቀድሱት ክብሩን እንዲወርሱት ፈጥሯቸዋል፡፡ /ኢሳ. ፵፫፥፯/፤ ኢፌ. ፪፥፲/

፪ኛ.የቀረውን ፍጥረት ለአንክሮ ለተዘክሮ /የሕልውናው መታወቂያ እንዲሆኑ/ እና ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ እንዲሆኑ ፈጥሯቸዋል፡፡ ለአንክሮ ለተዘክሮ ተፈጥረዋል ማለት ሥነ-ፍጥረትን በመመልከት፣ በመመራመር ሥራው እንዲደነቅ ህልውናው እንዲታወቅ ተፈጥረዋል ማለት ነው፡፡ ይኸውም ሸማን ስናይ ሸማኔ፣ ሸክላን ስናይ ሸክላ ሠሪ፣ ሕንፃን ስናይ ሐናጺ መኖሩን እንደምናውቅ ሁሉ በጥበብ የተፈጠረውንም ፍጥረት ስናይ ፈጣሪ እንዳላቸው ያስረዳልና ነው፡፡

«የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉና ጌትነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብና በመመርመር ይታወቃል»እንዳለ፡፡ /ሮሜ. ፩፥፳/

*ለምግበ ሥጋ ተፈጥረዋል የተባሉትም አዝዕርቱን፣ አትክልቱን፣ ፍራፍሬውን የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ለምግበ ነፍስ የተፈጠሩትም እንደ ስንዴውና፣ ወይኑ ያሉት ናቸው፡፡ የሕይወት /የነፍስ/ ምግብ ሥጋውና ደሙ ይዘጋጅባቸዋልና፡፡*

### ፫.፪ የስድስቱ ቀናት ፍጥረታት

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር የተጠቀመባቸው ዕለታት  ናቸው፡፡ እነርሱም እሁድ፣ ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ረብዕ፣ ኀሙስና አርብ ናቸው፡፡ እነዚህን ዕለታት ቀድመን መዘርዘራችን በየዕለቱ በየተራ የተፈጠሩትን ለመመልከት ያስችለን ዘንድ ነው እንጂ ዕለታቱ ከፍጥረታቱ ቀድመው ተገኝተዋል ለማለት አይደለም፡፡ ዕለታቱ በእያንዳንዳቸው ፍጥረታት ሲፈጠሩባቸው የተፈጠሩና የተገኙ ናቸው፡፡

*ውድ ተማሪዎች እግዚአብሔር በእነዚህ ዕለታት ፍጥረታትን ያስገኘው ከሁለት ወገን ነው፡፡*

፩ኛ. ካለመኖር ወደ መኖር /እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ/ በማምጣት፡- በዚሁ መልኩ የተፈጠሩት ፍጥረታት እግዚአብሔር በሥልጣኑ ቀድሞ ካልተገኘ ነገር ያስገኛቸው ናቸው፡፡

፪ኛ. ከተፈጠረው በመፍጠር /ግብር እም ግብር/፡- በዚህ መልኩ የተፈጠሩት ፍጥረታት ደግሞ አስቀድሞ ከተፈጠረ ነገር የተገኙ ናቸው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ወገኖች የፈጠራቸውን ፍጥረታት ያስገኘባቸው ደግሞ ሦስት መንገዶች አሉ

**፩. በማሰብ /በሐልዮ/**

እግዚአብሔር በዚህ መልኩ ከፍጥረታት ወገን ያስገኛቸውን የፈጠረውን በቃሉ ሳይናገር በእጁም ሳይሰራ በሕሊናው በመፍቀድ ብቻ ነው፡፡

**፪ኛ. በመናገር /በነቢብ/**

እግዚአብሔር በዚህ መንገድ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ያስገኘው ደግሞ ይሁን ብሎ በቃሉ አዝዞ ነው፡፡

**፫ኛ. በሥራ /በገቢር/**

እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በሥራ /በገቢር/ ያስገኘው አዳምን ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር በመፍጠር ስልጣኑ « ሰውን በመልካች እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ብሎ ከምድር አፈር ሠርቶታል /አበጃጅቶታል/፡፡ /ዘፍ. ፪፥፫/ ይህንንም ልበ አምላክ ዳዊት እንዲህ ገልጾታል «እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም» /መዝ. ፻፲፰፥፸፫/

## *፫.፪. ፩ ዕለተ እሑድ*

እሑድ የሚለው ስም አሐደ አንድ አደረገ ከሚል የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉምም አንድ፣ አንደኛ፣ መጀመሪያ ማለት ነው፡፡ የፍጥረት የመጀመሪያ ቀን ነውና፡፡

***ውድ ተማሪዎች የዕለተ እሑድ ፍጥረታት ስንት እና እነማን ናቸው?***

እግዚአብሔር በዚህ ዕለት ራሱን ዕለቱንና ሌሎች ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ እነዚህም ፍጥረታት፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ. እሳት | ፪ኛ. ነፋስ | ፫ኛ. ውኃ | ፬ኛ. መሬት |
| ፭ኛ. ጨለማ | ፮ኛ. ሰባቱ ሰማያት | ፯ኛ. መላእክት | ፰ኛ.ብርሃን ናቸው፡፡ |

እግዚአብሔር ፍጥረታቱን ያስገኘበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነው፡፡

*በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት /ከሌሊቱ ፩ ሰዓት/፡-*
በዚህ ሰዓት አራቱ ባሕርያት የተባሉት (መሬት፣ ውኃ፣ እሳት፣ ነፋስ) እና ጨለማን እምኀበ አልቦ /ካለመኖር/ አምጥቶ በሐልዮ በመፍቀድ ብቻ ፈጥሯቸዋል፡፡

❖ የአራቱ ባህርያት ምሳሌነታቸው

እግዚአብሔር ለፍጥረታት ከሚሰጡት ጥቅም፣ ለአንክሮ ለተዘክሮ ከመፈጠራቸውም ባሻገር በባሕርዩ አራት ነገሮች አሉ ሲል አስቀድሞ አራቱን ባሕርያት ፈጥሯቸዋል፡፡ ይኸውም፡-

1. በባሕርዩ ኃያል ነኝ ሲል ፡- እሳትን ፈጠረ

- እሳት፡- ኃያል ነው ውኃ ካልከለከለው ደረቁንም እርጥቡንም ልብላ (ላጥፋ ) ቢል ይቻለዋል፡፡
- ጌታም ፡- እንዲሁ ከሀሊነቱ፣ ምሕረቱ ካልከለከለው በቀር ትልቁንም ትንሹንም ፣ ክፉውንም መልካሙንም አንድ ጊዜ ላጥፋ ቢል ይቻለዋል፡፡ ስለዚህኃያልነቱ በእሳት ይመሰላል፡፡

መዝ 7÷11- 12 ፡- እግዚአብሔር እውነተኛ ዳኛ ነው ኃይለኛም ታጋሽም ነው ሁል ጊዜም አይቆጣም» እንዲል፡፡

2. ፈታሒ (እውነተኛ ፈራጅ ) ነኝ ሲል ነፋስን ፈጠረ

- ነፋስ ፡- ፈታሒ ነው ገለባን ከፍሬ ፣ፍሬን ከገለባ ይለያል እንደዚሁም
- ጌታም ፡- ጻድቃንን ከኃጥአን ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያልና እውነተኛ ዳኝነቱ በነፋስ ይመሰላል፡፡

- መዝ 7÷11፣ መዝ 9÷16 «የአምር እግዚአብሔር ገቢረ ፍትሕ / እግዚአብሔር ፍርድን በማድረግ የታወቀ ነው » እንዲል፡፡
- ሉቃ 3÷17 ፡- «መንሹም በእጁ ነው አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል ስንዴውንም በጎተራው ይከታል ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል»

- ማቴ 25÷32 ፡- «እረኛ በጎቹን ከፍየል እንደሚለይ አርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል፡፡ በጎችን በቀኝ ፍየሎችን በግራ ያቆማቸዋል፡፡» እንዲል፡፡

3. ርጎሩን ነኝ ሲል አንድም መንጽሒ (የማነጻ) ነኝ ሲል ውኃን ፈጠረ

   - ውኃ ፡- መንጽሒ (የሚያነጻ) ነው፤ ያደፈውን የሚያነጻ የቆሸሸውን የሚያጠራ ነው፡፡

- ጌታም ፡- ኃጢያተኛ ኃጢአቱን አምኖ ማረኝ ብሎ ቢቀርበኝ ከኃጢያቱ አነጻዋለሁ ሲል ውኃን ፈጥሮታል፡፡

- ቅዱስ ዳዊት፡-መዝ 50÷1 « እንደ ቸርነትኅ መጠን ማረኝ እንደ ምህረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ ከበደሌም ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢያቴም አንጻኝ »
- በት/ሕቡአትም « ወኃበነ ማየ መንጽሔ ዚአነ / ሀብተ ንጽህ ሀብተ ሕይወት የሚሆን ሚያድን የጥምቀት ውኃን አደለን » በማየ ጥምቀት ከኃቲአት አዳነን፡፡ ት/ኅቡ/አልመስጦጊያ ምዕ 2÷ 7

4. ባለጠጋ ነኝ ሲል መሬትን ፈጠረ
   - መሬት ፡- ሁሉ ነግር ይገኙበታል ለፍጡራን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ታስገኛለች
     - መዝ 64፤9 ፡- « ምድርን ጎበኘሃት አጠጣሃትም ብልጥግናዋንም እጅግ አበዛህ»
   - ጌታም ፡- በባሕርየ ብሰጥ የማይጎድልብኝ ባለጸጋ ነኝ ሲል ምሳሌ ትሆነው ዘንድ መሬትን ፈጠረ፡፡
     - በመዝ 84፤12 «እግዚአብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች» እንዲል አንድም፡-
   - ምድር ፡- ከሀሊ (ሁሉን ቻይ ናት) ናት ፈጣሪዋ እግዚአብሔር በሰጣት ፀጋ ጌታ የፈጠረውን ፍጥርት ሁሉ ችላ ትኖራለች ፡፡ እነደዚሁም፡-
   - ጌታም ፡- ሁሉን ችሎ ሁሉን ታግሶ ፀጋውን ለፍጥረቱ ሰጥቶ ይኖራል

ለምሳሌ ፡- ኃጥኡን ከጻድቁ ፤አማኒውን ከኢአማኒው ሳይለይ ሁሉን ችሎ ታግሶ ብርሃኑን እያበራ ፤ዝናሙን እያዘነበ በመግቦቱ እየመገበ ያኖረዋል፡፡በፍርድ ቀን ግን ለሁሉ እንደየስራው ይሰጠዋል እስከዛው ግን በከኃሊነቱ ይታገሳል በዚህም ከኃሊ ነኝ ሲል መሬት ፈጠረ፡፡

- ❖ እግዚአብሔር አራቱን ባሕርያት ሲፈጥር ሦስት ሦስት ጠባይ (ግብር) እንዲኖራቸው አድርጎ ነው፡፡ይኸውም በባሕርዩ አንድነት ሦስትነት እንዳለ እወቁ ሲል ነው፡፡

  - የእሳት ግብሩ ( ጠባዩ) ፡- ማቃጠል፣ ብሩህነት፣ደረቅነት ነው፡፡
  - የነፋስ ግብሩ (ጠባዩ)  ፡- አርጥብነት ፤ማቃጠል እና ጨለማነት  ነው፡፡
  - የወኃ ግብሩ  ( ጠባዩ) ፡- ብሩህነት ፤እርጥብነት እና ቀዝቃዛነት ነው፡፡
  - የመሬት ግብሩ (ጠባዩ) ፡- ደረቅነት ፤ቀዝቃዛነት እና ጨለማነት ነው፡፡

## *ከሌሊቱ ፩ ሰዓት እስከ ሌሊቱ ፱ ሰዓት*

በነዚህ ሰዓታት ከእሳት ዋዕዩን /ማቃጠሉን፤ሙቀቱን/ ትቶ ብርሃኑን ነስቶ /ወስዶ/ ሰባቱ ሰማያትን ፈጥሯል፡፡ የሰባቱ ሰማያት አፈጣጠርም እንደሚከተለው ነው፡፡

፩ኛ. ከሌሊቱ ፪ ሰዓት **መንበረ መንግሥትን** ፈጠረ፡፡ ከጽርሐ አርያም በታች ከሰማይ ውዱድ በላይ የምትገኛ ናት፡፡ መጠኗ የምንኖርባት ዓለም የሚያህል፣ ከዳር እስከ ዳር የማይደርስ፣ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያላት ናት፡፡ በዚህች ሰማይ እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ በወደደው መልክ ይገለጥላቸዋል፡፡ /ኢሳ. ፮÷፩፤ ሕዝ. ፩÷፳፮፤ ራዕ. ፬÷፪/

፪ኛ. ከሌሊቱ ፫ ሰዓት **ጽርሐ አርያምን** ፈጠረ፡፡ ይህች ሰማይ ከሰማያት ሁሉ በላይ ናት፡፡ መጠኗም ይህን ያህላል፣ ድንበሯም እስከዚህ ድረስ ነው ብሎ ከፍጥረታት ወገን የሚያውቃት የለም፡፡

፫ኛ. ከሌሊቱ ፬ ሰዓት **ሰማይ ውዱድን** ፈጠረ፡፡ ይህች ሰማይ ኪሩቤል የሚሸከማት ለመንበረ መንግሥት እንደ አዳራሽ ወለል የሆነችና መንበረ መንግሥት እንደ ዙፋን የተዘረጋባት ናት፡፡

፬ኛ. ከሌሊቱ ፭ ሰዓት **ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን** ፈጠረ፡፡ ሌላው ስሟ መንግስተ ሰማያት ነው፡፡ ቀዳም ሳጥናኤል የተፈጠረባት፣ ከዶ ቢወጣ ለምዕመናን የተሰጠች ናት፡፡ በመካከሏ የእመቤታችን ምሳሌ የሆነ የብርሃን ታቦት /ታቦት ዘዶር/ ይገኝባታል፡፡ /ራዕ. ፲፩÷፲፱/

፭ኛ. ከሌሊቱ ፮ ሰዓት **ኢዮርን** ፈጠረ፡፡

፮ኛ. ከሌሊቱ ፯ ሰዓት **ራማን** ፈጠረ፡፡

፯ኛ. ከሌሊቱ ፫ ሰዓት **ኤረርን** ፈጠረ፡፡

ውድ ተማሪዎች ኢዮር፣ ራማና ኤረር ዓለመ መላእክት /የመላእክት ከተሞች/ ተብለው ይጠራሉ፡፡ ምክንያቱም መላእክት በየነገዳቸው የሰፈሩባቸው ቦታ ናቸው፡፡

***ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች የመላእክት ተፈጥሮ እንዴት ይመሰላችዋል?***

### *ከሌሊቱ ፱ ሰዓት እስከ ፲፪ ሰዓት*

በነዚህ ሰዓታት እግዚአብሔር መላእክትን በችሎታው ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጥሯል፡፡ በአንዳንድ መጻሕፍት /መዝ. ፻፫፥፬፤ መቃ. ፲፫፥፲፩፤ ድርሳነ ሚካኤል ዘኅዳር/ ቅዱሳን መላእክት ከእሳትና ከነፋስ ተፈጥረዋል ተብሎ መጠቀሱ መላእክት እሳትና ነፋስን በግብር መምሰላቸውን ለማመልከት ነው፡፡ ይህም ማለት እሳት ረቂቅ ነው፣ መላእክትም ረቂቃን ናቸው፣ ነፋስ ፈጣን ነው መላእክትም ለተልእኮ ፈጣን ናቸው ለማለት ነው፡፡

« ሶበስ ተፈጥሩ እምነፋስ ወነድ እሞቱ ወእማሰኑ ከማነ - ከነፋስና ከእሳትስ ተፈጥረው ቢሆን እንደ እኛ ታማሚ ሟች በሆኑ ነበረ »እንዲል፡፡ /አክሲማሮስ/

*የተፈጠሩ መላእክት መቶ ነገድ ናቸው፡፡ አፈጣጠራቸውም እንደሚከተለው ነው፡፡*

፩ኛ. ከሌሊቱ ፱ ሰዓት በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል፡፡

፪ኛ. ከሌሊቱ ፲ ሰዓት በኢዮር ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል፡፡

፫ኛ. ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት በራማ ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል፡፡

፬ኛ. ከሌሊቱ ፲፪ ሰዓት በኤረር ያሉትን መላእክት ፈጥሯቸዋል፡፡

*ኢዮር ከላይ ወደታች አራት ከተማ ሲኖራት በእያንዳንዱ አስር አስር ነገደ መላእክትን* አስፍሮበታል፡፡

- በመጀመሪያው ከተማ ያሉትን አስሩን ነገድ ***አጋዕዝት*** ብሎ ሰየማቸው ሳጥናኤልን በእነሱ ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው፡፡
- በሁለተኛው ከተማ ያሉትን ኪሩቤል ብሎ በየሰማቸው **ኪሩብን** አለቃቸው አደረገው፡፡
- በሶስተኛው ከተማ ያሉትን ሱራፌል ብሎ ሰየማቸው **ሱራፌን** አለቃቸው አደረገው
- በአራተኛው ከተማ ያሉትን ኃይላት አላቸው **ሚካኤልን** አለቃቸው አደረገው፡፡

*ራማ ከላይ ወደታች ሶስት ከተማ ሲኖራት በእያንዳቸው አስር አስር ነገደ መላእክት አስፍሮበታ፡፡*

- በራማ በላይኛው (በመጀመሪያዋ) ከተማ ያሉትን አርባብ ብሎ ስየማቸው **ገብርኤልን** አለቃ አድርጎ ሾመላቸው፡፡
- በሁለተኛው ከተማ ያሉትን መናብርት ብሎ ሰየማቸው፡፡ **ሩፋኤልን** አለቃቸው አድርጎ ሾመላቸው፡፡
- በሶስተኛው ከተማ ያሉትን ስልጣናት ብሎ ሰየማቸው፡፡ **ሱርያልን** አለቃቸው አድርጎ ሾመላቸው፡፡

ኤረርንም እንደ ራማ በሶስት ከተማ ከፍሏት በእያንዳንዱ ከተማ አስር አስር ነገድ አስፍሮባታል፡፡

- በኤረር በመጀመሪያዋ ከተማ ያሰፈራቸውን **መኳንንት** በሁለተኛዋ ከተማ ያሉትን **ሊቃናት** በሶስተኛዋ ከተማ ያሉትን **መላእክት** ብሎ ሰይሟቸዋል፡፡ ለመኳንንት **ስዳካኤልን** ለሊቃናት **ሰላታኤላን** ለመላእክት **እናንኤልን** አለቃ አድረጎ ሾሞላቸዋል፡፡

ውድ ተማሪዎች የነገደ መላእክትን ስም አስፋፈራቸውንና የአለቃቸውን ስም በሰንጠረዥ ፩ ተመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ ፩፡- የነገደ መላእክት ስም ፣የነገድ አለቆች ስምና የመላእክት አሠፋፈር

| **የሰማዩ ስም** | **የአሥሩ ነገድ ስም** | **የአለቃቸው ስም** |
|---|---|---|
| **ኢዮር** | አጋዕዝት | ሳጥናኤል |
| | ኪሩቤል | ኪሩብ |
| | ሱራፌል | ሱራፌል |
| | ኃያላት | ሚካኤል |
| ***ራማ*** | አርባብ | ገብርኤል |

| | | |
|---|---|---|
| | መናብርት | ሩፋኤል |
| | ሥልጣናት | ሱርያል |
| **ኤረር** | መኳንንት | ሰዳካኤል |
| | ሊቃናት | ሰላታኤል |
| | መላእክት | አንንኤል |

## *እሑድ ቀዳማይ ሰዓተ መዓልት (እሑድ ከንጋቱ ፩ ሰዓት)*

እግዚአብሔር አምላክ ቅዱሳን መላእክትን ከፈጠራቸው በኃላ በባሕርዩ ረቂቅ ነውና አብሯቸው ሳለ ተሰወረባቸው፡፡ ይህም መላእክቱ ከእግዚአብሔር በአገኙት እውቀት ተመራምረው እርሱን ፈጣሪያቸውን እንዲያውቁ ነው፡፡ ከዚህ በኃላ መላእክት "ማን ፈጠረን?" "ከወዴት መጣን?" እያሉ መመራመር ጀመሩ፡፡ ሳጥናኤልም ከሁሉም የበላይ ሆኖ ተፈጥሯልና ከወደታች መላእክት ይህን ሲነጋገሩ ቢሰማ ከወደ ላይ ግን ድምፅን ቢያጣ "እኔ ፈጠርኳችሁ" ብሎ ሐሰትን ከራሱ አመንጭቶ ተናገረ፡፡ በዚህ ሰዓት በመላእክት ዘንድ ታላቅ ሽብር ሆነ፡፡ ከዲያብሎስ የሐሰት ልቦና መንጭታ የወጣች ይህች የአመጽ ንግግር በአለቅነት የተሾመላቸው ፲ሩን ነገድ በሶስት ወገን ከፋፈላቸው፡፡ (ሄኖክ ፲፩÷፫፤ ዮሐ ፰)

፩ኛ. አዎን ሳጥናኤል ፈጥሮናል ያሉ አንድ ወገን

፪ኛ. ፈጥሮን ይሆን ወይስ አልፈጠረን ይሆን እያሉ የተጠራጠሩ ሁለተኛ ወገን

፫ኛ. ከዚያም ከዚህም ሳይሆኑ እንዲሁ ፈዘው የቀሩ ሶስተኛ ወገን

የቀሩት ፺ቱ ነገድ ከነገደ ሚካኤል ተጨምረው እርሱ በቦታ በበላይነት ስለሆነ ፈጠረን ካለ እኛም የበታቾቻችንን ፈጠርናችሁ እንባልን? ይህስ አይሆንም አሉ፡፡ በዚህ ሰዓት መላእክ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል "ንቁም በበህላዌነ እስከ ነአምር ፈጣሪነ-ፈጣሪያችንን እስከምናውቅ ድረስ በያለንበት ጸንተን እንቁም " ብሎ መላእክቱን አረጋጋቸው፡፡

ሳጥናኤልንም ፈጠርኳችሁ ካልከን ፈጥረህ አሳየን አሉት፡፡ መፍጠር ተሳነው፡፡ በዚህ ጊዜ መላእክቱን ፈጽሞ እንዳያስታቸው ብሎ እሑድ በነግህ (ጠዋት ፩ ሰዓት) " ለይኩን ብርሃን - ብርሃን ይሁን" ብሎ ብርሃንን ፈጠረ፡፡ ብርሃኑን መዓልት ጨለማውን ሌሊት ብሎ ጠራው (ዘፍ ፩÷፭)። መላእክትም ብርሃኑ ዕውቀት ሆኗቸው "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ እግዚአብሔር ምስጋናህ በሰማይና በምድር የመላ ነው" ብለው አመስግነውታል፡፡ ዲያብሎስና ያመኑበት መላእክት ግን ከክብራቸው ተዋርደዋል፣ ወደ ጥልቁም ተጥለዋል (ኢሳ ፲፬÷፲፪-፲፯)

## *እሑድ ከጠዋቱ ፪ ሰዓት*

በዚህ ሰዓት መንፈስ ቅድስ አንዱን ክንፉን ወደ ላይ አንዱን ክንፉን ወደታች አድርጎ ለመላእክት ታያቸው፡፡ «ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብለው ምስጢረ ሥላሴን አምልተው አስድተው ተናገሩ፣ ሃይማኖታቸውንም አጸኑ፡፡»

## *እሑድ ከቀኑ ፫ ሰዓት እስከ ቀኑ ፲፪ ሰዓት*

በነዚህ ሰዓታት ቅዱሳን መላእክትን በየነገዳቸው ከአጋዕዝት ጀምሮ እስከ መላእክት ያሉትን ቀባቸው፣ ማለትም አእምሮን፣ የማያቋርጥ ምስጋናን ሰጣቸው፤ ሕማም ሞት ድካም እረፍት የሌለባቸው አደረጋቸው፡፡

## ፫.፪. ፪ ዕለተ ሰኑይ (ሰኞ ዕለት)

> ሰኑይ ሰነየ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ሁለት መሆንን ፣ ሁለት ማድረግን ያመለክታል፡፡ሰኑይ (ሰኞ)ሁለተኛ ዕለት ማለት ነው፡፡

በዚህ ዕለት እግዚአብሔር ራሱን ዕለቱንና ጠፈርን ፈጥሮአል፡፡ ጠፈርን የፈጠረ በመጀመሪያው ሰዓት ሌሊት (ከሌሊቱ በ ፩ ሰዓት) ነው፡፡ ጠፈር ከመፈጠሩ በፊት በዕለተ እሑድ የተፈጠረው ውኃ ከምድር እስከ ኤረር መልቶ አድሮ ነበረ፡፡ ያንን ውኃ ከ፫ ወገን ከፍሎታል፡፡

፩ኛ. አንዱን እጅ በዚህ ዓለም አስፍሮታል
፪ኛ. ሁለተኛውን እጅ ከላይ አሳፍሮታል፡፡ ይህም ውኃ ሐኖስ ይባላል፡፡
፫ኛ. ሦስተኛውን እጅ "ለይኩን ጠፈር ማዕከለ ማይ ወማይ- በውኃና በውኃ መካከል ጠፈር ይሁን" ብሎ በመካከል አጽንቶታል፡፡

«በሁለተኛይቱም ቀን በሐኖስና በውቅያኖስ መካከል ጠፈርን አድርጓልና፡፡ በዚያችም ቀን ውኃዎች ተከፋፍለው እኩሌቶቹ ወደ ላይ ወጥተዋልና፣ እኩሌቶቹ ከጠፈር በታች ወደአለው ወደ ምድር መካከል ወርደዋና፣ በሁለተኛው ቀን ይህን ስራ ብቻ ሠራ» እንዲል (ኩፋ ፪÷፱)

❖ የሰኞ ፍጥረት ምሳሌ

ከላይ የሚገኙት ሁለቱ እጅ የውኃ ክፍሎች በላይ ተወስነው መኖራቸው እና አንዱ አጅ በዚህ ምድር መስፈሩ ምሳሌነቱ የሶስቱ አካላት የአብ፣የወልድ ፣ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነውይኸውም:-

- ከላይ የቀረው ሁለቱ እጅ ውኃ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሲሆን በዚህች ምድር የሰፈረው ደግሞ የወልድ ምሳሌ ነው፡፡ አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋ ለብሰው በዚች ምድር አልተመላለሱም ፤ ወልድ ግን የሰውን ልጅ ለማዳን በመወለድ ግብሩ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ለሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ለመመላለሱ ምሳሌ ነው፡፡

### ፫-፪-፫ ዕለተ ሠሉስ (ማክሰኞ ዕለት)

ሠሉስ ሠለሰ ሦስት አደረገ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ሦስተኛ ማለት ነው፡፡

*ውድ ተማሪዎች የዕለተ ሠሉስ(ማክሰኞ) ፍጥረታት እነማን ናቸው?*

በዚህም ዕለትም እግዚአብሔር ራሱን ዕለቱንና ፫ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ (ዘፍ፩÷፩፪) እነዚህም፡-

፩ኛ. በመጥረቢያ የሚቆረጡ ዕፀዋትን /ዛፎችን…/
፪ኛ. በማጭድ የሚታጨዱ አትክልትን /ሣር መሰል ነገሮችን…../
፫ኛ. በጣት የሚለቀሙ አትክልትን /ፍራፍሬዎችን…./

ከላይ የተጠቀሱትን ፍጥረታት እግዚአብሔር በዚህ ዕለት ከመፍጠሩ በፊት አስቀድሞ የተፈጠሩትን እንደሚከተለው አደላድሏል፡፡

፩ኛ. ከሰኞ እስከ ማክሰኞ ከጠፈር በታች ምድርና ውኃ ተቀላቅለው ነበረ፡፡ ምድር ላይ የቀረውን አንድ እጅ ውኃ ለሦስት ከፍሎ አንዱን እጅ መሬት በታች አደረገው፤ ሁለተኛውን ደግሞ መሬትን አጎድጉዶ ውቅያኖስ አደረገው፡፡

፪ኛ. በዚህ ዕለት ከላይ ካየነው በተጨማሪ አምስቱ ዓለማተ መሬትን አደላድሏል፡፡ (ስለ አምስቱ ዓለማተ መሬት በገጽ 21 ላይ ይመልከቱ)

❖ የማክሰኞ ፍጥረት ምሳሌነታቸው

ቅዱስ ኤፍሬም በውደሴ ማርያም ምስጋናው « አንቲ ውዕቱ ገራህት ዘኢተዘራ ዘር ውስቴታ ዘር ወጻ እምኔኪ ፍሬ ሕይወት / አንቺ ዘር ያልተዘራብሽ እረኛ ነሽ ካንቺ የሕይወት ፍሬ ወጥቶብሻልና » በማለት እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን እንዳመሰገናት ፡-

- ዘር ሳይዘራባት ፣ሳትታረስ፣ ፍሬ የሰገኘችው ምድር ፡- በእመቤታችን ትመሰላለች፤ ይኸውም እመቤታችን የለሩካቤ (ያለ ወንድ ዘር) እውነተኛ የሕይወት ፍሬ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የማስገኘቷ ምሳሌ ነው፡፡
- እግዚአብሔር እነዚህን የማክሰኞ ፍጥረታት በሦስቱ ዓለማተ መሬት ማለትም፡- በምንኖርባት ምደር፣ በገነት እና በብሔረ ብፁአን አስገኝቷቸዋል፡፡

### ፫.፪. ፬ ዕለተ ረቡዕ (ረቡዕ ዕለት)

ረቡዕ ማለት አራተኛውን ዕለት የሚያመለክት ነው፡፡ በግዕዝ ራብዕ ማለት ነውና፡፡

በዚህ ዕለት እግዚአብሔር ራሱ ዕለቱን እንዲሁም በመጀመሪያው ሰዓት ሌሊት ቀኑንና ሌሊቱን ይለዩ ዘንድ ፫ ብርሃናትን በሰማይ ጠፈር ላይ ፈጥሯል፡፡ (ዘፍ ፩÷፲፬) እነርሱም ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ናቸው፡፡

የፀሐይ ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ ነው፡፡ ጨረቃና ከዋክብትን ግን ከነፋስና ከውኃ አርግቶ ፈጥሯቸዋል፡፡ ከዚህ በኃላ «ለይኩን ብርሃን» ብሎ ከፈጠረው አንደኛው ብርሃን የስንዴን ቅንጣት ያህል አምጥቶ ያንን ከ7 እጅ ከፍሎ 6ቱን እጅ ለፀሐይ አደረገ፡፡ የቀረውን አንዱን እጅ እንደገና ከ7 ከፍሎ 6ቱን እጅ ለጨረቃ አደረገ፡፡ ቀሪውን አንድ እጅ ከዋክብትን እንደየ መጠናቸው ቅብቷቸዋል፡፡ ከዋክብትንም በብርሃን ሲቀባ አላልቅ ብለው ነበር፡፡ "ኮከብ ከኮከብ ይበልጣልና " እንዲል፡፡ (፩ ቆሮ ፩□)

❖ የረቡዕ ስነፍጥረት ምሳሌነታቸው

1. በ፤ኛ ቆሮ 15፣40 «የፀሀይ ክብር አንድ ነው ፤የጨረቃም ክብር ሌላ ነው፤የካክብትም ክብር ሌላ ነው፡፡አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያያልና» እንዲል የረቡዕ ፍጥረታት በክብር መበላለጣቸው ምሳሌነቱ የአንዱ ቅዱስ ክብር ከአንዱ ቅዱስ ክብር የመበላለጡ ምሳሌ ነው፡፡
   - ጌታ በወንጌል« … አንዱ መቶ አንዱ ሥልሳ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ፡፡» ብሎ እንዳስተማረ
   - ፀሐይ፡- የባለ መቶ
   - ጨረቃ፡- የባለ ስልሳ
   - ከዋክብት፡- የባለ ሠላሳ የሃይማኖት እና ምግባር ፍሬ የሚያፈሩ የቅዱሳን ምሳሌዎች ናቸው፡፡
2. አንድም ፀሀይ በምሳሌነቷ ለጻድቃንም ለሀጥአንም ምሳሌ ሆና ትነገራለች ይኸውም፡-
   - ፀሀይ የጻድቃን ምሳሌ ናት ሲባል ፡- ፀሀይ ሁል ጊዜ ሙሉ እንደሆነች ጻድቃንምምግባር እና በሀይማኖት ምሉአን ናቸውና በፀሀይ ይመሰላሉ፡፡
   - ፀሀይ የኃጥአን ምሳሌ ናት ፡- በዋዕይነቱ ፀንታ እንድትኖር ኃጥአንም በኃጢአታቸው ፀንተው የመኖራቻ ምሳሌ ነው፡፡ እንድም ፀሀይ ብርሃኗን ሳትለውጥ በምልአት እንደምትኖር ሁሉ ኃጥአንም በኃጢአት በክህደት ምሉዐን የመሆናቸወ ምሳሌ ናት፡፡
3. አንድም፡-ጨረቃ የጻድቃንም የኃጥአን ምሳሌ ሆና ትነገራለች
   - ጨረቃ የጻድቃነ ምሳሌ ናት ሲባል፡- ጨረቃ ከብርሃኗ እንድ ጊዜ ስትጎድል አንድ ጊዜ ስትሞላ እንደምትኖር ፃድቃንም አንድ በሃጢያት ሲሰናከሉ በንስሃ እየሞሉ የመኖራቸው ምሳሌ ናት፡፡

➢ ጨረቃ በሃጥአን መመሰሏ፡- ጨረቃ በመጠኗ እያነሰች እንደምትሄድ ኃጥአንም ከእውቀትና ከምግባር እያነሱ የሚሄዳቸው ምሳሌ ነው፡፡

### ፫.፪. ፭ ዕለተ ሐሙስ (ሐሙስ ዕለት)

> ሐሙስ ሐምስ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን አምስተኛ የሚል ትርጉም አለው፡፡

በዚህ ዕለተ ራሱን ዕለቱንና ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ፍጥረታት እንድታስገኝ ትአዛዝ በመስጠት በደመ ነፍስ ሕይወት ሕያዋን የሆኑ ፫ ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ እነዚህም፡-

፩ኛ. በልብ የሚሳቡ (ምሳሌ፡- ዓሣ አንበሪ)
፪ኛ. በእግር የሚሽከረከሩ(ምሳሌ፡- ዳክዬ)
፫ኛ. በክንፍ የሚበሩ (ምሳሌ፡- ዓሣ አውጭ) ናቸው፡፡

❖ የሐሙስ ስነፍጥረት ምሳሌነታቸው

ለሚስጥረ ጥምቀት ነው
ባህር ፡- የጥምቀት 1ኛ ቆሮ10÷2 ከባሕር ውስጥ የተገኙት ፍጥረታት የሰዎች ምሳሌ ሲሆኑ
ከባህር ወጥተው በየብስ የቀሩት የኢ-ጥሙቃን (ያልተጠመቁ) ሰዎች ፣
በባህር ውስጥ የቀሩት የጥሙቃን (የተጠመቁ) ሰዎች
አንዴ ከውኃ አንዴ ከየብስ የሚመላለሱ ደግሞ አንዴ ወደ ክርስትና አንዴ ወደ ኑፋቄ የሚወላውሉ ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡

### ፫.፪. ፮ ዕለተ ዓርብ (ዓርብ ዕለት)

> ዓርብ ዓረብ ካለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መካተቻ ማለት ነው፡፡ ይህም ዕለቱ የፍጥረት መካተቻ ፣ ማብቂያ/መፈጸሚያ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በዚህም ዕለት እግዚአብሔር ራሱን ዕለቱንና በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ከደረቅ ምድር በደመ ነፍስ ሕይወት ሕያዋን የሆኑ እንደ ሐሙስ ያሉ ፫ ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ እነዚህም፡-

፩ኛ. ሣር ነጭተው ውኃ ተጎንጭተው የሚኖሩ እንስሳት
፪ኛ. ሥጋ ቦጭቀው ደም ተጎንጭተው የሚኖሩ አራዊት እና
፫ኛ. ፍሬ ለቅመው ውኃ ጠጥተው የሚኖሩ አዕዋፍ ናቸው፡፡

❖ የዓርብ ሦስቱ ስነፍጥረታት ምሳሌነታቸው

ለ ትንሳኤ ሙታን ነው

እነዚህ ፍጥረታት የትንሳኤ ሙታን ምሳሌዎች ናቸው ፡፡ይኸውም እነዚህ ፍጥረታት መሬት ሁነው ሳለ እግዚአብሔር እንዲነሱ ሲያዝ ከመሬት ተነስተው ደመነፍስ ያላቸው ተንቀሳቃሽ እንደሚሆኑ ሁሉ በእለተ ምጽአትም እግዚአብሔር ሲያዝ ትብያ የነበሩ፣ አፈር ሁነው የነበሩ የሰው ልጆች ሕይወት ተዘርቶባቸው የመነሳታቸው (የትንሳኤ ሙታን) ምሳሌ ነው፡፡

በዕለተ ሐሙስና በዕለተ ዓርብ የተፈጠሩ ፍጥረታት «እንሰሳት» በመባል አንድ ቢሆኑም በአኗኗራቸው ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ የሐሙስ ፍጥረታት በየብስ የአርብ ፍጥረታት በውኃ መኖር አይሆንላቸውምና፡፡

***ውድ ተማሪዎች በዕለተ ዓርብ በመጨረሻ የተፈጠረው ማን ነው? አፈጣጠሩስ እንዴት ነው?***

በዚሁ ዕለት በነግህ እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» ብሎ 4ቱን ባሕርያተ ሥጋ 5ኛ ባሕርዩ ነፍስን አዋህዶ አዳምን ፈጥሮታል፡፡(ዘፍ ፩÷፳□) ከፈጠረውም በኃላ የሕይወት እስትንፋስን እፍ ብሎበታል፡፡ በዚህም ሰውን ከሌሎች በደመ-ነፍስ ሕያዋን ሆነው ከሚኖሩብ እንሰሳት ለይቶ ክብርን ልጅነትን ሰጥቶ ለዘለዓለም ሕያው ፍጥረት አድርጎታል፡፡ (ዘፍ ፪÷፯)

እግዚአብሔር እስከ 6ኛው ዕለት የፈጠራቸው ፍጥረታት ፳፪ ናቸው፡፡ ብዙውን አንድ እያለን ብንቆጥር፡፡ እነዚህን ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ በ7ኛው ቀን አረፈ፡፡ (ዘፍ ፪÷፪፣ ኩፉ ፫÷፪-፫) አረፈ ማለት ደክሞት አረፈ ማለት ሳይሆን መፍጠሩን ተወ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኃላ አዳም በተፈጠረ በ፫ተኛው ቀን በሁለተኛው ዓርብ ረዳት የምትሆን ሔዋንን ፈጠረለት፡፡ (ዘፍ ፪÷፲፰)

### ፫.፫ ሃያው ዓለማት

እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ብዙውን አንድ እያለን ብንቆጥር ፳፪ ሥነ-ፍጥረት እንዳለ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ (እሳት፣ ውኃ፣ መሬት፣ ነፋስ) ፳ ዓለማትን ፈጥሯል፡፡ ፈጥሯል ስንልም አደላድሏል፣ አከናውኗል ማለት እንጂ ሌላ አዲስ ፍጥረትን አስገኝቷል ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ ሃያው ዓለማት ከ ፳፪ቱ ሥነ-ፍጥረት ውስጥ ተካተው የሚቆጠሩ ናቸው እንጂ ከ፳፪ቱ ሥነ-ፍጥረት ውጭ ሌላ ፍጥረታት አይደሉም፡፡ ሃያው ዓለማት የተፈጠሩት ከእሑድ እስከ ማክሰኞ ነው፡፡ ሃያው ዓለማት የሚባሉት ዝርዝረዘቸው በሠንጠረዥ ፪ ተመልክቷል፡፡

***ሠንጠረዥ ፪፡-የሃያው ዓለማት***

| ተ.ቁ | የዓለማቱ ስም | ብዛት |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | ዓለማተ እሳት | ፱ |
| ፪ | ዓለማተ ነፋስ | ፪ |
| ፫ | ዓለማተ ማይ | ፬ |
| ፬ | ዓለማተ መሬት | ፰ |
| ጠቅላላ ድምር | | ፳፫ |

## ፩ኛ. ዓለማተ እሳት

ዓለማተ እሳት የተፈጠሩት ከእሳት ግብር፣ ጠባይ (ብሩህነት፣ ውዑይነት፣ ይቡስነት) ነው፡፡ የተፈጠሩበት ዕለትም ዕለተ እሑድ ነው፡፡ ዓለማተ እሳት በቁጥር ዘጠኝ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- ሰባቱ ሰማያት (በገጽ 13 ላይ ተመልከት)
- ምጽንዓተ ሰማይና
- ገሃነመ እሳት ናቸው

እግዚአብሔር ከእሳት ባሕርይ ብሩህ ብሩሁን ወስዶ ሰባቱን ሰማያትንና ምጽንዓተ ሰማይን ፈጥሯል፡፡ ምጽንዓተ ሰማይ (የሰማይ መጽኛ ወይ መሠረት) እግዚአብሔር ሁሉም ሰማያት እንዲጸኑበት አድርጎ የፈጠረው የእሳት ጉዛጓዝ ነው፡፡ከዚህ በኋላ የእሳቱን ዝቃጭ (ጨለማውንና ፍሙን) ወደ ታች አውርዶ ገሃነመ እሳትን ፈጥሮበታል፡፡

## ፪ኛ. ዓለማተ ነፋስ

ዓለማተ ነፋስ በነፋስ የተመሉ በነፋስ የረጉ የጸኑ ናቸው፡፡ የተፈጠሩትም በዕለተ ሰኑይ ነው፡፡ዓለማተ ነፋስ የሚባሉት ሁለት ናቸው፡፡

*ሀ*- **ባቢል፡**- ይህ የረጋ ነፋስ ከጠፈር በላይ የሚገኝ ሲሆን **ሐኖስ** ተብሎ የሚጠራውን ውኃ የሚሸከመው ነፋስ ነው፡፡
ለ- ይህንን ዓለም የሚሸከመው ነፋስ፡፡

## ፫ኛ. ዓለማተ ማይ

እነዚህ ዓለማት ከውኃ የተፈጠሩ ውኃ የመላባቸው ዓለማት ናቸው፡፡ የተፈጠሩትም በዕለተ ሰኑይና በዕለተ ሠሉስ ነው፡፡ዓለማተ ማይ የሚባሉት ፬ ናቸው፡፡

፩ኛ. **ሐኖስ፡**- ይህ ብጽብጽ ውኃ የመላበት ከኤረር በታች የሚገኝ የውኃ ዓለም ነው፡፡ ይህን የውኃ ዓለም ባቢል የሚባል ነፋስ ይሸከመዋል፡፡

፪ኛ. **ጠፈር**፡- ይህ ግግር ውኃ ነው፡፡ ጥንተ ባሕርዩን በመጠኑ ስለለቀቀ እንደ አንድ ፍጥረት ተቆጥሯል

፫ኛ. **ውቅያኖስ፡**- ይህ መሬትን የሚከባት ውኃ ነው

፬ኛ. **ከምድር በታች የሚገኝ ውኃ** ፡- ልበ አምላክ ዳዊት የምድር መሠረት ስለሆነው ስለዚህኛው የውኃ ዓለም እንዲህ ብሏል፡- "ምድርን በውኃ ላይ ያጸና" (መዝ)፻፴፭፥፮)

ከአራቱ ዓለማተ ማይ ሐኖስና ጠፈር የተፈጠሩት በዕለተ ሰኑይ ሲሆን ውቅያኖስና የምድር መሠረት የሆነው የውኃ ዓለም የተፈጠሩት ደግሞ በዕለተ ሠሉስ ነው፡፡

## ፬ኛ. ዓለማተ መሬት

እነዚህ ዓለማት ከመሬት (ከአፈር) የተፈጠሩ ናቸው፡፡ ዓለማተ መሬት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩ኛ. ***ገነት***፡- ቀድሞ ከበደል በፊት አዳምና ሔዋን የኖሩባት፤ ዛሬ በሃይማኖት ጸንተው ምግባር ሠርተው በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም የተለዩ ቅዱሳን በአካለ ነፋስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚቆዩባት የዕረፍት፣ የሕይወት፣ የታደለና የደስታ ቦታ ናት፡፡

በዚች በገነት በፍሬ የተሞላች ፍሬዋን ለቅመው የማይጨርሷት፣ መዓዛ ጣዕሟ ልብን የሚመስጥ እፀ ሕይወት፤ ከወተት ይልቅ እጅግ የምትነጣ፣ ከማር ሰባት እጅ የምትጣፍጥ ማየ ሕይወት፣ በአራቱ ማዕዘን ዞረው ገነትን የሚያመጡ 4ቱ አፍላጋት (ወንዞች) ይገኙበታል፡፡

፪ኛ. **ብሔረ ሕያዋን፡-** አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ ቅዱሳን በአካለ ሥጋ እያሉ ከዚህች ዓለም እየተነጠቁ በመሄድ የሚኖሩባት ናት፡፡ ከነዚህ ቅዱሳን ሰዎች መካከል ጻድቁ ሄኖክንና፣ ነቢዩ ኤልያስን መጥቀስ ይቻላል፡፡ (ዘፍ፭፥፳፬-፪ ነገ ፪፥፲፩)

፫ኛ. **ብሔረ ብጹዓን፡-** ይህች ዓለም ከገቢረ ኃጢያት ፍጹም የተለዩ የጽድቅ ሥራን ብቻ የሚሠሩ ብጹዓን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ የሚኖሩባት ናት፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ የብርሃን ምድር ናቸው፡፡ ከጠፈር ዝቅ ከምንኖርባት ምድር ከፍ ብለው የሚገኙ ሲሆን በዓይነ ሥጋ የማይታዩ (የተሠወሩ) ናቸው፡፡ ገነት በምሥራቅ ብሔረ ሕያዋን በሰሜን ብሔረ ብጹአን በደቡብ አቅጣጫ ይገኛሉ፡፡

፬ኛ. **የምንኖርባት መሬት፡-** ከአዳም በደል በኃላ ለሰው ልጆች መኖሪያ ሆና የተሰጠች ናት፡፡

፰ኛ. **ሲዖል**፡- የፀና ጨለማ የሞላበት፣ የሚያቃጥል እሳት ያለበት በምዕራብ አቅጣጫ ያለ ቦታ ነው፡፡ ኃጢያትን ሲሠሩ የኖሩ ሰዎች ከሞተ ስጋ በኃላ በአካለ ነፍስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እየተቀጡ የሚቆዩባት የቅጣት ቦታ ነች፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት 5ቱ ዓለማተ መሬት በብርሃን መጠን፣ በጥራትና በንጽሕና ይበላለጣሉ፡፡ ከሲኦል እኛ ያለንበት ዓለም ብሩህ ጥሩና ንጹሕ ነው፡፡ እኛ ካለንበት ዓለም ብሔረ ብጹዓን፣ ከብሔረ ብጹዓን ብሔረ ሕያዋን፣ ከብሔረ ሕይዋን ገነት ብሩህ ጥሩና ንጹሕ ነው፡፡

## ፫.፬. የምዕራፍ ማጠቃለያ

የፍጥረታት አስገኚ ልዑል እግዚአብሔር ከእሑድ እስከ ዓርብ ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ በሰባተኛው ዕለትም መፍጠሩን ፈጽሞአል፡፡ እግዚአብሔር በእነዚህ ዕለታት የፈጠራቸው ፍጥረታት በሠንጠረዥ 3 ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 3፡- የስድስቱ ዕለታት ፍጥረታት*

| የዕለት | በዕለቱ የተፈጠሩ ፍጥረታት ዝርዝር | በዕለቱ የተፈጠሩ ፍጥረታት ብዛት |
|---|---|---|
| **እሑድ** | ፩ኛ. እሳት ፬ኛ. መሬት ፯ኛ. መላእክት<br>፪ኛ. ነፋስ ፭ኛ. ጨለማ ፰ኛ. ብርሃን<br>፫ኛ. ውኃ ፮ኛ. ሰባቱ ሰማያት | ፰ |
| **ሰኞ** | ፩ኛ. ዕፅዋት / ዛፎች/<br>፪ኛ. አዝርዕት /ሣር መሰል ነገሮች/<br>፫ኛ. አትክልት /ፍራፍሬዎች/ | ፩ |
| **ረቡዕ** | ፩ኛ. ፀሐይ<br>፪ኛ. ጨረቃ<br>፫ኛ. ከዋክብት | ፫ |
| **ሐሙስ** | በውኃ ውስጥ<br>፩ኛ. በልብ የሚሳቡ<br>፪ኛ. በእግር የሚሽከረከሩ<br>፫ኛ. በክንፍ የሚበሩ እንሰሳት | ፫ |
| **ዓርብ** | ፩ኛ. እንስሳት ፫ኛ. አዕዋፍ<br>፪ኛ. አራዊት ፬ኛ. ሰው | ፬ |
| | **ድምር** | ፳፪ |

ከነዚህ ከ፳፪ ፍጥረታት መካከል ተካተው የሚቆጠሩ ሃያ ዓለማት አሉ፡፡ እነዚህ ፱ ዓለማት እሳት፣ ፪ ዓለማተ ነፍስ፣ ፬ ዓለማተ ማይና ፭ ዓለማተ መሬት ናቸው፡፡

*ሠንጠረዥ 4፡- ሃያው ዓለማት ዝርዝርና የተፈጠረባቸው ዕለታት*

| የዓለማቱ ስም | ብዛት | የዓለማቱ ዝርዝር | ዓለማቱ የተፈጠሩበት ዕለት |
|---|---|---|---|
| **ዓለማተ እሳት** | **፱** | ፩ኛ. ጽርሐ አርያም ፮ኛ. ራማ<br>፪ኛ. መናበረ መንግስት ፯ኛ. ኤረር<br>፫ኛ. ሰማይ ውዱድ ፰ኛ. ምጽንአተ ሰማይ<br>፬ኛ. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ፱ኛ. ገሃነመ እሳት<br>፭ኛ. ኢዮር | እሑድ |
| **ዓለማተ ነፍስ** | **፪** | ፩ኛ. ባቢል<br>፪ኛ. ይህን ዓለም የሚሸከመው ነፋስ | ሰኞ |
| **ዓለማተ ውኃ** | **፬** | ፩ኛ. ሐኖስ | ሰኞ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ፪ኛ. ጠፈር | |
| | | ፫ኛ. ከዋክብት<br>፬ኛ. ከምድር በታች ያለ ውኃ | ማክሰኞ |
| **ዓለማተ መሬት** | ፭ | ፩ኛ. ገነት ፬ኛ. የምኖርባት መሬት<br>፪ኛ. ብሔረ ሕያዋን ፭ኛ. ሲኦል<br>፫ኛ. ብሔረ ብጹዓን | ማክሰኞ |

# ምዕራፍ አራት

## አዕማደ ምሥጢር

*ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች ባለፉት ምዕራፎች የሃይማኖት ምንነት፣ ሀለወተ እግዚአብሔር እና ስለ ሥነ-ፍጥረት ለመመልከት ሞክረናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሃይማኖት ምሰሶዎች ስለሆኑ ስለ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን! አሜን!*

### ፬-፩ የምሥጢር ፍቺ በቤተ ክርስቲያን

ምሥጢር፡- አመሠጠረ ሠወረ ካለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ዘይቤያዊ ፍቺው ለልብ ጓደኛ ብቻ የሚነገር በሁለት ሰዎች መካከል የሚቀር ማለት ነው፡፡

ይህን ዘይቤያዊ ፍቺ ግን ቤተ ክርስቲያን ምሥጢር አትለውም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የማያውቀው በሰዎች መካከል ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነገር የለምና ነው፡፡ ሐናንያና ሰጲራ ከሰው ሁሉ ሠውረው የሠሩትን እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደገለጸለት፡፡ (ሐዋ ፭፥፩-፲)

**በቤተ-ክርስቲያን አፈታት ምሥጢር ማለት፡-**

በምርምር ጥልቀት፣ በእውቀት ብዛት ሊደርስበት የማይችል፣ በሥጋ አእምሮ ሳይሆን በመንፈስ አእምሮ የሚረዱት ረቂቅና ጥልቅ ኀቡዕ (የተሰወረ) ነገር ማለት ነው፡፡

### ፬.፪ ምሥጢር የተባሉበት ምክንያት

ምሥጢር ማለት ከዕውቀት በላይ የሆነ በእምነት ብቻ የሚረዱት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራትም ምሥጢር መባላቸው ከመምህራን ተምረው በልቦና መርምረው የሚያምኗቸው በዓይን የማይታዩ፣ በእጅ የማይጨበጡ ነገሮች የሚነገሩባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ ሰው እነዚህን ምሥጢራት የሚረዳው የማይታየውን በምታስረዳና ተስፋን በምታስረግጥ በእምነት ነው፡፡ አዋቂ ፍጥረት የሆነው የሰው ልጅ ሁሉን የመመርመርና የመረዳት ሥልጣን ከአምላኩ የተሰጠው ቢሆንም የፈጣሪውን ባሕርይውንና ግብሩን በሞላ ለመረዳት ውሱን ከሆነው አቅሙ በላይ ስለሚሆንበት በእምነት መቀበል ብቸኛ አማራጩ ነው፡፡

### ፬.፫ አዕማድ የተባሉበት ምክንያት

አዕማድ፡- የሚለው ዐምድ የሚለው የግዕዝ ቃል ብዙ ቁጥር ነው፡፡ ዐምድ ማለት ትክል፣ ምሰሶ ማለት ነው፡፡ አዕማድ ማለት ደግሞ ምሰሶዎች ማለት ይሆናል፡፡

ምሥጢራቱ ምሰሶዎች መባላቸው ምሰሶ ቤትን ደግፎ እንደሚያጸና እነዚህም ቤተ-ልቡናን ከኑፋቄ /በክህደት መውደቅ/ የሚያጸኑ ስለሆነ ነው፡፡ ምሰሶ የሌለው ቤት ይፈርሳል፤ ይወድቃል፡፡ የቀና ሃይማኖት ያልተማረ፣ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ያላወቀ ክርስቲያንም በክህደት በጥርጥር ይያዛል፣ ሃይማኖትን ባለመያዙ ምግባር ባለመሥራቱ በመንጸፈ ደይን ይወድቃልና ነው፡፡

### ፬-፬ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ዝርዝር አከፋፈል

*ውድ ተማሪዎች አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት እነማን ናቸው ዘርዝሯቸው?*

*፭ቱ አዕማደ ምሥጢራት የሚባሉት፡-*

፩. ምሥጢረ ሥላሴ
፪. ምሥጢረ ሥጋዌ
፫. ምሥጢረ ጥምቀት
፬. ምሥጢረ ቁርባን
፭. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው፡፡

ምሥጢረ ሥላሴና ሥጋዌ ነገረ መለኮት የሚነገርባቸው ምስጢራት ናቸው፡፡ ይህም የመለኮት ስሙን ግብሩን፣ ባሕርዩን እንዲሁም ምስጢረ ትስብእትን /ሰው የመሆንን ምስጢር/ የምንማርባቸው ናቸው፡፡

ምሥጢረ ጥምቀትና ምስጢረ ቁርባን የቤተ-ክርስቲያን ሀብታት ናቸው፡፡ ከ፯ቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መካከልም የሚመደቡ ናቸው፡፡

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ደግሞ ስለ ነገረ ሕይወት ማለትም ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት የምንማርበት ነው፡፡

በ፭ቱ አዕማደ ምሥጢራት ሁሉን አካቶ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ጠባይዓት፣ ስለሰው ልጅ በኃጢአት መውደቅና ዳግመኛ መዳን እንዲሁም ስለ ጽድቅና ኩነኔ መናገር ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ በ፭ቱ አዕማደ ምሥጢራት ሃይማኖትን መግለጥ የመረጠው፡፡

«...ሌሎችን አስተምር ዘንድ በቋንቋ ከሚነገር ብዙ ቃል ይልቅ በቤተ-ክርስቲያን በአእምሮዬ አምስት ቃላትን ልናገር እሻለሁ»/ቆሮ፲፬፥፱/

## ፬-፩ ምሥጢረ ሥላሴ

***ሥላሴ***፡- ሠለሰ ሦስት አደረገ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ሦስትነት፣ ሦስት መሆን የሚል ፍቺ አለው፡፡ የምሥጢርን ፍቺ በገጽ 32 ተመልከት፡፡

ምሥጢረ ሥላሴ ስንልም የአንድነትን የሦስትነትን ነገር የሚነገርበት ምሥጢር ማለት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን አብነት በማድረግ ከቅዱሳን አባቶቻችን በተላለፈልን ትምህርት መሠረት እግዚአብሔርን በአንድነት በሦስትነት እናምነዋለን፤ እናመልከዋለን፡፡

### ፬.፩.፩ የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት

እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት፣ ሦስት ሲሆን አንድ ነው፡፡

### ፬-፩-፩-፩ አንድነት በምን?

ሥላሴ በህልውና፣ እግዚአብሔር በመባል፣ በአምላክነት፣ በአገዛዝ፣ በሥልጣን፣ በመለኮት፣ በባህርይ፣ በልብ፣ በቃል በእስትንፋስ አንድ ናቸው፡፡ እነዚህንም በመሳሰሉት ሁሉ አንድ ናቸው፡፡ «እኔና አብ አንድ ነን፡፡» እንዲል፡፡/ዮሐ. ፲፥፴/

እግዚአብሔር በአንድነቱ የሚታወቅበቸው ስሞች ፈጣሪ፣ አምላክ፣ ጌታ፣ መለኮት፣ እግዚአብሔር፣ አዶናይ፣ ኤልሻዳይ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ሀ. ሥላሴ በህልውና /በአኗኗር/ አንድ ናቸው፡፡

ህልውና ማለት አንዱ በአንዱ መኖር ማለት ነው፡፡ ይኸውም በኩነታት /በሁኔታዎች/ የሚገናዘብ ረቂቅ ምሥጢር ነው፡፡ «እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምኑምን?....እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ» /ዮሐ ፲፬፥፲ እና ፲፯/

ሥላሴ በህልውና አንድ ስለሆኑ /አንዱ በአንድ ስላለ/ አብ ተጠራ ማለት አብን በተለየ አካሉ መጠቆም ቢሆንም ወልድና መንፈስ ቅዱስም በአብ ህልውና አሉ፡፡ ለወልድም ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ነው፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሥራው የሦስቱም ሆኖ ሳለ ለአንዱ አካል ሰጥቶ የሚናገረው፡፡

**ለአብ ሰጥቶ ሲናገር**

«እኔ የምነግራችሁን ይህ ቃልም ከራሴ የተናገርኩት አይደለም፤ በእኔ ያለ አብ እርሱ ይህን ሥራ ይሠራዋል እንጂ» /ዮሐ. ፲፬፥፲/

ሥራውን ለአብ ሰጥቶ መናገሩ ቅድመ ዓለም በአብ ልብነት የታሰበውን በእኔ ቃልነት እናገራለሁ ለማለት ነው፡፡ ሥራው የሦስቱም ሆኖ ሳለ ለአብ ሰጥቶ መናገሩ በአብ ህልውና ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስላሉ በአብ የሁሉንም መናገር ነው እንጂ አብ ብቻውን ይሠራል ማለት አይደለም፡፡ አብ ያለ ወልድ ምንም ሥራ እንደማይሠራ «... ሁሉም በእርሱ ሆነ፤ ከሆነውም ሁሉ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም ተብሎ ለእግዚአብሔር ወልድ ተነግሯል /ዮሐ. ፩፥፫/

**ለወልድ ሰጥቶ ሲናገር**

«እንደገና አስነሣት ዘንድ እኔ ነፍሴን እሰጣለሁና...እኔ ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ መልሼ እወስዳት ዘንድ ሥልጣን አለኝና፡፡» /ዮሐ. ፲፥፲፰/

ሥልጣን የሁሉም ሲሆን ለወልድ ሰጥቶ ይናገራል፡፡ በወልድ ህልውና አብና መንፈስ ቅዱስ ስላሉ የእነርሱንም የሥልጣን ባለቤትነት መናገር ነው፡፡ ለዚህ ነው ሥልጣኑ የአብም ሥልጣን ስለሆነ እንዲህ የተባለው፡- «እርሱ ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው» /ሐዋ. ፪፥፴፪/

**ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ሲናገር**

«ያ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ እርሱ ከራሱ አይናገርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል፡፡ እርሱ እኔን ያከብረኛል ከእኔ ወሰደ ይነግራችኋልና፡፡ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህም ከእኔ ወሰዶ ይነግራችኋል አልኋችሁ፡፡» /ዮሐ. ፲፮፥፲፫-፲፭/

መሪነት የሁሉም ሆኖ ሳለ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ይናገራል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ህልውና አብና ወልድ ስላሉ የእነርሱንም መሪነት መናገር ነው፡፡ በህልውናም አንድ ስለሆኑ "ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው" ይላል፡፡

የህልውና አንድነት በዮርዳኖስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅም ተገልጧል፡፡ ሦስቱ አካላት በዮርዳኖስ በአንድ ጊዜ ሲገኙ ህልውናቸው ደግሞ አብ በወልድ ቃልነት በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት « የምወደው ልጄ እርሱ ነው እርሱን ስሙ ብሎ» በመናገሩ ታውቋል፡፡

የሥላሴን የህልውና አንድነት በሰው ልጅ ባሕርይ ምሳሌነትም ይረዱታል፡፡ ለእኛ ለሰው ልጆች ሦስት ነገር አለን፡፡ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ፡፡ በልቦናችን አብ፣ በቃላችን ወልድ፣ በእስትንፋሳችን መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡ በልቦናችን እንደምናስብ ሥላሴም በአብ ልቦናነት ያስባሉ፤ በቃላችን ቃል እንድንናገር በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፤ በእስትንፋሳችን እንደምንተነፍስ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ፡፡

ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ የሥላሴ የባህርይ ከዊን /ሁኔታ/ ስማቸው ነው፡፡ ይህም የኩነታት /የሁኔታዎች/ ሦስትነት በህልውና የሚገናዘቡበት /አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚገኙበት/ ስም ነው፡፡

- አብ ለራሱ ለባዊ /አዋቂ/ ሆኖ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ልብ ዕውቀት ነው፡፡ በእርሱ ልብነት ወልድ መንፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው፤ ያስቡበታል፡፡
- ወልድ ለራሱ ነባቢ /ቃል/ ሆኖ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ ቃል ነው፡፡ በእርሱ ቃልነት አብ መንፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው፤ ይናገሩበታል፡፡
- መንፈስ ቅዱስ ለራሱ ህያው ሆኖ ለአብ ለወልድ ህይወት ነው፡፡ በእርሱ እስትንፋስነት አብ ወልድ ህልዋን ናቸው፤ ሕያዋን ሆነው ይኖሩበታል፡፡

ከዚህ ወጥቶ ግን ለሦስቱ አካላት ለየራሳቸው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ አላቸው ማለት ክህደት ነው፡፡

## ለ. ሥላሴ በእግዚአብሔርነት /እግዚአብሔር በመባል/ አንድ ናቸው፡፡

አብ እግዚአብሔር ይባላል፤ ወልድ እግዚአብሔር ይባላል፤ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ይባላል፡፡ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር ቢባል እንጂ ሦስት እግዚአብሔር አይባልም፡፡ «…አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡» እንዲል፡፡(ዘዳ ፮÷፬)

የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ሦስቱም አካላት እግዚአብሔር እንደሚባሉ /እግዚአብሔር በመባል አንድ እንደሆኑ/ ያሳያሉ፡፡

**አብ እግዚአብሔር ተብሎ እንደሚጠራ፡-**

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት…» /፪ቆሮ. ፲፫÷፲፬/

**ወልድ እግዚአብሔር እንደሚባል፡-**

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ-ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ…» /ሐዋ. ፳÷፳፰/

አማናዊት ቤተ-ክርስቲያንን በደሙ ፈሳሽነት የዋጃትና የመሠረታት እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

**መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ተብሎ እንደሚባል፡- /ሐዋ. ፭÷፫-፮/**

«ጴጥሮስም፡- ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልለው ዘንድ የመሬትህንም ዋጋ ከፍለህ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ እንዴት አደረ?… እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አላታለልህም አለው» ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያን ያታለለው /የዋሸው/ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንደሆነ ነግሮታል፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ አግዚአብሔር እንደሚባል ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ዕብ. ፫÷፯ እና ዘፀ. ፲፯÷፯ በማገናዘብ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሚባል ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን መጻፍ ሲጀምር ሦስቱንም አካላት እግዚአብሔር ብሎ በመጥራትና የህልውናቸውን ቅድምና በመመስከር ነው፡፡

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡» /ዮሐ. ፩÷፩-፪/ ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ማለቱ ሦስቱም አካላት እግዚአብሔር መባል የሚገባቸው በመሆናቸው ነው፡፡

## ሐ. ሥላሴ በፈጣሪነት አንድ ናቸው፡፡

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል “ፈጠረ” አለ እንጂ “ፈጠሩ” አለማለቱ ሥላሴ በፈጣሪነት አንድ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ /ዘፍ. ፩÷፩/፡፡ በተጨማሪም ልበ አምላክ ዳዊት « አንተ ከጥንት ምድርን መሰረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፡፡» ብሎ አንድ ፈጣሪ ብቻ መኖሩን ገልጧል፡፡ /መዝ. ፻፩÷፳፭/

ሥላሴ በመፍጠር አንድ በመሆናቸው « እግዚአብሔር ፈጠረ» ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ፈጣሪ መኖሩን እየተናገረ በሌላ መልኩ በህልውና አንድ ናቸውና ፈጣሪነትን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶም ይናገራል፡፡ /ስለህልውና አንድነት በገጽ 23 የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት/

- ✝ /ኢዮ. ፴፫÷፬/ « የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ» ሲል መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ መሆኑን
- ✝ /ዮሐ. ፩÷፫/ «ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም ሲል ወልድ ፈጣሪ መሆኑን»
- ✝ /መዝ. ፴፪÷፮/ «የእግዚአብሔር ይቅርታው ምድርን ሞላ፣ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፡፡” ሲል ሦስቱም አካላት ፈጣሪ መባል የሚገባቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

### መ. ሥላሴ አምላክ በመባል አንድ ናቸው

አብ አምላክ ይባላል፤ ወልድ አምላክ ይባላል፤ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ይባላል፡፡ ነገር ግን አንድ አምላክ ቢባል እንጂ ሦስት አምላክ አይባልም፡፡ /፩ጢሞ. ፩፥፲፯፤ ኢሳ. ፵፥፳፰/

### ፬-፭-፩-፪ ሦስትነት በምን?

ሥላሴ በስም በአካል፣ በግብር፣ በኩነት እና በመሳሰሉት ሦስት ናቸው፡፡

አካልና ስም ቋንቋዊ ፍቻቸውን ስንመለከት፡-

- **አካል**፡- ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር በሥጋ በአጥንት በጅማት በቁርበት የተያያዘ ገጽን መልክዕን አቋምን ያሳያል፡፡
- **ገጽ**፡- ልብስ የማይሸፍነው ከአንገት በላይ ያለውን መገለጫ ወይም በአጭሩ ፊትን ያመለክታል፡፡ መለያ መታወቂያ ማለት ነው፡፡
- **መልክዕ**፡- ኅብርን፣ ቅርጽን፣ ደም ግባትን፣ ያመለክታል፡፡ ይኸውም ቀይ መልክ፣ ጥቁር መልክ፣ መልከ መልካም፣ መልከ ክፉ ሲል ይታወቃል፡፡
- **ስም**፡- ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ያለው አካል ከሌላ አካል ተለይቶ ማን እንደሆነ ታውቆ የሚጠራበት ነው፡፡

ስም ስንል ሦስት ዓይነት ነው፡፡

ሀ. ***የተጸውዖ ስም***፡- አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚጠራበት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ለሆኑ ተመሳሳይ ባሕርይ ላላቸው የሚሰጥ ስም ነው፡፡ ከሌላ ሁለተኛ ወገን የሚሰጥ ስለሆነ በአብዛኛው ዋናው አገልግሎቱ ከብዙዎቹ ተመሳሳይ አካላት አንዱን ለይቶ ለመጥራት ነው፡፡

ለ. **የግብር ስም**፡- በአካል ተቀድሞ የአካልን እንቅስቃሴ ጠባይና ሥራ የመሳሰሉትትን የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ፡-ገበሬ፣ ሰዓሊ. . .

ሐ. **የአካል ስም**፡- ይህ ስም የሚነሳው ከባሕርይ በመሆኑ ከአካል የሚቀድም ሳይሆን ከአካል ጋር እኩል ህላዌ ያለው ስም  ነው፡፡

**ለምሳሌ**፡- ሰው፣ ፈረስ፣ አንበሳ እንደ ማለት ሲሆን ይህን ስም ያገኙት አካል ሲገኝ ጀምሮ ነው እንጂ ኖረው ኖረው አይደለም፡፡

## ሀ. የሥላሴ የአካል ሦስትነት

ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው፡፡ ይህም ማለት ለአብ ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው፡፡ ለወልድም ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው፡፡ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው፡፡

ሰው በአርአያ ሥላሴ ተፈጥሯልና የሥላሴ መገለጫ ነው፡፡ ለዚህ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር በሰው አካል አምሳል እጅ እግር፣ አይን፣ ጆሮ እንዳሉት የተጻፈው፡፡ «የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ጻድቃኑ ጆሮዎቹም ወደ ልመናቸው ናቸውና፡፡»/መዝ. ፴፫፥፲፭/ «. . .ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት» /ኢሳ. ፷፮፥፩/

ይህ ማለት ግን በእግዚአብሔር አካልና በሰው አካል መካከል ልዩነት የለም ማለታችን አይደለም፡፡ ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ይህንንም ልዩነት በሠንጠረዥ ፫ ተመልከት፡፡

***ሠንጠረዥ ፫፡- የሰውና የሥላሴ አካል ልዩነት***

| የሰው አካል | የሥላሴ አካል |
|---|---|
| ግዙፍ ነው | በዓይን አይታይም፣ በህሊናም አይታሰብም፣ ረቂቅ ነው |
| ውሱን ነው | በሰማይና በምድር በአየር በዕመቅ የመላ ነው፣ በሁሉም ቦታ አለ |
| ጠባብ ነው | ሰፉህ /ሰፊ/ ነው፡፡ ለስፋቱም ልክና መጠን የለውም፣ ላይና ታች ቀኝና ግራ የለውም |
| ፈራሽ በስባሽ ነው<br>/ዘፍ. ፫፥፲፱፤ መዝ. ፻፪፥፲፬/ | ይህ የሌለበት ሕያው ባሕርይ ነው፡፡ /ራዕ. ፩፥፲፰/ |
| ደካማ ነው | ሁሉን ቻይ ድካም የሌለበት ነው፡፡ /ኢሳ. ፵፥፳፲/ |
| አስገኚ አለው | አስገኝ የሌለው ነው፡፡ |

በአጭሩ ሰው ሥጋ ለባሽ ስለሆነ ግዙፍና ተዳሳሽ አካል ሲኖረው እግዚአብሔር ግን መንፈስ በመሆኑ ረቂቅና የማይዳሰስ አካል አለው፡፡ የእግዚብሔርን የአካል ሦስትነት ስናሰብ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ለእየራሳቸው ፍጽም አካል ስላላቸው ሦስቱም በተለየ አካላቸው እኔ ማለት የሚቻለውና እርሱ የሚባልላቸው ናቸው፡፡

«እኔ ፊተኛው ነኝ፤ እኔም ዘላለማዊ ነኝ...ከሆነበትም ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበረሁ፡፡ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል፡፡»

በቅዱስ ወንጌልም እንዲህ የሚል ተጽፏል፡፡

«እኔም አብን እለምነዋለሁ፡፡ እርሱም ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር ይኖር ዘንድ ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፡፡ እርሱም ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው» /ዮሐ. ፲፬፥፲፮-፲፯/

«ሌላ አጽናኝ»መባሉም፡- አብ አጽናኝ ነው ልጁን ወደ ዓለም የላከ ነውና፤ ወልድም አጽናኝ ነው ዓለምን ለማዳን የመጣ ነውና፤ ከሁለቱም ሌላ ፍጹም አካል ያለው አጽናኝ ለማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፡፡

«ከእናንተም ጋር ሳለሁ ይህን ነገርኋችሁ፤ ነገር ግን አብ በስሜ የሚልከው የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፡፡»/ዮሐ. ፲፬፥፳፭-፳፮/

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ ሦስቱም አካላት በአንድ ቦታ በአንድ ሰዓት ማገኘታቸውም ሥላሴ በአካል ፍጹማን ለመሆናቸው /ለእየራሳቸው አካል ያላቸው ለመሆኑ/ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ /ማቴ. ፫፥፲፮ እና ፲፯/

## ለ. የሥላሴ የስም ሦስትነት

ሥላሴ በአካላዊ ግብረ ስም ሦስት ናቸው፡፡ የስም ሦስትነታቸውም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

- አብ ማለት አባት፣ አሥራፂ ማለት ነው፡፡ ወልድን የወለደ፣ መንፈስ ቅዱስን ያሰረጸ ነውና
- ወልድ ማለት ልጅ ማለት ነው፤ የአብ የባሕርይ ልጅ ነውና
- መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ /የተገኘ፣ የወጣ/ ማለት ነው፡፡ ከአብ አብን መስሎ ወልድን አህሎ የሠረፀ ነውና፡፡

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለው የሥላሴ የአካል ሰማቸው ነው፡፡ ምንም እንኳ ሥላሴ በዚህ ጊዜ ተገኙ ባይባልም፣ ጥንት መሠረት ሳይኖረው ቅድመ ዓለም ሲኖር የኖረ ነው እንጂ እንደ ተጸውዖ ስም ኖሮ ኖሮ የወጣ አይደለም፡፡ የሥላሴ አካል ጥንት እንደሌለው ሁሉ ለስሙም ጥንት የለውም፡፡

አብ ተለውጦ ወልድ መንፈስ ቅዱስን እንደማይሆን የአብ ስሙ ተለውጦ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም፡፡ ለአብ የአባትነት ስም የአባትነት ክብር አለውና፡፡ ወልድም ወልድ ቢባል እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም፣ የባሕርይ ክብሩ ከአብ ሳያንስ የልጅነት ክብር የልጅነት ስም አለውና፡፡ መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ቢባል እንጂ አብ ወልድ ተብሎ አይጠራም፡፡ የባሕርይ ክብሩ ከአብ ከወልድ ሳያንስ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል እንጂ፡፡

የሥላሴ የስም ሦስትነት በብሉያትም በሐዲሳትም ተመስክሯል፡፡

**በብሉይ ኪዳን**

«እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድሁህ» /መዝ. ፪፥፯/

ቅድመ ዓለም አካል ዘእምአካል፣ ባሕርይ ዘእምባሕርይ የወልድኩህ ልጄ ነህ አለኝ፡፡ ዛሬም በተዋህዶ የወለድኩህ ልጄ ነህ አለኝ ብሎ አብና ወልድን ያነሳል፡፡ ተናጋሪው ወልድ ነው፤ እግዚአብሔር ብሎ አብን አንስቷል፡፡

«ይህን ታውቅ እንደሆንህ፤ ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?» /ምሳ. ፴፥፬/ ይህ ቃል አብ የአባትነት፣ ወልድ የልጅነት ስም እንዳላቸው ያሳያል፡፡

**በሐዲስ ኪዳን**

«ሂዱና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃኋችሁ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፡፡»/ማቴ. ፳፰፥፲፱/

«ያ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡...ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህም ከእኔ ወስዶ ይነግራችኋል አልኋችሁ፡፡» /ዮሐ. ፲፮፥፲፫-፲፭/

ሥላሴ በክብር በሥልጣን አንድ ስለሆኑ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብለው ሲጠሩ የሥልጣን ቅደም ተከተልን የሚያሳይ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወልድን አስቀድሞ፤ አብና መንፈስ ቅዱስን አስከትሎ ሲጠራ በሚከተለው ጥቅስ ማየት ይቻላል፡፡

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡» /፪ቆሮ. ፲፫፥፲፬/

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ አብን አስቀድሞ መንፈስ ቅዱስንና ከዚያም ወልድን አስከትሎ ሲጠራ የሚከተለው ምንባብ ያሳያል፡፡

«. . .እግዚአብሔር አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስ ቅዱስም እንደሚቀዱሱ፣ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ...» /፩ጴጥ. ፩፥፪/

## ሐ. የሥላሴ የግብር ሦስትነት

ግብር ማለት ሥራ ማለት ነው፣ ሥላሴ በግብር ሦስት ናቸው፡፡

- የአብ ግብሩ ወልድን መውለድ መንፈስ ቅዱስን ማሥረጽ ነው፡፡
- የወልድ ግብሩ ከአብ መወለድ ነው፡፡
- የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ከአብ መስረጽ ነው፡፡

አብ ቢወልድ ቢያሥርፅ እንጂ እንደ ወልድ አይወለድም፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሠርፅም፡፡ ወልድም ቢወለድ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም፤ እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም፡፡ መንፈስ ቅዱስም ቢሠርፅ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም እንደ ወልድም አይወለድም፡፡

ወላዲ አሥራፂ፣ ተወላዲ፣ ሠራፂ የሚለው የሥላሴ የአካል ግብር ስማቸው ነው፡፡ ይህም በቅድሳት መጻሕፍት ምስክርነት የተረጋገጠ ነው፡፡

«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው» /ማቴ. ፫፥፲፯/ ይህ ቃል አብ ወልድን እንደ ወለደ ያሳያል፣ ልጄ ብሎ ጠርቶታልና፡፡

«እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ጰራቅሊጦስ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ…» /ዮሐ. ፲፭፥፳፮/ ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደ ሰረፀ ያሳያል፡፡

አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሠርፅ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ በፊት የነበረ አያሰኝም፡፡ በእኛ ግዕዝ /ልማድ/ አባት ሲበልጥ ሲቀድም፤ ልጅ ሲተካ ሲከተል ነው፡፡ በሥላሴ ግን አብን አባት ወልድን ልጅ መንፈስ ቅዱስን ሠራፂ ስላለን መቅደም መቀዳደም፤ መከተል መከታተል፤ መብለጥ መበላለጥ የለባቸውም፡፡ የውስጥ የባሕርይ ግብር ነውና፡፡

## ሐ. የሥላሴ የኩነት ሦስትነት

ኩነታት በህልውና /በአኗኗር/ እየተገናዘቡ በአንድ መለኮት የነበሩ ያሉና የሚኖሩ ናቸው፡፡ እነርሱም ልብነት ቃልነትና እስትንፋስነት ናቸው፡፡

- **ልብነት**፡- በአብ መሰረትነት ለራሱ ልባዊ /አዋቂ/ ሆኖ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ልብ /ዕውቀት/ መሆን ነው
- **ቃልነት**፡- በወልድ መሠረትነት ለራሱ ነባቢ /ቃል/ ሆኖ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ /ቃል/ መሆን ነው
- **እስትንፋስነት**፡- በመንፈስ ቅዱስ መሠረትነት ለራሱ ሕያው ሆኖ ለአብ ለወልድ ሕይወት መሆን ነው፡፡

የኩነታት ሦስትነት ከአካላት ሦስትነት ይለያል፡፡ ኩነታት ያለተፈልጦ በተጋብኦ በአንድነት አካላትን በህልውና እያገናዘቡ በአንድ መለኮት ያሉና የሚኖሩ ናቸው፡፡ አካላት ያለተጋብኦ በፍጹምነት ያሉ በህልውና እያገናዘቡ በአንድ መለኮት ያሉና የሚኖሩ ናቸው፡፡ አካላት ያለተጋብኦ በፍጹምነት ያሉ ናቸው፡፡ ሥላሴ በአካላት ፍጹም ሦስት ሲሆኑ በልብ፣ በቃል፣ በእስትንፋስ ግን ተገናዛቢዎች ስለሆኑ በአንድ ልብ ያስባሉ፣ በአንድ ቃል ይናገራሉ፣ በአንድ እስትንፋስ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ፣ አንድ ፈቃድ ይፈቅዳሉ፣ አንድ አሳብ ያስባሉ፣ በአንድነት አንድ ሥራ ይሠራሉ፣ በአንድነት ይመለካሉ፡፡

*ውድ ተማሪዎች ይህ ከላይ በዝርዝር የተመለከትነው የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በብሉያትና በሐዲሳት እንዴት እንደተገለጠ ደግሞ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡*

**በብሉይ ኪዳን**

**ጥቅስ አንድ፡-**

«እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን እንፍጠር፡፡»/ዘፍ. ፩፥፳፮/

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል "እግዚአብሔርም አለ" ብሎ አንድነቱን፣ ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን እንፍጠር ብሎ ብዛቱን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም "እንፍጠር" የሚለው በፈጣሪነት ሥልጣን ትክክል /እኩል/ የሆኑ አካላት የሚነጋገሩ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ጥቅስ ሁለት፡-**

«እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፡፡»/ዘፍ ፫፥፳፪/ እግዚአብሔር አለ ብሎ አንድነቱን ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ብሎ ከሁለት አካል በላይ እንደሆኑና ሥላሴ አንድ አካል አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

**ጥቅስ ሦስት፡-**

« እግዚአብሔርም አለ…ኑ እንውረድ አንዱም የሌላውን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው፡፡» /ዘፍ. ፲፩፥፯/

«እግዚአብሔርም አለ» በሚለው አንድነቱን፣ «ኑ እንውረድ» በሚለው ደግሞ አንዱ አካል ከአንድ በላይ ለሆኑ ሌሎች አካላት መናገሩን እንገነዘባለን፡፡ በተጨማሪም «ቋንቋቸውን እንደባልቀው» የሚለው የመፍረድ የመቅጣት ስልጣናቸው እኩል /አንድ/ የሆኑ አካላት እንዳሉ ያሳያል፡፡

**ጥቅስ አራት፡-**

/ዘፍ. ፲፰፥፩-፲/

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍለ ንባብ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሦስት ሰዎች አምሳል መገለጹ ተመልክቷል፡፡ ይህም ቀደም ባሉት ጥቅሶች ግልጽ ሆኖ ያልተቀመጠውን የእግዚአብሔር ሦስትነት ገሃድ ያደርገዋል፡፡

አብርሃምም ይናገረው የነበረው አንድነትና ሦስትነትን የሚያሳይ ነው፡፡

- «አቤቱ በፊትህ ባለሟልነትን አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈው» ማለቱ ሦስቱ ሰዎች በጌትነት አንድ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ቀጠል አድርጎ…
- «ውኃ እናምጣላችሁ» ማለቱ በሦስትነታቸው መናገሩ ነው

- «ሦስት መስፈሪያ ዱቄት አዘጋጂ» ብሎ ሚስቱን ሣራን ሲያዛት ሦስትነትን «ለውሽውም እንጎቻ አድርጊ» ብሎ በአንድ ለውሳ አንጎቻ እንድትጋግር ማዘዙ ደግሞ የሦስቱን አንድነት ያጠይቃል፡፡

**ጥቅስ አምስት፡-**

«የእስራኤልን ልጆች ስትባርኳቸው እንዲህ በሏቸው፡፡ እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፡፡ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሳ ሰላምንም ይስጥህ» /ዘኍ ፮፥፳፫-፳፯/

ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር መባሉ ሦስትነትን፤ ቃሉ አንድ መሆኑ እንድነትን ያመለክታል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ፪ኛ ቆሮ. ፲፫፥፲፬ ላይ ከተናገረው ቃል ጋር በማቆራኘት እንደሚከተለው ይተረጎማል፡፡

«እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም» የሚለው ለእግዚአብሔር ወልድ የተነገረ ነው፡፡ ይህም ማለት ቡሩክ እግዚአብሔር መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን አርቆልህ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን ይስጥህ፣ በነፍስም በሥጋም ይጠብቅህ፣ ከክህደት ከጥርጥር ከሥጋዊ ጠላት፣ ከጸብአ አጋንንት ከመርገም ከኩነኔ ከገሃነም ይጠብቅህ ማለት ነው፡፡ ይህም ያለ እግዚአብሔር ጸጋ አይገኝምና ቅዱስ ጳውሎስ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ» ብሎ ጠቅሶታል፡፡«ጸጋሰ ሥርየተ ኃጢአት ይእቲ» እንዲል ሰው ከኃጢአት እስራት የተፈታ፣ከሲኦል የወጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነውና፡፡

«እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፣ ይራራልም»

ሰው ወዳጁን በብሩህ ገጽ በፈገግታ ይቀበለዋል፡፡ ብሩህ ገጽ የፍቅር መግለጫ ነው፡፡ ርህራሄ ደግሞ ከፍቅር የሚመነጭ ነው፡፡ ምስጢሩም እግዚአብሔር እኛን በፍቅር አይን ተመልክቶ በርህራሄው ከመከራ እንደሚያድነንን የሚያስረዳ ነበረ፡፡ «የእግዚአብሔር ፍቅር» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ለጠቀሰው ነው፡፡ /በተጨማሪም ዮሐ. ፫፥፲፯፤ ፩ዮሐ. ፫፥፲፱ ተመልከት/

«እግዚአብሔር ፊቱን ወዳንተ ያንሳ ሰላምንም ይስጥህ»

ይህም በምሕረት ዓይን ይመልከትህ፤ በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋ ሰላምን ይስጥህ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት» ያለው ነው፤ የመንፈስ ቅዱስ ሰላም ሲል፡፡ ሰላም የሚገኘው ሕብረት ባለበት ነውና፡፡ ሰላምና ሕብረት፤ ጸብና መለያየት አይነጣጠሉምና፡፡

**ጥቅስ ስድስት፡-**

«የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገች፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች» /መዝ. ፻፲፯፥፲፮-፲፯/ የእግዚአብሔር ቀኝ የሚለው ሦስት ጊዜ መነገሩ የሦስትነት፤ ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ያመለክታል፡፡

**ጥቅስ ሰባት፡-**

«እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤ ኃይሉም ታላቅ ነው፤ ለጥበቡም ቁጥር የለውም» /መዝ. ፻፵፮፥፭/

ይህም ማለት፡- እግዚአብሔር አብ ገናና ነው፤ ኃይሉ እግዚአብሔር ወልድም ገናና ነው፤ ኃይሉ አለው ኃይሉ ስለተገለጸበት፣ በኃይል አንድ ስለሆኑ፡፡ ጥበቡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ሀብቱ ፍጹም ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሀብቱ ብዙ ነውና ስፍር ቁጥር የሌለው ጥበብ ብሎ መንፈስ ቅዱስን አነሳ፡፡ /ኢዮ. ፱፥፬/

**ጥቅስ ስምንት፡-**

«አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድርም ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበረ፡፡»/ኢሳ. ፮፥፫/

ሦስት ጊዜ ቅዱስ መባሉ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ የአንድነቱ ምሳሌ ነው፡፡ በሌላም መልኩ ሦስት ጊዜ ቅዱስ መባሉ የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ ሦስቱ አካላት በምስጋና ትክክል መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ድግግሞሽ ነው እንዳይባል መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት በዕብራውያን የአነጋገር ዘይቤ ደጋም ቃል ሁለት ጊዜ ነው እንጂ ሦስቴ አይደለም፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች ተመልከት፡፡ /ዘፍ. ፳፪፥፲፩፤ ዘፀ. ፫፥፬፤ ፩ሳሙ ፫፥፲/

**ጥቅስ ዘጠኝ፡-**

«የጌታንም ድምጽ፡- ማንን እልካለሁ? ማንስ ወደዚያ ሕዝብ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ» /ኢሳ. ፮፥፰/ ማንን እልካለሁ? የሚለው አንድነቱን፣ ማንስ ይሄድልናል? የሚለው ደግሞ ሦስትነቱን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም የሚከተሉት የብሉይ ኪዳን ምንባባት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| - ኢሳ. ፵፰፥፲፪-፲፯ | - ጦቢ. ፰፥፮ | - ሲራ. ፫፥፳፪ |
| - መዝ. ፴፪፥፭-፯ | - ዘፍ. ፪፥፲፰ | |

## በሐዲስ ኪዳን
የአንድነቱና የሦስትነቱ ነገር በብሉይ ኪዳን በምሥጢር የታወቀ ቢሆንም በሐዲስ ኪዳን ግን በግልጽ ተቀምጧል፡፡

**ጥቅስ አንድ፡-**

«ጌታችን ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃ ወጣ፡፡ እነሆም ሰማይም ተከፈተለት፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየ፡፡ እነሆም በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ፡፡»/ማቴ. ፫፥፲፮-፲፯/

ሰማይ ተከፈተ መባሉ ደጅ በተከፈተ ጊዜ የውስጡ እንዲታይ እስከ አሁን ያልተገለጠ ምስጢር ታየ፣ ተገለጠ ለማለት ነው፡፡ ጌታ ሲጠመቅ ሦስት አካላት በአንድ ሰዓት /ጊዜ/ ተገኝተዋል፡፡ አንዱ አካል ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ሲወጣ፤ መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ በአምሳለ ርግብ ሲወርድ፤ አካላዊ አብ በተለየ አካሉ በደመና ሆኖ ሲመለከት፣ የወደደውን ለተዋህዶ ሥጋ ወደ ዓለም የላከው ኢየስስ ክርስቶስ መሆኑን ሲናገር ሦስትነት ተረድቷል፡፡

**ጥቅስ ሁለት፡-**

«ሂዱና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፡፡» /ማቴ. ፳፰፥፲፱/

ይህ ጥቅስ የሥላሴን የስም ሦስትነት /ሥላሴ በስም ሦስት መሆናቸውን/ ይገልጻል፡፡

**ጥቅስ ሦስት፡-**

«መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፤ የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል፣ ከአንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው፡፡» /ሉቃ. ፩፥፴፭/

**ጥቅስ አራት፡-**

«እነሆም በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ አየሁ፤ ከእርሱ ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግንባራቸው የተጻፈባቸው....»/ራዕ. ፲፴፥፩-፪/

በግ ያለው ለሰው ልጆች ቤዛ የሐዲስ ኪዳን መስዋዕት ሆኖ የቀረበውን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ስለጌታችን ሲመሰክር፡-

« እነሆ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» እንዳለ፡፡ /ዮሐ. ፩፥፴፮/

**ጥቅስ አምስት፡-**

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፡፡» /ራዕ. ፬፥፰/

ለትንቢተ ኢሳይያስ ፮፥፫ የተሰጠውን ማብራሪያ በገጽ 32 ተመልከት

## ፬-፫-፪ ስለምስጢረ ሥላሴ የሚያስረዱ ተፈጥሯአዊ ምሳሌዎች

### *ሀ. የሰው ምሳሌነት*
የሰው ነፍስ ሦስትነት አላት፡፡ ልብነት፣ ቃልነት፣ ሕይወትነት፡፡ በልብነቷ የአብ፣ በቃልነቷ የወልድ፣ በሕይወትነቷ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነች፡፡

- ነፍስ እነዚህ ሦስት ነገሮች ስላሏት ሦስት ነፍስ እንደማትባል ሥላሴም በአካል ሦስት ቢሆኑም አንድ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ቢባሉ እንጂ ሦስት እግዚአብሔር ሦስት አምላክ አይባሉም፡፡
- የነፍስ ልብነቷ ቃልነቷ ሕይወትነቷን ከራሷ ታስገኛለች፡፡ ቃልና ሕይወት ከአንዲት ልብ ስለተገኙ በከዊን /በመሆን/ ልዩ እንደ ሆኑ ሁሉ በመነጋገር ይለያሉ፡፡ ቃል ተወለደ እስትንፋስ ሠረፀ /ወጣ/ ይባላል፡፡ እንደዚሁ አብ ወለድን በቃል አምሳል ወለደው፤ መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ አምሳል አሠረፀው፡፡
- ነፍስ ስትገኝ በሦስትነቷ በአንድ ጊዜ ተገኘች እንጂ ልብነቷ ቀድሞ ቃልነቷና እስትፋስነቷ በኋላ የተገኙ አይደሉም፡፡ እንደዚሁ አብ ወልድን ሲወልደው መንፈስ ቅዱስን ሲያሰርፀው አይቀድማቸውም፡፡

ሰው በነፍሱ በዚህ አኳኋን እግዚአብሔርን ስለሚመስለው እግዚአብሔር «ሰውን በአርአያችንና በምሳሌአችን እንፍጠር» ብሎ ተናገረ፡፡ /ዘፍ. ፩፥፳፮/

### *ለ. የፀሐይ ምሳሌነት*
ለፀሐይም ሦስትነት አላት፡፡ ክበብ፣ ብርሃንና ሙቀት፡፡ በክበቧ አብ፤ በብርሃኗ ወልድ በሙቀቷ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡

- የፀሐይ ብርሃን የፀሐይ ክበብ፣ የፀሐይ ሙቀት ብለን ሦስት ጊዜ ፀሐይ ፀሐይ ማለታችን ለፀሐይ ሦስትነት እንዳላት ያሳያል እንጂ ሦስት ፀሐይ አለ እንደማያሰኝ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ማለታችንም ሦስት እግዚአብሔር ሦስት አምላክ አያሰኝም፡፡ /መዝ. ፲፰፥፬/

- የፀሐይ ክበቧ ብርሃኗንና ሙቀቷን ያስገኛል፤ ሆኖም ግን ብርሃንና ሙቀትን ቀድሞ የሚገኝበት ጊዜ የለም፡፡ እንደዚሁም ሁሉ አብ ወልድን ቢወልድ መንፈስ ቅዱስን ቢያሰርፅ ወልድና መንፈስ ቅዱስን ቀድሞ የኖረበት ጊዜ የለም፡፡ በሥላሴ ዘንድ መቅደም መቀዳደም የለም፡፡
- ክበብ ብርሃኑን ፈንጥቆ ጨለማን በማራቁ፣ ዋዕዩን /ሙቀቱን/ ልኮ በማሞቁ ህልውናውን /መኖሩን/ እንዲያሳውቅ የአብም ህልውናውን በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስለተገለጸ አብን ላኪ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን ተላኪ አልን እንጂ በሥላሴ መብለጥ መበላለጥ ኖሮባቸው አይደለም፡፡

### ሐ. የእሳት ምሳሌነት


ስዕል ፫፡ የሦስት ማዕዘን ቀርጽ ምሳሌነት

እሳትም አንድ ሲሆን ሦስትነት አለው፤ አካሉ፣ ብርሃኑና ሙቀቱ፡፡ በአካሉ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በሙቀቱ መፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡«እሳት አመጣ» ሲባል ብርሃኑን «እሳት አብራ» ሲባል ብርሃኑን «እሳት እንሙቅ» ሲባል ሙቀቱን መናገር ነው፡፡ በዚህም ለእሳት ሦስትነት እንዳለው እንረዳለን፡፡

- እሳት አንድ ሲሆን ሦስትነት እንዳለው፤ ሦስትነት ስላለው እንደ አንድ እንደሆነ ሥላሴም በአካል ሦስት ሲሆኑ በባህርይ በሕልውና አንድ ናቸው፡፡

### መ. የባህር /የቀላይ/ ምሳሌነት

የባህር ሦስትነት ስፋቱ ርጥበቱና ሑከቱ /መናወጹ/ ነው፡፡ በስፋቱ አብ፣ በእርጥበቱ ወልድ በሑከቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡





- ይህ ሦስት ከዊን /ሁኔታ/ ያለው ባሕር አንድ ባሕር ይባላል እንጂ ሦስት ባሕር እንደማይባል ሁሉ ሦስት ከዊን ያላት ባሕርየ ሥላሴ፣ መለኮተ ሥላሴም አንዲት ብትባል እንጅ ሦስት አትባልም፡፡

### ሠ. የሦስት ማዕዘን ቅርጽ (Equilateral Triangle) ምሳሌነት

ሀ = ለ = ሐ ጎኖቹ

በማናቸውም ሁኔታ አንድ ዓይነት የሆኑ ሦስት ጎንዎች ጫፍና ጫፋቸው ሲገናኝ ሦስቱም ሦስቱም አንግሎቹ እኩል የሆነ ሦስት ማዕዘን (Equilateral Triangle) ይገኛል፡፡




- ሦስቱ ጎኖች በየራሳቸው ጎን የቆሙ እንደሆነ ሁሉ
  ሥላሴም በሦስት አካላት፣ በሦስት ገጻት ፍጹማን ናቸው፡፡
- በሦስቱ ጎኖች መካከል የርዝመት የውፍረት ልዩነት
  እንደሌለ በማናቸውም ነገር እኩል እንደሆኑ ሥላሴም በክብር አንድ ናቸው፡፡
- ከሦስቱ ጎን አንዱ ከሌላ ሦስት ማዕዘን አይባልም
  እንደዚሁም ሁሉ ከሥላሴ አንዱ ፍጡር የሚል በአምላክ
  ሕልውና ላይ ምን ያህል የክህደት ትምህርት እንዳስተማረ ከምሳሌው እንረዳለን
- የሦስቱ ጎን ግራ ቀኙ እንዳይታወቅ ለሥላሴም ግራ ቀኝ የላቸውም

«ተቀዳሚና ተከታይ ቀኝና ግራ የለብንም፣ ጠፈር የለብንም መሠረትም የለብንም ጠፈርም መሠረትም እኛው ነን» /ቅዳሴ /

## ፬-፮ ምሥጢረ ሥጋዌ

### ፬.፮.፩ ትርጉም

*ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች ከአምስቱ አዕማደ ምስጢራት መካከል በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ምስጢረ ሥላሴ ከላይ ለመመልከት ሞክረናል፡፡ በዚህ ክፍል ምሥጢረ ሥጋዌን እንመከለታለን፡፡ ትምህርቱን ከመጀመራችን በፊት ምሥጢረ ሥጋዌ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ለመግለጽ ይሞክሩ?*

> *ሥጋዌ የሚለው ቃል ተሠገወ = ሥጋ ሆነ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ሠው መሆን፣ ሥጋ መልበስ ማለት ነው፡፡*

ምሥጢረ ሥጋዌ ስንልም ሰው የመሆን፣ ሥጋ የመልበስ ነገር የሚነገርበት፤ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል በከዊን ስሙ ቃል የሚባለው ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋ የመልበሱ ነገር የሚነገርበት ምሥጢር ማለት ነው፡፡ ይህንንም ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል ሥጋ ሆነ» ብሎ የገለጸው ነው፡፡ /ዮሐ. ፩፥፲፬/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ እግዚአብሔር ወልድ ሰው የመሆኑን ነገር ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ፡፡» /ገላ. ፬፥፬/

### ፬-፮-፪ የሰው ልጅ ተፈጥሮና ክብር

እግዚአብሔር ፳ ቀን ሙሉ ዓለምን በሥነ-ፍጥረት እያስጌጠ ካዘጋጀ በኋላ ዓርብ በነግህ «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ብሎ ተናገረ፡፡/ዘፍ. ፩፥፳፮/እንዲህ ተናገረና ግዙፍ አካል ሥጋን ከ፬ ባሕሪያት ከመሬት፣ ከውኃ፣ከነፋስና ከእሳት ከፍሎ አገናኝቶ በሥጋ አለስልሶ በደም አርሶ በጅማት አያይዞ ባጥንት አጽንቶ፣ ረቂቅ አካል ነፍስን ካለመገኛ አስገኝቶ ዕውቀት ቃል ሕይወት ሰጥቶ፣ እነዚህን ሥጋንና ነፍስን አዋሕዶ ሰውን በምሳሌው ፈጠረ፡፡ /ዘፍ. ፪፥፯፤ ዘፍ. ፩፥፳፯/

ሰው የሚለው በግእዝ ስብእ የሚለውን ቃል ነው፡፡ ሰብእ ማለት ፯ ሁኔታ /ጠብዓይት፣ ግብራት/ ያለው አካል ማለት ነው፡፡ የተለየ ስሙን ግን አዳም ብሎ ሰይሞታል /ዘፍ. ፫፥፪/፡፡ አዳም በተፈጠረ በ፫ኛው ቀን (በሁለተኛው ዓርብ) የምትረዳውን የምትስማማውን ረዳት እንፍጠርለት እንጂ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» ብሎ ከአዳም ጎን አንድ አጥንት ወስዶ የምትረዳውን ሴት ፈጠረለት፡፡/ዘፍ. ፪፥፲፰ እና ፳፩፥፳፫፤ ኩፋ. ፬፥፬-፮/፡፡ አዳምም ከጎኑ ለተገኘች ሴት ሔዋን ብሎ መጠሪያ ስም አወጣላት /ዘፍ. ፫፥፳/፤ ትርጉሙም የሕያዋን እናት ማለት ነው፡፡

**ሰው ክቡር ፍጥረት መሆኑ፡-**

- ✝ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ በመፈጠሩ
- ✝ ከአምላክ በታች በተሰጠው የገዥነት ሥልጣን ታውቋል፡፡ /ዘፍ. ፩፡-፳፰-፴፤ መዝ.፰፥፮-፰/

## ፬-፮-፫ የሰው ልጅ የተሰጠው ነጻ ፈቃድና አምላካዊ ትዕዛዝ

የሰው ልጅ ሙሉ ነጻነት ያለው ፍጡር ነው፡፡ ይህም የሚታወቀው በተሰጠው አእምሮ የወደደውን /ክፉውን ከሻተ ክፉውን መልካሙን ከሻተ መልካሙን/ እንዲመርጥ የመምረጥ ሙብት የተሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ የሚከተሉት ምንባባት ይህን የሰው ልጅን ነጻነት ያሳያሉ፡፡

«እነሆ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና ሞትን መልካምንና ክፋትን አኑሬአለሁ፡፡ ዛሬ እኔ የማዝህን የአምላክንህ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ብትሰማ፣ አምላክህን እግዚአብሔርንም ብትወድድ፣ በመንገዶቹም ሁሉ ብትሄድ፣ ሥርዓቱንና ፍርዱንም ብትጠብቅ በሕይወት ትኖራለህ...ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፣ ብትታለልም ለሌሎች አማልክትም ብትሰግድ ብታመልካቸውም ፈጽመህ እንደምትጠፋ እኔ ዛሬ እነግርሃለሁ...አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖር ዘንድ ሕይወትን ምርጥ...እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመትና ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ውደደው፣ ቃሉን ስማው፣ አጥናውም፡፡»/ዘዳ. ፴፥፲፫-፳/

«እሺ ብትሉና ብትሰሙኝ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉና ባትሰሙኝ ግን ሰይፍ ይበላችኋል» /ኢሳ. ፩፥፲፱/

« ከወደዳችሁኝስ ትእዛዜን ጠብቁ» /ዮሐ. ፲፬፥፲፫/

እግዚአብሔርም ለአዳም «ከገነት ካለው ዛፍ ሁሉ ብላ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያሳየውና ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፡፡ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» ብሎ አምላካዊ ትእዛዝ ሰጠው፡፡ /ዘፍ. ፪፥፲፯/ ውድ ተማሪዎች ይህም አምላካዊ ትእዛዝ የተሰጠበት ምክንያት እንደ ሚከተለው እንመለከተዋለን፡-

**፩ኛ. አዳም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር እንዲገለጥ**

እግዚአብሔር ለአዳም ያለው ፍቅር ከመፍጠር እስከ መግቦት ባለው ተገልጧል፡፡ የአዳም ፍቅር የሚታወቀው ደግሞ የፈጣሪውን ሕግና ትእዛዝ በመጠበቅ ነው፡፡ «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለ፣ የሚጠብቀውም የሚወደኝ እርሱ ነው፡፡»እንዲል፡፡ /ዮሐ. ፲፬፥፳፩

ይህንን ትእዛዝ በማክበር አዳም ከክብሩ ሳይጎድልበት፤ ከጸጋው ሳይቀነስበት ለ፯ ዓመታት እርሱ በእግዚአብሔር ቤት እግዚአብሔርም በእርሱ ልቦና ኖሩ፡፡ «ትእዛዙን የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል፣ እርሱም ይኖርበታል»እንዲል /፩ዮሐ. ፫፥፳፬/

**፪ኛ. ፍጡርነቱ ይታወቅ ዘንድ**

ዕፀ በለስ አዳም የሚገዛለት ፈጣሪ እንዳለው የምታሳውቅ የተገዥነት ምልክት ነበረች፡፡ አዳም «ሁሉን ግዛ» ቢባልም ካስገዛለት በታች መሆኑን ያውቅ ዘንድ አድርግ አታድርግ የሚል ሕግ ተሰጥቶታል፡፡

**፫ኛ. ነጻ ፈቃዱ ይገለጥ ዘንድ**

የአንድ ሰው ነጻ ፈቃዱ የሚታወቀው የመምረጥ ሙብት ሲኖረው ነው፡፡ በመሆኑም ለአዳም ሁለት ምርጫ ተሰጠው፤ ሌሎችን ዛፎች ቢበላ በሕይወት የመኖርና ዕፀ በለስን ቢበላ የመሞት ምርጫ፡፡ ዕፀ በለስን ባይፈጥርለት ኖሮ አዳም ወዶ ፈቅዶ መርጦ መታዘዙን ማውቅ ባልተቻለ ነበረ፡፡

## ፬-፮-፬ የሰው ልጅ አወዳደቅ

አዳምና ሐዋን በገነት ፯ ዓመት ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው በሕይወት ከኖሩ በኋላ ሰይጣን በእባብ አድሮ አስቀድሞ «ለእመ ትበልዑ ኢንትኮ በለሰ ሞተ ዘትመውቱ» ያላቸውን "ለእመ ትበልዑ ኢንትኮ በለስ አኮ ሞተ ዘትመውቱ አላ አማልክተ ትከውኑ" ብሎ አስቷቸው በሉ፡፡ የአምላካቸውንም ሕግ ሻሩ፡፡ /ዘፍ. ፫፥፩/፡፡ ክብሩ የሰው ልጅ ወደቀ፡፡

*ውድ ተማሪዎች አዳም ወደቀ ስንል የሚከተሉትን ለማለት ነው፡-*

- ✝ *ጸጋው ተገፈፈ*
- ✝ ባሕርይው ጎሰቆለ ማለት ነው፡፡

**፩ኛ. ጸጋው ተገፈፈ ስንል፡-**

- ***ራቁቱን ሆነ***

አዳምና ሔዋን ለብሰውት ከነበረው በጸጋ ከተሰጣቸው የብርሃን ልብስ ተራቆቱ፡፡ «የሁለቱም ዐይኖች ተከፈቱ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ፡፡» እንዲል፡፡ /ዘፍ. ፫፥፯/

- ***ኃይልን አጣ***

አዳም ከበደል በኋላ ፈቃደ ነፍሱ በፈቃደ ሥጋው ላይ የነበራትን ኃይል አጣች፡፡ እንስሳን ይመስል ለመብላት ባማረ፣ ለዓይን በሚያስጎመጅ፣ ለጥበብ መልካም መስሎ በሚታይ ነገር ተሸነፈ፡፡ «ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም፤ ልብ እንደሌላቸው እንስሶች ሆነ፤ መሰላቸውም፡፡» /መዝ. ፵፰፥፲፪/

ይህም ብቻ ሳይሆን የአምላኩን የፍቅር ድምፅ እንኳ የሚያዳምጥበት መንፈሳዊ ኃይል አጥቷል፡፡ «በገነት ስትመላለስ ድምፅህን ሰማሁ ዕራቁቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ ተሸሸግሁም፡፡» /ዘፍ. ፫፥፲/

- ***እንግዳ ሆነ***

የገነት ባለርስት የዚህ ዓለም ጌታ የነበረው የሰው ልጅ ከበደል በኋላ ይህንን ሁሉ አጥቶ እንግዳ ሆነ፡፡ «እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና፤ እንደ አባቶችም ሁሉ እንግዳ ነኝና፡፡» /መዝ. ፴፰፥፲፫፤ ዘፍ. ፵፯፥፰/

**፪ኛ. ባሕርይው ጎሰቆለ ስንል፡-**

- ***ሰላሙን አጣ***

አዳም ከበደል በኋላ በባሕርይው የነበረውን ፍጹም ሰላም አጥቷል፡፡ የኃጢአት ፍጻሜው ሰላምን ማደፍረስ፣ ፍርሃትን ማንገስ ነውና አዳም ኃጢአትን ከፈጸመ በኋላ "ፈራሁ ተሸሸግሁ" የሚል ሆኗል፡፡ መጽሐፍ እንዲህ እንዲል፡

«ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ተማምኖ ይኖራል» /መጽ. ተግ ፬፥፩/በግሪኩ ምሳሌ ፳፰፥፩/

- ***ሕያውነትን አጣ***

እግዚአብሔር ሰውን በንጹሕ ባሕርይ ያለ ሞት ፈጥሮት ነበረ፡፡ሕያው ፍጥረት አዳም ግን በነጻ ፈቃዱ ተጠቅሞ "አትብላ" የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ በማፍረሱ በነፍስ በሥጋ ሟች ሆነ፡፡በሥጋው ርደተ መቃብር በነፍሱ ርደተ ሲዖል ተፈረደበት፡፡

- ***እግዚአብሔርን መምሰል አጣ***

አምላክ ዘበጸጋ የነበረ ሰው ከአለቆች እንደ አንዱ /ዲያብሎስ/ በኃጢአት በመውደቁ እግዚብሔርን የመምሰል ክብር አጣ፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት ይህን እንደተናገረ

«እኔ ግን እላለሁ አማልክት ናችሁ፤ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፡፡ እናንተ ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ፡፡»/መዝ. ፹፥፩-፯/

- ***ገነትን አጣ***

እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለምና /ማቴ. ፳፪፥፴፪/ ሞትን የተሸከሙ አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረሩ፡፡

- **ባለዕዳ ሆነ**

ነጻ ፍጥረት የነበረው አዳም ሞትን ያህል ዕዳ ተሸከመ፡፡

*ውድ ተማሪዎች ለአባታችን አዳማና ለእናታችን ሔዋን መውደቅ ተጠያቂ ማን ይመስላችኋል?*

## ለአዳም መውደቅ ተጠያቂ ማን ነው?

**፩ኛ. የዕፀ በለስ መኖር ነውን?**

ዕፀ በለስ ቀድሞውን የተፈጠረችው ለአዳም መሳሳት ምክንያት እንድትሆን ሳይሆን የአዳም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር፣ እንዲሁ ነጻ ፈቃዱ እንዲገለጥባት፣ ፍጡርነቱ እንዲታወቅባት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም ዕፀ በለስ መታዘዝን የምትገልጥ የምልክት ዛፍ ነበረች እንጂ በራሷ ተጉዛ መጥታ አዳምን ብላኝ ብላ አላስገደደችውም፤ በአዳም ላይ ሞትን ያመጣችው ባለመታዘዙ እንጂ ሞትን የሚያመጣ መርዝ በመያዟ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ዕፀ በለስ ልትሆን አትችልም፡፡

**፪ኛ. ዲያብሎስ ነውን?**

ዲያቢሎስ ክፉን ምክር ለአዳምና ለሔዋን መከራቸው እንጂ እጃቸውን ይዞ ዕፀ በለስን አላስቆረጣቸውም፡፡ አመዛዝኖ መወሰን የእነርሱ ድርሻ ነበረ፡፡ ዲያብሎስ ምክንያተ ስህተት ይሆናል እንጂ ስህተት እንድናደርግ የማስገደድ ሥልጣን የለውም፡፡ እርሱን የመቃወም ሥልጣን የእኛ ነው እንጂ፡፡

«ለእግዚአብሔር እሺ በሉት፤ ሰይጣንን ግን እንቢ በሉት፤ ከእናንተም ይሸሻል፡፡ እግዚአብሔር ቅረቡት ይቀርባችሁማል» እንዲል፡፡/ያዕ. ፬፥፰/

አዳም እግዚአብሔር የታመነ አምላክ እንደሆነ ሰባት ዓመት በገነት ሲኖር ፈትኖ አውቋል፡፡ በእነዚያ "አትብላ" የሚለውን የአምላኩን ትእዛዝ በጠበቀባቸው ዓመታት እግዚአብሔር እንደነገረው ጸጋው ሳይለየው፣ ባሕርይው ጉስቁልና ሳያገኘው በሕይወት ኖሮ ነበረና፡፡ የዲያብሎስ ምክር ግን ለአዳም ሁለተኛና እንግዳ ትምህርት ነበረ፡፡ ሰባት ዓመት ፈትኖ ከሚያውቀው ከእግዚአብሔር ሕግም የሚጻረር ነበረ፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ግን አዳም በነጻ ፈቃዱ ወስኖ በዲያብሎስ ምክር ተመራ፡፡ ስለዚህ ለሰው ልጅ መሳሳት ተጠያቂው ራሱ የሰው ልጅ ነው ማለት ነው፡፡

## ፬-፮-፫ አምላክ ለምን ሰው ሆነ?

አዳምና ሔዋን ከበደል በኋላ እግዚአብሔርን እውነቱን የሰይጣንን ሐሰቱን በተረዱ ጊዜ አዝነዋል፣ አልቅሰዋል፣ ንሰሐም ገብተዋል፡፡ እግዚአብሔርም ንሰሐቸውን ተቀብሎ የሚድኑበትን ተስፋ ሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት አምላክ ሰው የሆነው እንደ ተስፋው ቃል ከፍርድ በታች የሆነውንና በሞት ቀንበር የተያዘውን የሰውን ልጅ ለማዳን ነው፡፡ ሰውን ሊያድነው የሚቻለው ከአምላክ ሌላ ማንም ወይንም ምንም አልነበረምና፡፡

### ፩ኛ. ነቢያት - ሊሆኑ አልቻሉም

ከክርስቶስ መምጣት በፊት የነበሩት ነቢያት ቀድሞውኑ ወደ ሕዝቡ ይላኩ የነበሩት ለትምህርት፣ ለተግሣጽ እና መጻኢያቱን እየነገሩ ለመምከር ነበረ፡፡ በመሆኑም በየዘሙኑ ከሚደርሰው መከራ በትምህርታቸውና በጸሎታቸው ሕዝቡን ከመዓት ከቁጣ ታድገዋል /መዝ. ፻፭፥፫/ነገር ግን አዳምን ከጥንተ አብሶ ሊያላቅቁት፣ የሞትን ዕዳ ሊከፍሉለት ግን አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም በአዳም በደል ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ሞት በአዳም ባሕርይ የተወለዱትን ሁሉ ስለገዛ ነብያት ራሳቸውም ከዚህ የሞት ዕዳ ሊከፍሉለት ግን አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም በአዳም በደል ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ሞት በአዳም ባሕርይ የተወለዱትን ሁሉ ስገዛ ነብያት ራሳቸውም ከዚህ የሞት ዕዳ ነጻ ስላልነበሩ ነው፡፡ ባለ ዕዳ ሌላኛውን ባለዕዳ ሊክሰው ዋስ ሊሆነው አይችልምና፡፡ /ሮሜ. ፭፥፲፪-፲፬/

### ፪ኛ. መላዕክት - ሊሆኑ አልቻሉም

ምክንያቱም የሞትን ፍርድ የፈረደ እግዚአብሔር ነውና ያንን ፍርድ መላዕክት ማንሣት አይቻላቸውም፡፡ በመሆኑም ከገነት አዳምን ያስወጣው በመልዕኩ ሰይፍ ገነትን ያስጠብቀ እግዚአብሔር ስለሆነ እርሱ ያስወጣውን መላዕክት ሊመልሱት አልቻሉም፡፡ መልዕክት በምልጃቸውም የሰውን ልጅ ከተፈረደበት የሞት ፍርድ ሊያድኑት አይችሉም ነበረ፡፡ ምክንያቱም የአዳም ውድቀት በምልጃ የሚመለስ ሳይሆን ቀድሞ የነበረውን ጸጋ የሚመልስለት ሞትን ሽሮ ዳግም ሕያው የሚያደርገው ያሻው ነበረ እንጂ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ጋር የተጣለ የእርሱ ከሆነ ሁሉ ጋር ስለሚጣላ አዳም ከበደል በኋላ ከመላዕክት ጋር የነበረውን ኅብረት አጥቶ ነበረ፡፡

### ፫ኛ. መሥዋዕተ ኦሪት -ሊሆን አይችልም

በኦሪት የሚሠዋው መሥዋዕት የፍጡር /የእንስሳ/ መስዋዕት በመሆኑ ፍጡርን ፍጡር ሊፈጥረው እንደማይችል ሁሉ ፍጡርን ፍጡር ማዳን አይችልምና መስዋዕተ ኦሪት ሰው ሊያድነው አልቻለም፡፡ /ዕብ. ፲፥፮-፰/ በተጨማሪም የሚሰዋው መስዋዕት /በግ፣ ፍየል…/ ሞቶ በስብሶ የሚቀር፣ የሞትን መውጊያ፣ የመቃብርን መዝጊያ ማሸነፍ የማይችል በመሆኑ ለባለዕዳው አዳም ሰጥቶ ከሞት ሊያወጣው አልቻለም፡፡ ስለዚህ አዳም ሊያድነው የሚቻለው ሁሉን ቻይ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ አዳምን ከምድር አፈር ያበጀው፣ "መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ" ብሎ የፈረደበትም እግዚአብሔር ነውና፤ እንዴት እንደ ፈጠረው እንዴትም እንደ ፈረደበት ምስጢሩን የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ሲያደርግ ማንንም አላማከረምና በብልየተ ኃጢአት ያረጀ የሰውን ማንነት አድሶ በሐዲስ ተፈጥሮ እንዴት ሊፈጥረው እንደሚችልም የሚያውቅ፣ አውቆም ማድረግ የሚችል እርሱ ብቻ ነው፡፡

*ውድ ተማሪዎች እንግዲህ ከአምላክ በቀር ሰውን ሊያድን የሚችል ማንም እንዳልነበረ ካየን አምላክስ ሁሉን ቻይ ሆኖ ሳለ ሰውን ለማዳን ሰው መሆን ለምን አስፈለገው የሚለውን ጥያቄ እንመልሳለን፡፡*

### ፩ኛ. በአዳም ላይ የተፈረደበት የሞት ፍርድ ለማጥፋት

ከላይ እንደተመለከትነው የሰውን ልጅ ከሞት ለማዳን ከአምላክ በቀር ሌላ ማንም የሚቻለው አልነበረም፡፡ ሞትን ደግሞ ለማስቀረት ካሹ ራሱ የሚሞት መሆን አለበት፡፡ ለዚያ ደግሞ ሰው መሆን ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ሞትን ከነመውጊያው ሻረው፡፡ /፩ኛ ቆሮ. ፲፭፥፶፭፤ ፩ኛ ጴጥ. ፫፥፲፰/

### ፪ኛ. በኃጢአት የረከሰውን የአዳምን ባሕርይ ለማደስ

በአዳም በደል ምክንያት የሰው ልጅ ሞት ብቻ የገጠመው ሳይሆን የንጽሕና ባሕርዩ ረከሶበታል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደመሆኑ በአምላክነት ሥልጣኑ የአዳምን ሞት አስቀርቶ ሕያው እንዲሆን ማድረግና እንዲሁ ያለ ምንም ምክንያት ከወጣበት ገነት እንዲገባ ማድረግ ይቻለዋል፡፡ ነገር ግን ይህ አለማድረጉ፡-

- ✝ ሕያውነቱ የዲያብሎስ ሕያውነት እንዳይሆን ነው፡፡ ይህም ማለት እንዲሁ ለአዳም ባሕርዩ ሳይታደስ ሕያውነትን ሰጥቶት ቢሆን ኖሮ አዳም እንደ ዲያብሎስ ባሕርዩ ርኩስ እንደሆነ ይኖር ነበረ፡፡ አስቀድሞም ጌታ እግዚአብሔር ከገነት አስወጥቶ የነበረው ከዕፀ ሕይወት በልቶ ባሕርዩ እንደረከሰበት ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር ነው፡፡
  "አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር ስለዚህ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ ደስታ ከሚገኝባት ገነት አስወጣው፡፡" እንዲል፡፡/ዘፍ. ፫፥፳፪/

- ✝ የፈራጅነት ባሕርዩን የሚቃረን እንዳይሆን ነው፡፡ እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ነው፤ ዝም ብሎ ያለቅጣት አዳምን ቢያድነው ከፈራጅነት ባሕርዩ ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡ ያጠፋ ስለጥፋቱ መቀጣት አለበትና፡፡ /፩ኛ ጴጥ. ፩፥፲፯/
- ✝ ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሔር በባሕርዩ ሁሉን ቻይ በመሆኑና ተቃዋሚ የሌለው በመሆኑ እንደ ሰው በሥልጣኑ ተጠቅሞ መሆን የማይገባውን አያደርግም፡፡ በእርሱ ዘንድ ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ነውና፡፡

ስለዚህ ከላይ እንዳየነው ፈጣሪ ሥርዓት ባለው መንገድ አዳምን ለማዳን ፈታሒ በጽድቅ /እውነተኛ ፈራጅ/ ያሰኘውን የፈራጅነት ባሕርዩን ከመሐሪነት ባሕርዩ ጋር ሳያጋጭ የረከሰውን የአዳምን ባሕርይ ለማደስ ሰው ሆነ፡፡ በጥንተ ተፈጥሮ ከፈጠረን ከእርሱ ሌላ በሐዲስ ተፈጥሮ ሊፈጥረን የሚችል ሌላ ማንም የለምና፡፡ /ቆላ. ፫፥፲/

## ፫ኛ. ሰው አጥቶ የነበረውን ምግባር ሃይማኖት የመሥራት ጸጋ ለመስጠት

አዳም ባመጣው ዕዳ ምክንያት የሰው ልጅ ለመልካም ምግባር ልምሾ ሆኖ ነበረ፡፡ ከዚህ በኋላ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን እየደራረበ በመሥራት እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ እስኪባል ድረስ ክፋትን አበዛ፡፡ ያ የመጀመሪያው በደል /ጥንተ አብሶ/ ነፍስን የሥጋ ተገዢ አደረጋት፡፡ በዚህ ምክንያት ሰው ለሥጋ አጓጊ በሆነ ነገር ሁሉ የሚሸፍ ሆነ፡፡ ሕግ ቢሰጠው ሕግን በፈጸም አልቻለም፡፡ ይልቁንም የተሰጠችው ሕግ ኃጢአትን ቆጥራ የምታስቀጣው ሆነች፡፡ ጌታ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ግን እርሱ ጋር አንድነትን መሠረትን፡፡ እርሱ ኃጢአትን ድል ነስቷልና /ማቴ. ፬፥፬-፯/ እኛም በእርሱ ኃጢአትን ድል ነስተን በምግባር ጸንተን ፍጹማን መባልን አገኘን፡፡

«በእርሱም የሚኖር ሁሉ አይበድልም፤ የሚበድልም ሰው አያየውም፣ አያውቀውምና፡፡» እንዲል፡/፩ኛ» ዮሐ. ፫፥፮/

## ፬ኛ. አባታዊ ፍቅሩን የሁሉ እረኛ መሆኑን ለመገለጽ

እግዚአብሔር በባሕርዩ ያለ ፍቅር አስገድዶት ወዶ ሰው ስለሆነ በራሱ ጥፋት ከፈጣሪው የተጣላውን እራሱ እንደ በደለኛ ክሶ ታረቀው፡፡ ልዑለ ባሕርይ ሲሆን ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ ሰው ሆኖ መከራን ተቀብሎ በመስቀል ተሰቅሎ ሞቶ ካሣን በመክፈሉ ለሰው ያለውን ልዩ ፍቅር ገልጧል፡፡

«ፍቅር ኃያል ወልድን ከዙፋኑ ሳበው እስከሞትም አደረሰው» እንዳለ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም፡፡ ሰው ሆኖ በመምጣቱም ህልውናው ጠፍቶን ከእርሱ እርቀን የነበረን ሰዎች አየነው፣ በዚህም አባትነቱን አወቀን፤ ከሞትም ስላዳነን የሥጋና የነፍሳችን እረኛ መሆኑን ተረዳን፡፡«እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበረና አሁንም ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመለሱ» እንዲል፡፡

## ፭ኛ. ሰይጣንን ድል ለመንሳት

የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር ድንቅ ረቂቅ ነው፡፡ ጌታ በቤተ-መንግሥት ሲጠበቅ በከብቶች በረት፣ በሠራዊት ታጅቦ በመኮንኖች ተከቦ ይመጣል ተብሎ ሲጠበቅ እንደ ምስኪን ደኃ ከብዙ ሰዎችና ከዲያብሎስ በተሰወረ ጥበቡ ሰው ሆነ፡፡ ይህም የሰይጣንን እኩይ ተግባር ለማጥፋት ነው፡፡ ዲያብሎስ በእባብ በሥጋዋ ተሠውሮ ምላሷን ምላስ አድርጎ አዳምንና ሔዋንን አስቷቸዋል፡፡ ክርስቶስም ይህን ሊሽር በሰው ሥጋ ተሰውሮ ተገልጧል፡፡ ጌታ እንደ ሰውነቱ ሲራብ፣ ሲጠማ፣ ሲያንቀላፋ፣ አላዋቂ መስሎ ሲጠይቅ ተመልክቶ ሰይጣን ፈጣሪነቱን ሳይረዳ ደካማ መስሎት ነበረ፡፡ በመስቀል ላይም ጌታችን «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ» ሲል ዕሩቅ ብእሲ መስሎት ሥጋውን በመቃብር ነፍሱን በሲዖል ለመቆራኘት ሲመጣ በእሳት ዛንጅር በነፋስ አውታር ወጥሮ ይዞ ሲያስለፈልፈው ነፍሳትን በነጻ እንደሚለቅ ተናግሮ እጅ ሰጥቷል፤ በመስቀሉ ሥር ድል ተነስቷል፡፡

## ፬.፭.፮ የእግዚአብሔር ወልድ ልደታት

እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት አሉት፡፡ እነዚህም፡-

**፩ኛ. ልደት ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት መወለዱ**

**፪ኛ. ልደት በዚህ ዓለም ቅድስት ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ ነው፡፡**

**"ነአምን ክልኤተ ልደታት** - ሁለት ልደታትን እናምናለን" እንዳሉ ሊቃውንቱ ባስልዮስ ሳዊሮስ፡፡ ሥጋው ቃል በዚህ ልደቱ በተዋሕዶ የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ይባላል፡፡ ይህ የጌታ ልደት አስቀድሞ ትንቢት የተነገረለት ነው፡፡ ቀጥለን ስለጌታ ልደት ከተነገሩ ትንቢቶች መካከል የተወሰኑትን እናያለን፡፡

«በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፡፡ እርሱ /የሴቲቱ ዘር/ ራስህን ይቀጠቅጣል፣አንተም ስኩናውን ትነድፋለህ፡፡» /ዘፍ. ፫፥፲፭/

በዚህ የመጽሐፍ ቃል ሴቲቱ የተባለችው ለጊዜው ሔዋን ስትሆን በፍጻሜው ግን እመቤታችን ናት፡፡ የሴቲቱ ዘር የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የሴቲቱ /የእመቤታችን/ ልጅ ጌታችን የዘንዶውን /የዲያብሎስን/ ራስ በመስቀል ቀጥቅጦታል፡፡ /ራዕ. ፳፥፪፤ ፲፪፥፫-፮፤ ገላ. ፬፥፬፤ ቆላ. ፪፥፲፬/

«እግዚአብሔርም አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድኩህ» /መዝ. ፪፥፯/

«እግዚአብሔርም አለኝ አንተ ልጄ ነህ» ያለው ተናጋሪው እግዚአብሔር ወልድ ነው፤ ቅድመ ዓለም አካል ዘእምአካል፣ ባሕርይ ዘእምባሕርይ የወለድኩህ ነህ አለኝ ሲል፡፡ «እኔ ዛሬ ወለድኩህ» ማለቱ ደግሞ ዛሬም በተዋህዶ የወለድኩህ ልጄ ነህ አለኝ ሲል ነው፡፡

በተጨማሪም የሚከተለትን የትንቢት ቃሎች ተመልከት፡፡

«ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች»/ኢሳ. ፯፥፲፬/

«ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘለዓለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡» /ኢሳ. ፱፥፮/

«አንቺም የኤፍራታ ምድር ቤተልሔም ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፍት መካከል ትሆኝ ዘንድ ታናሽ ነሽ፡፡ ነገር ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ የዘለዓለም የሆነ በእስራኤል ላይ ገዥ የሚሆን ከአንቺ ይወጣል፡፡»/ሚክ. ፭፥፪/

«እነሆ መልእክተኞዬን እልካለሁ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፣ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፣ የምትወድዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ እነሆ ይመጣል፡፡»/ሚል. ፫፥፩/

## ፬-፮-፯ የተዋሕዶ ምስጢር

*ውድ ተማሪዎች የጌታችን መድኃኒታችን ሰው የመሆኑ ነገር ታላቅ ምስጢር ነው፡፡ ይህንንም ታላቅ የሆነውን የተዋሕዶ ምሥጢር ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው እናያለን፡፡ ነገረ እግዚአብሔር በሚገደብ በሰው አእምሮ የሚመረመር አይደለም እና ፈጣሪ ምሥጢሩን ይግለጥልን! አሜን!*

አምላክ ሰው የሆነው፡-

### ፩ኛ. በመለወጥ/ውላጤ/ ነውን? - አይደለም

ምክንያቱም መለወጥ ማለት ሥጋ ወደ መለኮትነት ወይም መለኮት ወደ ሥጋነት ተለውጧል፡፡ አንዱ ጠፍቷል ማለት ነው፡፡ ምሳሌ፡- የሎጥ ሚስት ወደ ጨው ሐውልት፣ የሙሴ በትር ወደ እባብ፣ የቃና ውኃ ወደ ወይን እንደ ተለወጡ /ዘፍ. ፲፱፥፳፮፤ ዘፀ. ፯፥፲-፲፫፤ ዮሐ. ፪፥፩-፲፩/

መለኮት ወደ ሥጋ ተለወጠ ካልን ዓለም አልዳነም ያሰኛል፡፡ ፍጡር የሆነው ሥጋ ማዳን አይቻለውምና፡፡ ሥጋ ወደ መለኮት ተለወጠ ካልን መከራ ባልተቀበለ ነበረ፤ የመለኮት ባሕርይ የማይታመም ነውና፡፡ ስለዚህ ጌታችን ሰው ሲሆን ሥጋ ወደ መለኮት፣ መለኮትም ወደ ሥጋ አልተለወጡም፤ በተፀቅቦ /በመጠባበቅ/ አንድ ሆኑ እንጂ፡፡ በእግዚአብሔር ባሕርይ መለወጥ መለዋወጥ የለም፡፡ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና አልለወጥም» እንዲል፡፡/ሚል.፫፥፮/

### ፪ኛ. በሚጠት ነውን? - አይደለም

ሚጠት የቃሉ ትርጉም መመለስ ማለት ሲሆን ይህም በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ሥጋ ሆነ፤ መልሶ ቃል ሆነ ማለት ነው፡፡ ምሳሌውም እንደ ሙሴ በትር ወይም እንደ ግብጽ ውኃ ማለት ነው፡፡ /ዘፀ. ፯፥፲፯-፳፫/

### ፫ኛ. በኅድረት ነውን? - አይደለም

የዚህ ሀሳብ መነሻው በምንታዌ /ሁለትነት/ የሚያምኑ በ፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱ መናፍቃን ሐሳብ ነው፡፡ ሁለት አምላክ አለ፤ ክፉና ደግ፡፡ ክፉው አምላክ ሥጋን ጨምሮ ማንኛውም ቁስ አካል ፈጥሯል፤ ደጉ አምላክ ደግሞ እንደ ነፍስ ያሉ ረቂቃን ነገሮችን ፈጥሯል፤ ስለሆነም ሥጋ የክፉው አምላክ ፍጥረት ስለሆነ አምላክ ሥጋን አልተዋሐደም ይላሉ፡፡ በመጨረሻም በአንድ አምላክ እናምናለን የሚሉ እነ ንስጥሮስ «አምላክ ከድንግል ማርያም በተወለደው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አደረበትና የፀጋ አምላክ አደረገው እንጂ ሥጋን አልተዋሐደም» አሉ፡፡ ይህም አባባል በምሳሌ ሲገለጽ እንደ ዳዊትና ማኅደር፣ እንደ ሰይፍና ሰገባ ማለት ነው፡፡ ይህን ይዘው ሁለት ባሕርይ ነው /የሥጋና የመለኮት ባሕርይ አልተዋሐደም/፣ ሥጋን አልተዋሐደም የሚሉ መናፍቃን ዛሬም አሉ፡፡

ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም፡-

***ሀ.*** እመቤታችን ሰውን ብቻ ወለደች ካልን ከፅንሰቱ ጀምሮ በልደቱ ጊዜ የተነገረውን መሻር ይሆናል፡፡ መጽሐፍ ድንግል የወለደችው አምላክን እንደሆነ ይመሰክራልና፡፡

«ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘለዓለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡»/ኢሳ. ፱፥፮/

ለዚህም ነው ቅድስት ኤልሳቤጥ በድንግል ማርያም ማኅፀን ያለው የባሕርይ ጌታ ስለነበረ "ጌታዬ" ብላ የጠራችው፡፡ /ሉቃ. ፩፥፵፫/

**ለ.**ሁለት ባሕርይ ነው መለኮትና ሥጋ አልተዋሐዱም ካልን ሥጋ ብቻውን መከራ ተቀበለ ያሰኛል ይህን ካልን ደግሞ ሰው የራሱን መከራ ተቀብሏልና ገና አልዳነም ያሰኛል፡፡ «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸክሟል…ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ… ተጨነቀ ተሰቃየ አፉን አልከፈተም፡፡» /ኢሳ. ፶፫/ የሚለው ግን በተዋሐደው ሥጋ ታመመ ተቸገረ፣ ቆሰለ ለማለት እንደሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡

በተጨማሪም እግዚአብሔር አብ «የምወደው ልጄ እርሱ ነው» ብሎ ሲመሰክር ከእነቅዱስ ጴጥሮስ ፊት በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ የቆመውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልጄ አለው እንጂ የልጄ ማደሪያ አላለውም፡፡ /ማቴ. ፲፯፥፭/

### ፬ኛ. በቱሳሔ ነውን? አይደለም

ቱሳሔ ቅልቅል ማለት ነው፡፡ ምሳሌ፡- ማርና ውኃ፣ ወተትና ቡና፣ ወዘተ…፡፡ ማርና ውኃን ብንወስድ ሲቀላቀሉት፡- ስም ማዕከላዊ፣ መልክ ማዕከላዊ፣ ጣዕም ማዕከላዊ ይነኛል፡፡

- **ስም ማዕከላዊ፡-** የዕለቱ ብርዝ የሰነበተው ጠጅ ይባላል እንጂ ውኃ ወይም ማር አይባልም

- ❖ ***መልክዕ ማዕከላዊ፡-*** እንደ ማር ሳይነጣ እንደ ውኃ ሳይጠቁር መካከለኛ መልክ ይይዛል
- ❖ ***ጣዕም ማዕከላዊ፡-*** እንደማር ሳይከብድ እንደ ውኃ ሳይቀል መካከለኛ ጣዕም ይይዛል፡፡

በምስጢረ *ሥጋዌ ሥጋ* ወደ መለኮት መለኮትም ወደ *ሥጋ* ባሕርይ መጥቶ መካከለኛ የሆነ ነገር አልመጣም፡፡ ስለሆነም አምላክ ሰው የሆነው በቱሳሔ አይደለም፡፡

## ፫ኛ. በትድምርት ነውን? - አይደለም

ትድምርት *መደረብ፣ መደመር* ማለት ነው፡፡ ምሳሌ፡- ልብስ፣ እንጀራ፣ ወዘተ...ልብስ ቢደርቡት ይደረባል፣ ቢነጥሉትም ይነጠላል፡፡ እንጀራም እንዲሁ፡፡ መለኮትና *ሥጋ* ግን በመጀመሪያም በተዋሕዶ አንድ ሆነዋል፣ ኋላም ያለመነጣጠል ኖረዋል፣ ይኖራሉ፡፡ ሰለሆነም አምላክ ሰው የሆነው በትድምርት አይደለም፡፡

## ፬ኛ. በቡዐዴ ነውን? - አይደለም

ቡዐዴ *መለየት መለያየት* ማለት ነው፡፡ ምሳሌ፡- በቆሎና ስንዴ፤ በቆሎና ስንዴ ከተቀላቀሉ በኋላ በቆሎን ለይቶ በቆሎ ስንዴውን ለይቶ ስንዴ ማለት ይቻላል፡፡ ቃል *ሥጋን* ሲሆን ግን መለኮትንና *ሥጋን* ለያይቶ ይህ መለኮት ነው ይህ *ሥጋ* ነው አይባልምና አምላክ ሰው የሆነው በቡዐዴ አይደለም፡፡

## ፭ኛ. በተዋሕዶ ነውን? - አዎን

ሁለት አካላት አንዱ አንዱን ሳያጠፋ ሳይለውጠው፣ ያለመቀላቀል ያለመደራረብ /በተዐቅቦ/ በመጠባበቅ አንድ ሲሆኑ ተዋሕዶ ይባላል፡፡ አምላክ ሰው ሲሆን ሁለት የተለያዩ ባሕርያት ያሏቸው አካላት ተዋሕደው አንድ ባሕርይ ሆነዋል፡፡

**ባሕርይ**፡- ማለት የአካል መገኛ ሥር፣ አካል ሥራውን የሚሰራበት መሣሪያ ነው፡፡ አካል ያለ ባሕርይ ብቻውን አይቆምም፣ ባሕርይም ያለ አካል አይፈጸምም፡፡ እንደ ሥርና እንደ ግንድ /ዐፀቅ/ የተያያዙ የማይለያዩ ናቸው፡፡

- ❖ ***መለኮታዊ አካል፡-*** *ረቂቅ፣ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ እሳታዊ፣ ምሉዕ ነው፡፡*
- ❖ ***ሥጋዊ አካል፡-*** *ግዙፍ፣ ውሱን የሚዳሰስ፣የሚጨበጥ ነው፡፡*
- ❖ ***መለኮታዊ ባሕርይ፡-*** *ፊተኛና ኋለኛ፣ መጀመሪያና መጨረሻ፣ ፈጣሪ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል፣ ዘላለማዊ፣ የማይሞት የማይለወጥ የማይታመም...ነው*
- ❖ ***ሥጋዊ ባሕርይ፡-*** *መራብ መጠማት፣ መድከም፣መሞት፣...የሚስማማው ነው፡፡*

*ቃል ከሥጋ ጋር ተዋሐደ ማለት መለኮታዊ አካልና ሥጋዊ አካል መለኮታዊ ባሕርይና ሥጋዊ ባሕርይ ተወሕዱ፤ ከእመቤታችን የተወለደው ጌታችን ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው፡፡ ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደው ቃል እግዚአብሔር ወልድ ድኅረ ዓለም /ከአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን በኋላ/ በሥጋ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰለተወለደ ወልደ ማርያም /የማርያም ልጅ/ መባልን ገንዘቡ አደረገ፡፡ በተዋሕዶ ረቂቁ፣ ምልዑ መለኮት ርቀቱን ምልዓቱን ሳይለቅ በተዐቅቦ ግዙፍ ውሱን ሥጋን ሆነ፣ ግዙፉ ውሱኑ ሥጋ ግዝፈቱን ውስንነቱን ሳይለቅ በተዐቅቦ ረቂቅ ምሉዕ መለኮትን ሆነ፡፡*

*«እንተአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ ከመ ተዋህዶተ ኅፂን ምስለ እሳት» እንዲል /ቅዱስ ቄርሎስ/*

*እግዚአብሔር አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሰውም በተዋሕዶ አምላክ ሆኗል፡፡ መሆን የሁለቱም ነው፡፡ በዚህም ከላይ ቅዱስ ቄርሎስ እንደተናገረው የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆነ፡፡ ቃል የሚባለውም መለኮቱ ነው ሥጋ የሚባለው ደግሞ ትስብእቱ ነው፡፡* ***ትስብእት*** *ማለት ሰው መሆን ሰውነት ማለት ነው፡፡ ምስጢሩም በግልጽ ሲነገር ነፍስና ሥጋ ማለት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ቃል ሥጋ ሆነ ማለት ቃል ከሥጋ ጋር፣ ሥጋ ከቃል ጋር በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው፡፡ ይህንንም የተዋሕዶ ምሥጢር በብረትና እሳት፤ በነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌነት ማየት በይበልጥ ምሥጢሩን ለመረዳት ያግዛል፡፡*

***የብረትና እሳት ተዋሕዶ ለመለኮትና ሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌነት፡-***

- ✝ ብረት ከእሳት ሲገባ ብረት የእሳትን ገንዘብ ያደርጋል፡፡ */መፋጀት፣ ማበራት/* እሳትም የብረትን ገንዘብ ገንዘቡ ያደርጋል */ቅርጽ መያዝ፣ መጨበጥ፣ መዳሰስ፣ መመታት/*
- ✝ እሳት ብረቱን ተዋሕዶ እሳትነቱ እንደሚታይ ረቂቁ መለኮት *ሥጋን* ተዋሕዶ በግዙፍ ለመታየቱ ምሳሌ ነው፡፡
- ✝ እሳት ከብረት ጋር ሆኖ በመዶሻ እንደሚመታ ባሕርይውን እሳት ግን እንደማያናውጽበት መለኮትም በተዋሐደው *ሥጋ* መከራ ተቀበለ፣ ሞተ፤ ይህ ግን መለኮታዊ ባሕርይውን አላገኘውም፡፡
- ✝ ብረትም የማቃጠል ባሕርይ ከእሳት ወርሶ እሳት ይሆናል፤ ደካማ የነበረ *ሥጋም* ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ ሞትን ድል የሚያደርግ ሆኗል፡፡

**የነፍስና *ሥጋ* ተዋሕዶ ለመለኮትና *ሥጋ* ተዋሕዶ ምሳሌነት፡-**

*ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ቄርሎስ ስለነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌነት የሚከተለውን አስተምሯል፡፡*

*«የሚረዳህስ ከሆነ የትስብእትና /የሥጋና/ የመለኮትን ተዋሕዶ በእኛ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ መስለን እንነግርሃለን፡፡ እኛ በነፍስ በሥጋ የተፈጠርን ነንና፡፡ አንዱን የነፍስ ብለን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አናደርገውም፡፡ ሰው ከሁለት አንድ በመሆኑ አንድ ነው እንጂ፡፡ ከሁለቱ ባሕርያት አንድ በመሆኑ ሁለት አካል ሁለት ሰው አይባልም፡፡ በነፍስ በሥጋ የተፈጠረ ሰው አንድ ነው እንጂ፡፡ ይህንንስ ካወቅን ጌታችን*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከተዋህዶ በፊት እርስ በእርሳቸው አንድ ካልነበሩ ከተዋህዶ በኋላም ከማይለያዩ ከሁለት ባሕርያት አንድ እንደሆነ እናውቃለን፡፡» /ሃይ አበ ዘቄርሎስ ፸፰፥፲፱/

በምሥጢረ ሥላሴ እግዚአብሔር በአካል ሦስት በመለኮት አንድ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በምሥጢረ ሥጋዌ ደግሞ መለኮት ሥጋን መዋሐዱን፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ሰው መሆኑን አይተናል፡፡ ይህ ሲባል ግን መለኮት እንደ አካል ከሦስት አይከፈልም፡፡ ወይም ሦስቱም ሰው ሆኑ አያሰኝም፤ አይባልምም፡፡ ይህን ለመረዳት በምሥጢረ ሥላሴ የተመለከትነውን የኩነታት ምሥጢር በበቂ ሁኔታ መረዳት ያሻል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ነፍስ በአካሏ ከሦስት የማትከፈል አንዲት ስትሆን ሦስት ከዊን /ሁኔታዎች/ አላት፤ እነርሱም፡- ልብነት፣ ቃልነትና እስትንፋስነት ናቸው፡፡ በልብነቷ አብ፣ በቃልነቷ ወልድ፣ በእስትንፋስነቷ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡ ሰው አሳቡን ሊገልጥ ባሰበ ጊዜ የነፍስ ቃልነቷ ከሥጋዊ ምላስ ጋር ተዋህዶ ድምፁን ይሰጣል፡፡ በአንደበትም በተገለጠ ጊዜ ከልብና ከእስትንፋስ አይለይም፡፡ ልብ፣ ቃልና እስትንፋስ በተዋህዶ እያሉ ቃል ሥጋዊ ምላስን ተዋህዶ በተገለጠና ድምፁን በሰጠ ጊዜ ይህ የቃልነት ከዊን ልብን እስትንፋስን ወደ ቃልነት ሊለውጣቸው አይችልም፡፡ ስለዚህ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ በቃልነቱ ከዊን ሰው ሲሆን የቃል ሰው መሆን መለኮትን እንደ አካላት አይከፍለውም፤ አብ መንፈስ ቅዱስም ሰው ሆኑ አያሰኝም፡፡

### የተዋሕዶ ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ

### *ሀ. ዕፀ ጳጦስ ዘሲና*

«የእግዚአብሔርም መልአክ ለሙሴ በእሳት ነበልባል በቁጥቋጦ መካከል ታየው፤ እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ፡፡» /ዘፀ. ፫፥፪/

ቅጠልና እሳት አንድ ሆነው ተዋሕደው እሳቱ ቅጠሉን ሳያቃጥል ቅጠሉ እሳቱን ሳያጠፋ እሳት እሳቱን ቅጠልም ቅጠልነቱን እንደያዘ፣ ዳሩ ግን በተዋህዶ አንድ ሆኖ ታይተዋል፡፡ ይህም አካላዊ ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ መለኮት ሥጋን አልመጠጠውም፣ አላጠፋውምና፣ ሥጋም ተለውጦ መለኮት አልሆነምና፣ መለኮት መለኮትነቱን ሥጋም ሥጋነቱን ሳይለቅ በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡

### ለ. ሱራፌ በጉጠት የያዘው ፍሕም

«ከሲራፌልም አንዱ ወደ እኔ ተላከ፤ በእጁም ከመሰዊያው በጉጠት የወሰደው ፍሕም ነበረ፡፡ አፌንም ዳሰሰበትና እነሆ ይህ ከንፈሮችህን ነክቷል በደልህም ከአንተ ተወገደ ኃጢአትህም ተሰረየልህ አለኝ፡፡» /ኢሳ.፮፥፪/

ፍሕም የሥግው ቃል የጌታችን ምሳሌ ነው፡፡ ፍሕም የከሰልና የእሳት ውሕደት ነው፡፡ እሳት የመለኮት ከሰል የሥጋ ምሳሌ ነው፡፡ ፍሕሙ ባለመታዘዝ ምክንያት ለምጻም የሆነውን ኢሳይያስን ከኃጢአቱ እንዳነጻው በተዋሕዶ የተገለጸው ጌታችንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሶ የወደቀውን አዳምን ከውድቀቱ አንስቶ ከርኩሰቱ ቀድሶ ወደ ቀደመ ግብሩ የመመለሱ የዚያ ምሳሌ ነው፡፡

## ፬-፮-፫ የክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው፡፡ ይህንን በሚከተለት ሦስት መንገዶች ዘርዝረን እናያለን፡፡

### ፩ኛ. ስለኢየሱስ ክርስቶስ ነቢያት ሲናገሩ እግዚአብሔር ብለው ጠርተውታል፡፡

ሀ. ልበ አምላክ ዳዊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኋላ ወደ ሰማይ ማረጉን አስመልክቶ በትንቢት ሲናገር ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል፡፡

**ትንቢት፡-** «እግዚአብሔር በእልልታ፣ ጌታችንም በመለከት ድምፅ አረገ»/መዝ. ፵፮፥፬-፭/

ለ. ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ስለ ምጽአተ ክርስቶስ ሲናገር እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል፡፡

**ትንቢት፡-** « እነሆ ጌታ እግዚአብሔር በኃይሉ ይመጣል፣ ክንዱም ይገዛል፡፡ እነሆ ዋጋው ከእርሱ ጋር ሥራውም በፊቱ ነው» /ራዕ. ፵፥፲/

**የትንቢት ፍጻሜ፡-** « እኔ ኢየሱስ...እነሆ ፈጥኜ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡ አልፋና ኦሜጋ ቀዳማዊና ደኃራዊ መጀመሪያና መጨረሻው እኔ ነኝ»/ራዕ. ፳፪፥፲፪ ና ፲፮/

ሐ. ነቢየ እግዚአብሔር ዘካርያስም በተመሳሳይ ሁኔታ ክርሰቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል

**ትንቢት፡-** «አምላኬ እግዚአብሔርም ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል፡፡» /ዘካ. ፲፬፥፭/

**የትንቢት ፍጻሜ፡-** "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር በሚመጣ ጊዜ..." /፩ተሰ ፫፥፲፪/

### ፪ኛ. ለእግዚብሔር ብቻ የሚነገሩ ለክርስቶስም ተነግረዋል

***ሀ. ፊተኛና ኋለኛ፡-*** ከእግዚአብሔር በቀር ከዘመናት በፊት የነበረ እስከ ዘለዓለምም የሚኖር የለምና ከእርሱ ሌላ ፊተኛና ኋለኛ መባል የሚገባው የለም፡፡

"የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር የሚቤዥም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡፡ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም፡፡" እንዲል፡፡ /ኢሳ. ፵፬፥፮፤ዘፀ.፫፥፲፬/

ኢየሱስ ክርስቶስም እኔ ፊተኛና ኋለኛ ነኝ ማለቱ እግዚአብሔርነቱን ያስረዳል፡፡

«ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበረሁ እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ሕያው ነኝ፡፡» /ራዕ. ፩፥፲፯/

**ለ. አምላክ፡-** ከእግዚአብሔር በቀር የባሕርይ አምላክ የለም «ከእኔ በፊት አምላክ አልነበረም ከእኔም በኋላ አይኖርም፡፡» እንዲል /ኢሳ. ፵፫፥፲/

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር በመሆኑ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ መሆኑ በመጻሕፍት ተመስክሯል፡፡

«እውነተኛም በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንኖራለን፡፡ እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው፡፡» /፩ዮሐ. ፭፥፳/

«ከእርሱም ክርስቶስ በሥጋ ተወለደ፤ እርሱም ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘለዓለም ቡሩክ አምላክ ነው፣ አሜን፡፡» /ሮሜ. ፱፥፭/

«ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘለዓለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡» /ኢሳ. ፱፥፮/

***ሐ. የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ፡-*** እግዚአብሔር የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ ነው፡፡

«አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶች ጌታ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራውም በፍርድ የማያዳላ መማለጃ የማይቀበል ነውና» /ዘዳ. ፲፥፲፯/

ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር እንደመሆኑ በዚሁ ስም ተጠርቷል፡፡

«በልብሱ ላይና በጎኑ ላይ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሚል ስም ተጽፎበታል፡፡» /ራዕ. ፲፱፥፲፮/

**፫ኛ. በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክርስቶስ እግዚአብሔር ተብሏል፡፡**

«እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ-ክርስቲያንን እንድትጠብቁ...»/ሐዋ. ፳፥፳፰/

በደሙ ፈሳሽነት አማናዊት ቤተ-ክርስቲያንን የመሠረተው በተለየ አካሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ፍጹም ሰው የሆነው ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ እግዚአብሔር ተብሎ መጠራቱን ልብ ይሏል፡፡

በአጠቃላይም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው፡፡ ሥጋ በተዋሕዶ መለኮት የባሕርይ አምላክነትን ገንዘቡ አድርጓል፤ መለኮትም በተዋሕዶ ሥጋ የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጓል፡፡ ይህም በሚከተሉት ምንባባትና ታሪኮች ተመስክሯል፡፡

«ሊቀ ካህናቱም..የቡሩክ ልጅ ክርሰቶስ አንተ ነህን? አለው፡፡ ጌታችን ኢየሱስም አዎን እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ተቀምጦ በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ አለው፡፡» /ማር. ፲፬፥፷፩/

በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ በመሆኑ ተይዞ ለፍርድ የቀረበው ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በመጨረሻው ቀንም ለሁሉ እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ለመክፈል የሚመጣውም ያው እርሱ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነውና፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፪ ከቁጥር ፩ እስከ ፲፪ በተጠቀሰው የቃና ሠርግ ላይ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ ወደ ሠርጉ የተጠራው፤ ፍጹም አምላክ እንደመሆኑም ውኃውን ወይን ያደረገው አንድ እርሱ ሥግው ቃል ክርሰቶስ ነው፡፡

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ከቁጥር ፳፯ ላይ የተመዘገበው ታሪክ ላይ በመርከቡ የውስጠኛው ክፍል ተኝቶ የነበረው፤ ተነስቶም ነፋሳትንና ማዕበላትን የገሰጸው አንዱ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ መተኛት፣ መንቀሳቀስ የሰውነት ሥራ፤ ነፋሳትንና ማዕበላትን መገሠጽ (ጸጥ) ማድረግ የአምላክነት ሥራ ነው፡፡ ሠሪያቸው ግን አንድ ክርስቶስ ነው፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፱ ቁጥር ፯ ላይ ከተወለደ ጀምሮ ዕውር ለነበረው ሰው ምራቁን እንትፍ ብሎ በምድር አፈር ለውሶ የዓይኑን ብርሃን እንደመለሰለት እናነባለን፡፡ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ ምራቅን እንትፍ አለ፤ ፍጹም አምላክ እንደመሆኑም በምራቁ በደረቅ ግንባር ላይ ዐይንን ሠራ፡፡ ይህም ትስብእት /ሰውነት/ መለኮትን ተዋሕዶ የመለኮትን ባሕርይ ማድረጉን ያሳያል፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፳ ከቁጥር ፲፱ እስከ ፳፱ ላይ በተጻፈው ታሪክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዘጋው በር በርቀት ገባ፤ ገብቶም እዩኝ ዳሱኝ አለ፡፡ በርቀት ***/ጠብቆ ይነበብ/*** በዝግ በር የገባው መለኮት ነው እንዳይባል እዩኝ ዳሱኝ ብሏል፤ መለኮት በባሕርዩ አይታይም አይዳሰስምና ይህ አይሆንም፡፡ እዩኝ ዳሡኝ ያለ ሥጋ ነው እንዳይባል ሥጋ በርቀት በተዘጋ በር ለመግባት አይችልም፡፡ ይህ የሆነው ግን በተዋሕዶ፡- ሥጋ የመለኮትን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ በርቀት ገብቷል፤ መለኮትም የሥጋን ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ በተዋሕዶተ ሥጋ ታይቷል፣ ተዳሷል፡፡ በርቀት የገባ፣ እዩኝ ዳሱኝ ያለም አንድ እርሱ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

### ፬-፮-፱ የእግዚአብሔር የማዳን ጉዞ ከልደት እስከ ትንሣኤ

ውድ ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ሥር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልደቱ እስከ ትንሣኤው በፈጸመው የካሣነት ሥራ እንዴት የሰው ልጅ እንደተቤዠ እንመለከታለን፡፡

- ✝ **ልደት፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀቱም ድንግል ከእመቤታችን ተወለደ፡፡ /ማቴ. ፩፥፳፫/፤ ኢሳ. ፯፥፲፬/፡፡ ይኸም ከኀቱም መሬት ተገኝቶ የተሳሳተውን አዳምን ሊቤዠ ነው፡፡ *መርገመ ሥጋ መርገመ* ነፍስ ከሌለባት ከንጽሕት ድንግል ከእመቤታችን መወለዱ መርገም ካልደረሰባት ከንጽሕት ምድር ተገኝቶ የሳተውን አዳምን ሊያድን ነው፡፡ ሲወለድም በከብቶች በረት በእንስሶች መካከል ተኛ /ሉቃ. ፪፥፯/፡፡ ይህም ከዓለመ መላእክት ተሰዶ በእንስሶች መካከል የተገኘ አዳምን ለማዳን ነው፡፡
- ✝ **ስደት፡-** ያለ በደሉ መድኃኒዓለም ክርስቶስ የገነት ምሳሌ ከሆነች ከነዓን የሲኦል ምሳሌ ወደ ሆነች ግብጽ ተሰድዷል /ማቴ. ፪፥፲፫-፳፫/ ይህም በበደሉ ምክንያት ከገነት ወደ ሲዖል የተሰደደውን አዳምን ሊያድን ነው፡፡
- ✝ **ሕግ ጠባይዓዊና መጽሐፋዊን መፈጸም፡-** ሕግ ጠባይዓዊ የሚባለው የሰውንትንና የተፈጥሮን ሕግጋት በመጠበቅ ከመጸነስና ከመውለድ ጀምሮ ቀስ በቀስ ማደግ መከራ መቀበልን፣ መብላት፣ መጠጣትን፣ ወዘተ ያጠቃልላል፡፡ ይህንን ከኃጢአት በቀር በየደረጃው ፈጽሞታል፡፡ ሕግ መጽሐፋዊ የሚለው ደግሞ ሕገ ኦሪትን እየፈጸመ ማደጉን ያሳያል፡፡ በስምንተኛው ቀን መገረዝን፣ በ፵ኛው ቀን ቤተ መቅደስ መግባትን፣ በዓመት ሦስት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድን፣ ወዘተ ያጠቃልላል /ሉቃ. ፪፥፳፩-፶፪/፡፡ ጌታ ሕግን ሁሉ የፈጸመው እኛ ሕግ አፍራሾችን እንደ ሕግ ፈጻሚዎች ሊቆጥረን ነው፡፡ ይህንንም በማድረጉ በሕግ አፍራሽነታችን ከሚመጣብን ፍርድና ኩነኔ ነጻ አውጥቶናል፤ አድኖናልም፡፡ /ሮሜ. ፲፥፯-፩/
- ✝ **ጥምቀት፡-** መድኃኒዓለም ክርስቶስ በ፴ ዘመኑ ተጠምቋል፡፡ /ማቴ.፫፥፫-፲፯/ በዚህም የ፴ ዘመን ጐልማሳ ሆኖ የተፈጠረውን፣ በምክረ ከይሲ ተታሎ ልጅነቱን ያጣውን አዳምን አድኖታል፡፡
- ✝ **ፈተናን ድል መንሳት፡-** ጌታችን «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ»ብሎ በመብል ድል ለተነሳው አዳም ፈቃደ ሥጋን አጠፋለት /ማቴ. ፬፥፬/፡፡ ጌታችን ከከተማ ርቃ በምትገኝ በገዳመ ቆሮንቶስ መጾሙ ዲያብሎስ ከምድር ተለይታ በምትገኝ ገነት በመብል ድል ያደረገውን አዳምን ሊያድነው ያሳተውን ዲያብሎስን ድል ሊያደረግ ነው፡፡
- ✝ **ስቅለት፣ ሞትና ትንሣኤ፡-** ጌታችን ራቁቱን በመልዕልተ መስቀል ተሰቀለ፡፡ /ማቴ. ፳፯፥፴፫/፤ ይህም ሕግ ጥሶ ከጸጋ የተራቆተው አዳምን ሊያድን ነው፡፡ እጅና እግሩ በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፤ ይህም እጅና እግሩ ወደ እፀ በለስ ያመሩትን አዳምን ሊያድን ነው፡፡ የማይሞተው ሞተ /ማቴ. ፳፯፥፶/፤ ይህም በአዳምና በልጆቹ ነግሶ የነበረው ሞትን ይሽር ዘንድ ነው፡፡ በመስቀሉ ያስገኘውንም ታላቅ ድል በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ሲነሳ አረጋግጦታል፡፡

«ሞት ሆይ እንግዲህ መውጊያህ ወዴት አል? መቃብር ሆይ አሸናፊነትህ ወዴት አለ?" ተብሏል፡፡» /፩ቆሮ. ፲፭፥፶፭-፶፯/

## ፬.፯ ምሥጢረ ጥምቀት

### ፬-፯-፩ ትርጉም

*ውድ ተማሪዎች በአዕማድ ምሥጢራት ትምህርታችን በሰስተኛ ደረጃ የምንገኘው ምሥጢር ጥምቀትን ነው፡፡ መልካም ቆይታ*

ጥምቀት ማለት አጥመቀ አጠመቀ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የሚወጣ ማጥመቅ መጠመቅ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሳቢ ዘር ነው፡፡ መጠመቅ ማለት መነከር፣ መዘፈቅ፣ ውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ማለት ነው፡፡

ጥምቀት ማለት ከአዳም የወረስነውን ኃጢአትና እኛም የበደልነውን በደል ደምስሶ በመንፈስ ቅዱስ እንደገና እንድንወለድ የሚያደርገን የመጀመሪያው የጸጋና የእምነት ምሥጢር ነው፡፡ በአጠቃላይ ምስጢረ ጥምቀት የሥላሴ ልጅነት የሚሰጥበትና የኃጢአት ሥርየት የሚገኝበት ምሥጢር ነው፡፡

### ፬-፯-፪ አጀማመሩ

ጥምቀትን ጌታ መሥርቷል፡፡ በዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ጥምቀትን ከመሠረተም በኋላ እኛም እንድንጠመቅ በተግባር አስተምሮ አርአያ ሆኖናል፡፡ ስለዚህም ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር መንግስተ ሰማያት እንደማይገባ ተደንግጓል /ዮሐ. ፫፥፭/፡፡ ሐዋርያትንም በዓለም ዞረው ወንጌለ መንግሥቱን ሲሰብኩ ያመኑትን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ አዟቸዋል፡፡ /ማቴ. ፳፰፥፲፰-፲፱/ ይህም የሆነው ጥምቀት የልጅነት ጸጋን ስለሚያሰጥ ሌሎችን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመሳተፍና የቤተ-ክርስቲያን አባል ለመሆን የመጀመሪያው መግቢያ በር በመሆኑ ነው፡፡

### ፬-፯-፪ አስፈላጊነቱ

#### (፩ኛ). ድኅነትን ለማግኘት

ጥምቀት ለድኅነት ከሚያስፈልጉ ምስጢራት አንዱ ነው፡፡ ሰው ያለጥምቀት ከፍርድ ነጻ መሆንና የእግዚአብሔር መንግሥት መውረስ አይቻለውም፡፡ «ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» /ማር. ፲፮-፲፯/

#### (፪ኛ). ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ደግሞ ለመወለድ

ሰው ከወላጅ አባቱና እናቱ በሥጋዊ ልደት እንደሚወለደው ሁሉ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅጸነ ዮርዳኖስም በመንፈሳዊ ልደት በጥምቀት አማካኝነት ዳግም ሊወለድ ያስፈልገዋል፡፡ በዚህም ከእግዚአብሔር ልጅነትን በጸጋ አግኝቶ መንግስቱን ለመውረስ የተዘጋጀ ይሆናል፡፡

«...እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛም ያልተወለደ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት ለማየት አይችልም አለው፡፡ ኒቆዲሞስም ሰው ከሸመገለ በኋላ ዳግመኛ መወለድ እንደምን ይችላል? ዳግመኛ ይወለድ ዘንድ ወደ እናቱ ማኅጸን ተመልሶ መግባት ይችላልን? አለው፡፡ ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡» እንዲህ፡፡/ዮሐ. ፫፥፫-፯/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በጥምቀት ስለሚሆነው አዲስ ልደት እንዲህ ብሏል፡፡

«ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ ዳግም ልደትንና በመንፈስ ቅዱስ መታደስን በሚያሰጥ ጥምቀት በምሕረቱ አዳነን እንጂ በጽድቅ ሥራችን አይደለም፡፡»/ቲቶ ፫፥፭፤ ኤፌ. ፭፥፳፮/

በአጭሩ በጥምቀት ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልደት መወለድን /ልጅነትን/ እናገኛለን፡፡

### (፫ኛ). የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት

ጥምቀት ኃጢአትን ትደመስሳለች፡፡

«...ንስሐ ግቡ ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ ኃጢአታችሁም ይሠረይላችኋል፡፡» እንዲል፡፡ /ሐዋ. ፪፥፴፯-፴፰/

«(ሳውል እንዲህ እየተባለ) ተነሥና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፣ ከኃጢአትህም ታጠብ፡፡» /ሐዋ. ፳፪፥፲፮/

«ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋልም» /፩ቆሮ ፮፥፲፩/

ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያንም በሃይማኖታዊ ድንጋጌያቸው ላይ « ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት - ኃጢአትን በምታሠተሠርይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን» ብለዋል፡፡ /ጸሎተ ሃይማኖት/

### (፬ኛ). ከጌታ ሞትና ትንሣኤ ጋር ለመተባበር

«በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችኋል፤ በእርሷም ከሙታን ለይቶ ባስነሣው በእግዚአብሔር ረዳትነትና በሃይማኖት ከእርሱ ጋር ተነስታችኋል፡፡» እንዲል፡፡ /ቆላ. ፪፥፲፪/

በጥምቀትም ከጌታ ጋር መቀበር ማለት በጥምቀት ለኃጢአት ሥራ ምውት መሆን ማለት ነው፡፡ በጥምቀት ከጌታ ጋር መነሳት ማለት ደግሞ በጥምቀት ለጽድቅ ሥራ ሕያው መሆን ማለት ነው፡፡

«እንዲሁ እናንተም ራሳችሁን ለኃጢአት ምውታን አድርጉ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም ለእግዚአብሔር ሕያዋን ሁኑ፡፡» እንዲል፡፡ /ሮሜ ፮፥፲፩/

ይህንንም አንድ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር የሞቱም የትንሣኤውም ተካፋይ መሆኑን በሥርዓተ ጥምቀቱ ያሳያል፡፡

- ከውኃው ውስጥ መግባቱ ከጌታ ጋር መሞቱ መቀበሩ «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን እኛ ሁላችን በሞቱ እንደተጠመቅን ሁላችሁ ይህን ዕወቁ...በሞቱም እንመስለው ዘንድ ከእርሱ ጋር በጥምቀት ተቀበርን» እንዲል፡፡ /ሮሜ. ፮፥፫-፬/
- ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ማለቱ ጌታ በመቃብር ሦስት ቀንና ሌሊት መቆየቱን ያመለክታል፡፡
- በሦስተኛው ከውኃው መውጣቱ በሦስተኛው ቀን ከመቃብር ሞትን ድል አድርጎ ለመነሳቱ ምሳሌ ነው፡፡
  «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ ጌትነት ከሙታን እንደተነሣ እኛም እንደ እርሱ በአዲስ ሕይወት እንኖራለን፡፡ በሞቱም ከመሰልነው በትንሣኤውም እንመስለዋለን፡፡ ተብሏልና» /ሮሜ. ፮፥፭/

### (፭ኛ). አዲስ ሕይወት ለማግኘት

በኃጢአት ምክንያት ያደፈው ሰውነታችን የሚታደሰውና አዲስ ሕይወትን የምናገኘው በጥምቀት ነው፡፡ /ሮሜ. ፮፥፬/

### (፮ኛ). ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን

ከብልየተ ኃጢአት የታደሰውን፣ ከመርገም የጸዳውን አዲሱን ሰውነት የምንለብሰውና የክርስቶስ ተከታዮች የምንሆነው በጥምቀት ነው፡፡ «በክርስቶስ የተጠመቃችሁ እናንተማ ክርስቶስን ለብሳችኋል፡፡» እንዲል /ገላ. ፫፥፳፯/

### (፯ኛ). የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን

ግዝረት ለሕዝበ እስራኤል የአብርሃም ቃል ኪዳን ተሳታፊዎች እንዳደርጋቸው ጥምቀትም ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ጸጋ ተካፋይ ያደርጋል፡፡ /ቆላ. ፪፥፲፩-፲፫/

## ፬-፯-፫ የጥምቀት ምሳሌዎች

**፩ኛ. የኖኅ መርከብ ታሪክ /ዘፍ. ፯፥፲፯/**

በኖኅ ዘመን ሰው ሁሉ ምግባር ሃይማኖት አጥቶ እግዚአብሔርን በኃጢአቱ ምክንያት ያሳዘነበት ወቅት ነበረ፡፡ በዚህም ምክንያት ፍጥረት ሁሉ በጥፋት ውኃ ሲቀጣ በመርከቢቱ ውስጥ የነበሩት ኖኅና ቤተሰቡ ለዘር ከቀሩት እንስሳት ጋር ብቻ ተርፈዋል፡፡ ይህም ምሳሌ ነው፡- ኖኅና ቤተሰቡ የምዕመናን፣ መርከብ የቤተ-ክርስቲያን፣ ውኃው የጥምቀት፡፡ ክርስቶስ በሠራት መርከብ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ በጥምቀት የጸጋ በር የገባ ምዕመን ይድናል፤ ያልገባ ሁሉ ግን መዳንን አያገኛምና፡፡

« ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፋሳት በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲሰራ በኖህ ዘመን የእግዚአብሔር ትዕግስት በዘገየ ጊዜ ቀድሞ ከደውት ለነበሩት ሰበከላቸው፡፡ አሁንም እኛ በዚያው አምሳል በጥምቀት ያድነናል፡፡»/፩ኛ. ጴጥ. ፫፥፳-፳፩/

**፪ኛ. ግዝረት**

ግዝረት የጥምቀት ምሳሌነቱ እንደሚከተለው ነው፡፡

- ግዝረት የእግዚአብሔር ሕዝብ መለያ ምልክት ነበረ፤ የአብርሃም ልጅነትን የእስራኤል ወገንነትንም ያሰጥ ነበረ፡፡ እንደዚሁም ጥምቀት የሥላሴ ልጅነትን የክርስቲያን ወገንነትን ያሰጣል፡፡
- ያልተገረዘም ከሕዝቡ ተለይቶ እንዲጠፋ ታዞ ነበረ፡፡ /ዘፍ. ፲፯፥፲፬/ እንደዚሁም ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገባ ታውጇል፡፡ /ዮሐ. ፫፥፫/
- ግዝረት ከአካል ላይ ሥጋን ቆርጦ መጣል ነው፡፡ ጥምቀትም የኃጢአትን ሰንኮፍ ከሕይወት ቆርጦ መጣል ነው፡፡
- ግዝረት ከአንድ ጊዜ በላይ አይሆንም፣ አይደገምም፡፡ ጥምቀትም የማትደገም የማትከለስ አንዲት ናት፡፡ /ኤፌ. ፬፥፭/ ይህም የሆነው ጌታ የሞተው አንድ ጊዜ ነውና ጥምቀቱም ከሞቱ ጋር መተባበር ነውና አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማል፡፡
- በመገረዝ ጊዜ ደም ይፈሳል፡፡ በጥምቀትም በክርስቶስ ደም የተዋጁ ክርስቲያኖች ከኃጢአት የታጠቡበትን የጌታን ደም ያገኙበታል፡፡

ስለዚህ ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ሐዋርያው እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡

«የኃጢአትን ሰውነት ሽለፊት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በሰው እጅ ባልተደረገ መገረዝን በእርሱ ሆናችሁ ተገረዛችሁ፡፡ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችኋል፤ በእርሷም ከሙታን ለይቶ ባስነሣው በእግዚአብሔር ረዳትነትና በሃይማኖት ከእርሱ ጋር ተነስታችኋል፡፡» /ቆላ. ፪፥፲-፲፪/

**፫ኛ. የእስራኤል ባህረ ኤርትራን ማቋረጥ /ኢያ. ፫፥፲፭/**

ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ተለቀው ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞአቸውን የጀመሩት የኤርትራ ባሕር ለሁለት ተከፍሎላቸው ነው፡፡ ያሳድዷቸው የነበሩት ፈርዖንና ሠራዊቱ ግን በዚያው በኤርትራ ባሕር ሰጥመው ቀርተዋል፡፡ የኤርትራን ባሕር መሻገር ለእስራኤል ሕይወትን፣ ደስታን፣ ነጻነትን ሲያጐናጽፍ ለፈርአንና ሠራዊቱ ግን ሞትን አስከትሎባቸዋል፡፡ ጥምቀትም ለክርስቲያኖች ከፍዳ፣ ከሞት ነጻ መሆንን፣ የሥላሴ ልጅነትን ሲያሰጥ አጋንንትን ግን ድል ይመቱበታልና የዚያ ምሳሌ ነው፡፡

«ወንድሞቻችን ሆይ፡- አባቶቻችን ሁሉ ደመና እንደጋረዳቸው ሁሉም በባሕር መከከል አልፈው እንዲሄዱ ልታውቁ እወዳለሁ፡፡ ሁሉንም ሙሴ በደመናና በባሕር አጠመቃቸው፡፡» እንዲል፡፡ /፩ኛ ቆሮ. ፲፥፩-፪/

**፬ኛ. የኢዮብና የንዕማን በዮርዳኖስ ውኃ ተጠምቀው መዳናቸው /፪ኛ ነገ. ፭፥፲፬/**

ኢዮብ ከደዌው በዮርዳኖስ ውኃ ተጠምቆ ድኗል፡፡ ንዕማንም ከለምጹ በዮርዳኖስ ውኃ ተጠምቆ ነጽቷል፡፡ እኛም ከኃጢአት ደዌ የምንነጻውና ያረጀው ሕይወታችን የሚታደሰው በጥምቀት ነውና የዚያ ምሳሌ ነው፡፡

ስለ ጥምቀት ግን ታሪክና ምሳሌ ብቻ ሳይሆን ትንቢትም ተነግሯል፡፡

«ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ከርኩሰታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ፡፡» /ሕዝ. ፴፮፥፳፭/

በተጨማሪም የሚከተሉት ስለጥምቀት የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው፡፡ /መዝ. ፻፲፫፥፫፤ ሕዝ. ፵፯፥፩-፲፪/

**፬-፯-፬ የእግዚአብሔር ወልድ ጥምቀት**

*ውድ ተማሪዎች ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል፡፡ ይህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ከአይሁድና ከዮሐንስ ጥምቀት ይለያል፡፡ ጥምቀተ አይሁድ ትእዛዘ ኦሪትን ለጣሰ ሰው ይደረግ የነበረ ነው /ዘሌ. ፮፥፲፰/፡፡ የዮሐንስ ጥምቀት ደግሞ የንስሐ ነበረ፡፡ /ማቴ. ፫፥፩-፮/ ጌታችን የተጠመቀው ግን እንደ አይሁድ ሥርዓት ለመንጻት፣ እንደ ዮሐንስም ጥምቀት ለሥርየት ኃጢአት አልነበረም፡፡ ታዲያ ጌታ ለምን የተጠመቀ ይመስላችዋል?*

ጌታችን ኢየሱስ ከረስቶስ የተጠመቀው፡-

**፩ኛ. ትሕትናን ለማስተማር፡-** ወደ አገልጋዩ /ፍጡሩ/ ሄዶ በእርሱ እጅ መጠመቁ መምህረ ትሕትና መሆኑን ይገለጣል፡፡

**፪ኛ. አርአያ ለመሆን፡-** በጥምቀት ከእግዚአብሔር ለምንወለድ ለእኛ አብነት ሊሆነን፤ እርሱ ተጠምቆ ተጠመቁ ሊለን ነው፡፡

**፫ኛ. ዲያብሎስ በዮርዳኖስ የደበቀውን የዕዳ ደብዳቤ ሊቀድልን፡-** ዲያብሎስ «አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፣ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ - አዳም የዲያብሎስ ባሪያ፣ ሔዋን የዲያብሎስ ገረድ» የሚል ደብዳቤ ጽፎ አንዱን በሲኦል አንዱን በዮርዳኖስ ወንዝ ደብቆት ነበረ፡፡ የአዳምና የልጆቹ ቤዛ ክርስቶስ በሲኦል ያለውን በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ አጥፍቶታል፡፡ በዮርዳኖስ የተጣለውን ደግሞ በጥምቀቱ ጊዜ እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ እንደ ሰም አቅልጦ ደምስሶታል፡፡ ሊቁ ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ይህን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፡፡

« ወነስተ ምክሮ ለጸላኢ ወሠጠጠ መጽሐፈ ዕዳሆሙ ለአዳም ወለሔዋን - የጠላትን ምክሩን አፈረሰበት፣ የአዳምንና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤአቸውን ቀደደላቸው» /የሰኞ ውዳሴ ማርያም/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል፡፡

«ከባላጋራችን የተነሣ በትእዛዝ የተጻፈውን የዕዳችንን ደብዳቤ ደመሰሰልን» /ቆላ. ፪፥፲፫-፲፭/

**፬ኛ. አንድነቱን ሦስትነቱን ለመግለጥ፡-** በጌታ ጥምቀት "ሥውር የነበረው የሥላሴ ምስጢር ገሃድ ሆኗል፡፡" /በገጽ 49 የተሰጠው ማብራሪያ ተመልከት/

**ጌታ ጥምቀቱን ለምን በዮርዳኖስ አደረገው?**

**፩ኛ. ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ**

ልበ አምላክ ዳዊት ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ ጥምቀቱን ሲፈጽም የሚሆነውን አስቀድሞ በትንቢት ቃል ተናግሮ ነበረ፡፡ ይህንን ትንቢት ለመፈጸምም ጌታችን በዮርዳኖስ ተጠምቋል፡፡

"ባሕር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ፡፡ ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ አንቺ ባሕር የሸሸሽ አንተም ዮርዳኖስ ወደ ኋላህ የተመለስህ ምን ሁናችሁ ነው እናንተም ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችስ እንደ በጎች ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ ከያዕቆብ አምላክ ፊት" /መዝ. ፻፲፫፥፫-፯/

**፪ኛ. ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ**

ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ ነው፣ ዝቅ ብሎ በዮርና በዳኖስ ተለይቷል፡፡ ዮር በእስራኤል በኩል፣ ዳኖስ ደግሞ በአሕዛብ በኩል ነው፡፡ ዝቅ ብሎ ተገናኝቷል፣ በግንናኛው ጌታ ተጠምቋል፡፡

- ❖ ነቁ አንድ መሆኑ ሰው ሁሉ የአንዱ አዳም ልጅ የመሆኑ ምሳሌ
- ❖ ዝቅ ብሎ መለያየቱ በእስራኤል በኦሪት /በግዝረት/፣ አሕዛብ በጣኦት /በቁልፈት/ የመለያየታቸው ምሳሌ
- ❖ ወረድ ብሎ መገናኘቱ ጌታም በዚያ መጠመቁ ሕዝብና አሕዛብን በጥምቀቱ አንድ የማድረጉ ምሳሌ ነው

ከዚህ በተጨማሪም፡-

- ❖ ኢዮብ ከደዌው የዳነው ንዕማንም ከለምጹ የነጻው በዮርዳኖስ ውኃ ተጠምቀው ነበረ፡፡ ይህም ኢዮብ/ንዕማን የአዳም፣ ደዌ/ለምጽ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ፣ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ /፪ነገ. ፭፥፲፬/
- ❖ እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል፡፡ ምዕመናንም ተጠምቀው ገነት መንግስተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ነው፡፡
- ❖ ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ብሔረ ሕያዋን አርጓል፡፡ ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግስተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ነው፡፡

**፫ኛ. የዕዳ ደብዳቤዎችን ይደመስስ ዘንድ**

በገጽ 52 የተሰጠውን ማብሪራያ ተመልከት፡፡

**ጌታ ለምን በ፴ ዘመኑ ተጠመቀ?**

፩ኛ. አዳም የ፴ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በ፵ ቀን ያገኛትን ልጅነት አስወስዶ ነበረና የአዳምን ልጅነት ለማስመለስና ልጅነትም የምትሰጠው በጥምቀት መሆኑን ለማረጋገጥ በ፴ ዘመኑ ተጠምቋል፡፡

፪ኛ. ደግን ነገር መንፈሳዊን ነገር ባሰባችሁ ጊዜ ከ፴ ዓመት በላይ እንጂ ከ፴ ዓመት በታች አይሁን ሲል ሥርዓት ሲሠራልን ነው፡፡

**ጥምቀቱን ለምን በውኃ አደረገው?**

፩ኛ. ጌታችን ጥምቀቱን በውኃ ያደረገው ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው

**ትንቢት፡-** "ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ...."/ሕዝ. ፴፯፥፩-፪/

**ምሳሌ፡-**በዕለተ ሐሙስ ባሕር ሕያው ነፍስ ያላቸውን እንስሳት ታስገኝ ባለ ጊዜ ከአንድ ባሕር ተፈጥረው እኩሌቶቹ ዕለቱን በረው ሄደዋል፣ እኩሌቶቹ ከዚያው ቀርተዋል /ዘፍ. ፩፥፳/፡፡ ይህም ምሳሌ ነው፤ ባሕር የጥምቀት፣ በረው የሄዱት የባህታውያን፣ እዚያው የቀሩት የቀና ሃይማኖት ተምረው በጎ ምግባር ሰረተው ሥጋውን ደሙን በንጽሕና ተቀብለው የሚኖሩ የሰብአ ዓለም ምሳሌ ነው

፪ኛ. ውኃ ለሁሉ ይገኛል፣ ጥምቀትም መሠራቱ ለሁሉ ነውና

፫ኛ. ውኃን ከአትክልት ቢያፈሱት ያለመልማል ጥምቀትም ልምላሜ ሥጋ ልምላሜ ነፍስን ያስገኛል፡፡

፬ኛ. ውኃ ከእድፍ ያነጻል፣ ጥምቀትም ከርስሐተ ሥጋ ከርስሐተ ነፍስ ያነጻልና/ያድናልና

፭ኛ. ውኃ መልክአ ገጽ /የፊት መልክ/ ያሳያል፣ በማየ ገቦ /ከክርስቶስ ጎን በፈሰሰው ውኃ/ የተጠመቀም መልክአ ሥላሴን ያያልና

፮ኛ. ውኃ እሳትን ያጠፋዋል፣ ጥምቀትም ከገሃነመ እሳት ያድናልና በእነዚህ እና በሌሎች ምክንያቶች ጥምቀቱን በውኃ አድርጎታል፡፡

**ጌታችን ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በረግብ አምሳል መውረዱስ ለምንድር ነው?**

፩ኛ. በኖኅ ጊዜ ርግብ “ሐፀ ማየ አይኅ፣ ነትገ ማየ አይኅ - የጥፋት ውኃ ጎደለ” እያለች በአፏ ቆጽለ ዕፀ ዘይት ይዛ መጥታለች፤ መንፈስ ቅዱስም ሐፀ ማየ ኃጢአት፣ ነትገ ማየ ኃጢአት - የኃጢአት ውኃ ፈጽሞ ጎደለ፣ ምልአተ ኃጢአት ተሻረ ሲል በአምሳለ ርግብ ወርዷል፡፡

፪ኛ. ርግብ ቢመቷት ቢያባርራት ዕንቁላሏን ቢሠብሩባት ቤቷን ካላፈረሱባት አትርቅም፡፡ መንፈስ ቅዱስም ምንም ኃጢአት ቢሰሩ ጨርሰው ካልካዱት በቀር ከፍጥረቱ አይለይምና፡፡

፫ኛ. ርግብ የዋህ ቂም በቀል የማትይዝ ነች - መንፈስ ቅዱስም ኅዳጌ በቀል ነውና በርግብ አምሳል ወርዷል፡፡

## ፬-፯-፩ የክርስቲያኖች ጥምቀት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወንድ ልጅ በአርባ ቀን ሴት ልጅ በሰማንያ ቀን ጌታችን በወንጌል እንደ አዘዘ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃል፡፡ /ማቴ. ፳፰፥፲፱/፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ሕጻናትን ማጥመቋ መሠረቱ ጌታችን ኢየሱስ ክረስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፱ ከቁጥር ፲፫ ጀምሮ «ሕጻናትን ተዋቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው መንግስተ ሰማያት እንደዚህ ላሉት ናትና» ብሎ ያስተማረው ትምህርት ነው፡፡ መንግስተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና የሚለው የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነት መስጠት ያለበት ከሕፃንነት ጀምሮ መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግስተ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ካልተወለዱ በቀር አይወረስምና ነው፡፡ /ዮሐ. ፫፥፭/

**ጥምቀት በ፵ና በ፹ እንዲሆን የተወሰነው፡-**

፩ኛ. የአዳምና የሔዋንን የጸጋ ልደት ምሳሌ በማድረግ ነው፡፡ አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ የተፈጥሮ የባሕርይ ንጽሕናው ሳያድፍበት በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተወልዶ ገነት ገብቷል፡፡ ሕፃናትም ወንዶች በ፵ ሴቶች በ፹ ቀን የባሕርይ ንጽሕናቸው ሳያድፍባቸው ተጠምቀው አዳምና ሔዋን ያገኙትን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ /ልጅነትን/ ያገኛሉ፡፡

፪ኛ. በሕገ ኦሪት መሠረት እስራኤላውያን ወንዶች ልጆቻቸውን በ፵ ሴቶች ልጆቻቸው ደግሞ በ፹ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው መስዋዕት ይሰውላቸው ነበር፤ ለእግዚአብሔርም ያሰግዷቸው ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ ሕፃናቱ ጸጋ እግዚአብሔርን ተቀብለው ሕዝበ እስራኤል ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ /ዘሌ. ፲፪-፩-፰/፡፡ በዚህም መሠረት ቤተ-ክርስቲያናችን ሕጻናትን በ፵ና በ፹ ቀን በማጥመቅ ውሉደ እግዚአብሔር ሕዝበ ክርስቲያን ታሰኛቸዋለች፡፡

ከዚህ በተረፈ ከአረማዊነት፣ ከክህደት የሚመለሱ ሰዎች ካሉ በልጅነታቸው ከመጡ ከላይ ባየነው በሕጻናት የጥምቀት ሥርዓት ይጠመቃሉ፡፡ አዋቂዎች ከሆኑ ግን ከጥምቀት በፊት እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ሃይማኖትን እየተማሩ ይቆያሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ይጠመቃሉ፡፡

# ፬-፰ ምሥጢረ ቁርባን

## ፬-፰-፩ የቁርባን ትርጉም

> ቁርባን ቃሉ የሱርስት ሲሆን ትርጉሙም “ስጦታ” ማለት ነው፡፡ በኦሪቱ ሰው ለእግዚአብሔር ያቀርብ ነበረውን ብቻ በሚመለከት ነበረ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን ለሰዎች ደኅነት ለዓለሙ ሁሉ የሰጠውን በሥጋና በደም የመጣውን የልጁን ሥጦታ ያስገነዝባል፡፡

ስለዚህ በጸሎተ ቅዳሴ የጌታ ሥጋና ደም ሆኖ የሚቀርበው ቅዱስ ቁርባን ይባላል፡፡ ምሥጢረ ቁርባን ማለትም ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደበት፣ የዘለዓለም ሕይወትን ያስገኘበት፣ የመዳናችን መሠረት የጸጋችን ሁሉ ምንጭ የሆነውን የቅዱስ ሥጋውንና የከቡር ደሙን የማዳን ጸጋ የሚያመለክት ማለት ነው፡፡

## ፬-፰-፪ የምሥጢረ ቁርባን አመሠራረት

ምሥጢረ ቁርባንን ጌታችን ከሕማሙና ከሞቱ በፊት በዋዜማው ሐሙስ ማታ መሥርቶታል፡፡ ጊዜውም የኦሪት የፋሲካ በግ የሚሠዋበት በመሆኑ ጌታችን መሥዋዕተ ወንጌልን መሥርቷል፡፡

«ደቀ መዛሙርቱም ጌታችን ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፣ ፋሲካንም አዘጋጁ፡፡.... ሲበሉም ጌታችን ኢየሱስ ኅብስቱን አንስቶ ባረከ ቆረሰ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ይህ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሎ ሰጠ፡፡ ጽዋውንም አንስቶ አመሰገኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፡- ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡» /ማቴ. ፳፮፥፲፱ እና ፳፮-፳፲/

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከቤተ እስራኤል ጋር ቃል ኪዳን የገባው በእንስሳት ደም ነበረ፡፡ /ዘፀ. ፳፬፥፮-፲፮/፡፡ ቤተ እስራኤል ሕገ ኦሪትን ሲፈጽሙ፣ ዐሥርቱ ትእዛዛትን ሊጠብቁ፤ እግዚአብሔር ደግሞ አምላካቸውና ጠባቂያቸው ሊሆን፣ ምድረ ርስትንም ሊያወርሳቸው ቃል ተጋብተዋል፡፡ በወንጌል ግን እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባው በልጁ ደም ነው፡፡

ቅዱስ ቁርባን መታሰቢያ ወይም ምሳሌ ሳይሆን እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም ነው፡፡ በሉቃስ ወንጌል ፳፪፥፲፱ ላይ « ስለእናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት፡፡» ባለው ላይ መታሰቢያዬ ያለው ስለሕማምና ሞቱ ነው፡፡ የሞቱን ዜና የመስቀሉን ነገር ጌታ እስኪመጣ ድረስ በምሥጢረ ቁርባን እንደሚነገር ሲያሳይ ነው፡፡

«ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን እራሱን በያዙበት በዚያች ሌሊት ኅብስቱን አነሣ፡፡ አመሰገነ፣ ባረከ፣ ፈተተ፤ እንዲህም አላቸው እንኩ ብሉ ስለእናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ መታሰቢያዬንም እንዲሁ አድርጉ፡፡ እንዲሁም ኅብስቱን ከተቀበሉ በኋላ ጽዋውን አንስቶ ሐዲስ

ሥርዓት የሚጸናበት ይህ ጽዋ ደሜ ነው፡፡ እንዲህ አድርጉ በምትጠጡበትም ጊዜ አስቡኝ አላቸው፡፡ ይህን ኅብስት በምትበሉበት ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታችን እስከሚመጣበት ቀን ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ፡፡» እንዲል፡፡ /፩ቆሮ. ፲፩፥፳፫-፳፮/

በቅዳሴአችንም «ንዜኑ ሞተከ እግዚአ ወትንሣኤከ ቅድስተ - አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን» የምንለውም ይህንን መሠረት አድርገን ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን ግን አማናዊ እንጂ መታሰቢያ እንዳልሆነ ጌታችን አረጋግጦ ተናግሯል፡፡

«እውነት እውት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፡፡ እኔም በኋለኛይቱ ቀን አነሣዋለሁ፡፡ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነውና ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡» /ዮሐ. ፮፥፶፫/

«....ይህ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሉ ብሎ ሰጠ፡፡ ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፡- ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡» /ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፱/

በዚህ ቃል ጌታ እንካችሁ ሥጋዬ ደሜ አለ እንጂ የሥጋዬ የደሜ መታሰቢያ እንዳላለ ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ አማናዊ ሥጋውና ደሙን መታሰቢያ ነው ማለት ግን "ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይቻለዋል" /ዮሐ. ፮፥፶፪/ ብለው እንደ ተጠራጠሩት እንደ አይሁድ መሆን ነው፡፡ "...እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው፡፡" ብሏልና ይህን አምኖ መቀበል ይገባናል፡፡ /ዮሐ. ፮፥፶፪/

***ውድ ተማሪች በምሥጢረ ቁርባ የሚገኝ ጥቅም ምንድር ነው?***

## ፬-፫-፫ የቁርባን ጥቅም

የሚታየው የህብስትና ወይን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በክርስቶስ ቃል፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ በካህኑ ጸሎት ወደ ጌታ ሥጋና ደም መለወጡን በሙሉ ልብ አምነው በንስሐ ተዘጋጅተው ለሚቀበሉ አማኖች የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛሉ፡፡

**፩. የሕይወት ምግብ**

በሥጋዊ ልደት ከእናት ከአባታችን ከተወለድን በኋላ በሕይወተ ሥጋ ለመኖር ምግበ ሥጋ እንደሚያስፈልግ ሁሉ በጥምቀትም ከሥላሴ ልጅነትን ካገኘን በኋላ በመንፈሳዊ ዕውቀት እያደጉ፣ በጸጋው እየበለጸጉ ለመኖር የሕይወት ምግብ ያስፈልገናል፡፡ ይህም የሕይወት ምግብ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡

«የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፡፡ በእኔ የሚያምን ለዘለዓለም አይጠማም...ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡» እንዲል፡፡ /ዮሐ. ፮፥፴፫ ና ፶፫/

**፪. ሥርየተ ኃጢአትን**

«ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው»/ማቴ. ፳፮፥፳፯/

የኃጢአት ሥርየት ከተገኘ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅና ሰላም ይወርዳል፡፡ እርቅ ከተገኘ ደግሞ ሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ይጨመራሉ፡፡ ለዚህ ነው፡፡

«መተላለፉ የቀረችለት፣ ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው፡፡» የተባለው፡፡ /መዝ. ፴፩፥፮/

**፫ኛ. ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆኖ በኅብረት መኖርን**

«ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡» /ዮሐ. ፮-፶፯/

ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆኖ መኖር ሕይወትን ያስገኛል፤ ከእርሱ ጋር ካልሆንን ግን በራሳችን ሕይወት አይኖረንም፡፡

«እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላችሁም፡፡» /ዮሐ. ፮፥፶፫/

**፬ኛ. ለፍሬ ክብር የሚያደርስ መንፈሳዊ ኃይልን**

ሥጋውና ደሙ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆንን እንደሚያስችል ከላይ ተመልክተናል፡፡ ይህ ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረት ደግሞ ከክብር የሚያበቃ ሥራ የምንሰራበት ኃይል መንፈሳዊን ያስጠናል፡፡

«ቅርንጫፍ በወይን ግንድ ካልኖረ ብቻውን ሊያፈራ እንደማይችል እናንተም እንዲሁ በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ማፍራት አትችሉም፡፡»እንዲል፡፡ /ዮሐ. ፲፭-፬/

**፭ኛ. የዘለዓለም ሕይወትን**

ሥጋው መብላት ደሙን መጠጣት ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘት አማራጭ የሌለው መንገድ ነው፡፡

«ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፡፡ እኔም በኋለኛይቱ ቀን አነሣዋለሁ፡፡»/ዮሐ. ፮፥፶፬/

**፮ኛ. እርስ በእርስ በፍቅር መተሣሠርን**

« ይህ የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር አንድ አይደለምን? የምንፈትተው ይህስ ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር አንድ አይደለምን? ኅብስቱ አንድ እንደሆነ እንዲሁ እኛም ብዙዎች ስንሆን አንድ አካል ነን፣ ሁላችንም ከአንድ ኅብስት እንቀበላለንና፡፡ » /፩ ቆሮ. ፲፥፲፮-፲፯/

## ፬-፳-፬ የቁርባን ምሳሌዎች

*ውድ ተማሪዎች እግዚአብሔር በሐዲስ ኪዳን ለመጣ ያለው ምስጢረ በብሉይ ኪዳን በብዙ ኀብረ አምሳል እና ኅብረ ትንቢት ቀድሞ ለፍጥረቱ ይገልጣል፡፡ ስለ ምሥጢረ ቁርባን በብሉይ ኪዳን የተመሰሉ ምሳሌዎች የተነገሩ ትንቢቶች አሉ፡፡ ስለሥጋውና ደሙ የተመሰሉ ምሳሌዎች፡-*

**፩ኛ. የመልከጼዴቅ መሥዋዕት - /ዘፍ. ፲፬፥፲፰-፳፤ ዕብ. ፭፥፮-፲/**

አብርሃም ኮሎዶጎሞርንና ከእርሱ ጋር የነበሩት ነገስታት ድል ነስቶ ሲመለስ የሳሌም ንጉሥ መልከጼዴቅ ኅብስት ወይን ይዞ ተቀብሎታል፡፡ ይህም ምሳሌ ነው፡፡ የመልከ ጸዴቅ ኅብስተ አኮቴት፣ ጽዋዐ በረከት የሥጋ ወደሙ፣ መልከጼዴቅ የጌታ፣ አብርሃም የምዕመናን ምሳሌ ነው፡፡

**፪ኛ. የፋሲካው በግ - /ዘፀ. ፲፪፥፮-፳፩፤ ፩ቆሮ.፭፥፯/**

- እስራኤል ከሞተ በኩር የዳኑበት ተባት በግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡
- ነውር የሌለበትን በግ የሚያዝያ ወር በገባ ከአሥረኛው ቀን እስከ አሥራ አራተኛው ቀን አስረው በአሥራ አራተኛው ቀን ይሠውታል፡፡ ይህም ንጹሐ ባሕርይ ጌታ በቅንዓተ አይሁድ ታሥሮ በመስቀል ለመስዋዕቱ ምሳሌ ነው፡፡
- የበጉን ደም የቤታቸውን መቃንና ጎበኑን እንዲቀቡ መደረጉ ለጊዜው ለቀሳፊው መልአክ ምልክት ሆኖት ያን ቤት አልፎ እንዲሄድ ሲሆን ለፍጻሜው ግን "ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው" እንዳለ ጌታ በሥጋ ወደሙ የታተሙት ሞተ ነፍስ እንደማያገኛቸው ይጠይቃል፡፡
- የበጉን ሥጋ ጥሬውን ወይም ቅቅሉን ሳይሆን ጥብሱን እንዲበሉ መታዘዛቸው
  - 'ጥሬውን አትብሉ' ማለት ነፍስ ያልተለየው፣ መለኮት ያልተወሐደው እያላችሁ አትብሉ ሲል ነው
  - 'ቅቅሉን አትብሉ' ማለት ሥጋው በመቀበር ፈርሶ በስብሶ ቀረ አትብሉ ሲል ነው
  - 'ጥብሱን ብሉ' ማለት መለኮት የተዋሐደውን ነፍስ የተለየውን እንድትቀበሉ እወቁ፣ እመኑ ሲል ነው
- ከመራራ ቅጠል ጋር እንዲበሉ መታዘዛቸው ሥጋ ወደሙን ጸመን ለአፋችን ምሬት ሲሰማን እንድንቀበል ነው፡፡

**፫ኛ. ከሰማይ የወረደው መና /ዘፀ. ፲፮፥፲፮-፳፫፤ ዮሐ. ፵፱፥፶፮/**

ሕዝበ እስራኤል በምድረ በዳ ከሰማይ መና ወርዶላቸው ተመግበዋል፡፡ ይህም ምሳሌ ነው፡፡ መና የጌታ ሥጋና ደም፣ መናው የተገኘበት ደመና ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው የሆነባት የእመቤታችን ምሳሌ ነው፡፡

**፬ኛ. ጥበብ ያዘጋጀችው ማዕድ /ምሳ. ፱፥፩/**

ጥበብ የክርስቶስ፣ ማዕድ የሥጋ ወደሙ፣ አገልጋዮች የካህናት፣ ተጋባዦች የምዕመናን ምሳሌ ናቸው፡፡

***ስለ ሥጋውና ደሙ የተነገሩ ትንቢቶች፡-***

"ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ይከብራልና፣ በየሥፍራውም በስሜ ዕጣን ያጥናሉ፣ ንጹሕንም ቁርባን ያቀርባሉ፡፡" /ሚል. ፩፥፲፩/

ይህ የትንቢት ቃል የተነገረው በብሉይ ኪዳን ይቀረብ ስለነበረው ቁርባን አለመሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን አምልኮተ እግዚአብሐርን ይፈጽሙ መስዋዕት ይሰው የነበሩ ሕዝበ እስራኤል እንጂ ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ያሉ አሕዛብ አልነበሩም፡፡ የዕጣኑም መስዋዕት ቁርባኑም የሚቀርቡት በምድረ ፍልስጥኤም እንጂ በዓለም ሁሉ አልነበረም፡፡ ይህ የትንቢት ቃል ግን በሐዲስ ኪዳን የክርሰቶስ ስም በዓለም ሁሉ እንደሚሰበክ የሐዲስ ኪዳኑ የክርስቶስ ስም በዓለም ሁሉ እንደሚሰበክ የሐዲስ ኪደኑ መስዋዕት ሥጋውና ደሙ /ቅዱስ ቁርባን/ በየሥፍራው ምዕመናን ባሉበት ሁሉ እንደሚቀርብ ያሳያል፡፡

« እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ሂዱ፣ ገንዘብም የሌላችሁ ሂዱና ግዙ ብሉ፣ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ጠጡ...በረከትንም ብሉ...» /ኢሳ. ፶፭፥፩-፪/

ይህ የነብዩ የኢሳይያስ የትንቢት ቃል በመብልና በመጠጥ ስለሚመጣው ስለምሥጢረ ቁርባን የተነገረ ነው፡፡

## ፬-፱ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

### ፬-፱-፩ ትንሣኤ ሙታን ምን ማለት ነው?

*ውድ ተማሪዎች ይህ ምሥጢረ ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት በአምስተኛ(በስተመጨረሻ )የሚገኝ ምሥጢር ነው፡፡ ተስፋ መንግስተ ሰማያት የሚውጅ ምሥጢረ ነው፡፡*

ትንሣኤ ሙታን ማለት ተለያይተው በተለያየ ሥፍራ ይኖሩ የነበሩት ነፍስና ሥጋ እንደገና ተዋሕደው መነሣትና ከሞት በኋላ በነፍስና በሥጋ ሕይወት ማግኘት ማለት ነው፡፡

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ስንልም ሙታን በዓለም መጨረሻ የፈጣሪያቸውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው ነፍስና ሥጋቸው ተዋሕደው ከመቃብር የሚነሱና የዘለዓለም ሕይወትን የሚያገኙ መሆናቸውን ምንማርበት፣ የምናምንበት የሃይማኖት ምሥጢር ነው፡፡

### ፬-፱-፪ የትንሣኤ ሙታን አስፈላጊነት

ሰው የተፈጠረው ነፍስና ሥጋው ሳይለያዩ በሕይወት ለመኖር እንጂ ለሞት አልነበረም፡፡ ሰው ግን ኃጢአትን በመሥራቱ በራሱ ላይ ሞትን አመጣ፡፡ /ሮሜ. ፭፥፲፪/

«እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና፤ የሕያዋንም ጥፋት ደስ አያሰኘውምና፡፡ ነዋሪ ይሆን ዘንድ ፍጥረቱን ፈጥሯልና…ለሲኦልም በምድር ላይ ግዛት አልነበረውምና… ክፉዎች ግን በእጃቸውና በቃላቸው ጠሩት ባልንጀራም አሰመሰሉት፡፡» /ጥበብ ፩፥፲፫ እና ፲፫፥፲፯/

እንደ ዲያብሎስ በድሎ ያልቀረው ሰው በንስሐ ቢመለስ ፈጣሪው ሰው ሆኖለት ሞቶ ከፍርድ አዳነው፤ ሞትን አጥፍቶ ሕይወትን መለሰለት፡፡ የተፈጠረበትም በጥንት ሕይወቱ ይኖር ዘንድ ለሰው ትንሣኤ ሆነለት፡፡

### ፬-፱-፫ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና እርገት

የሙታንን ትንሣኤ ማመናችን የክርስቶስ ከሙታን መነሣት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ጌታችን ስለሁላችንም ሞቶ ፫መዓልት ፫ ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ መቃብር ክፈቱልኝ፣ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ከሙታን ተለይቶ ከሙታን ቀድሞ በዘመነ ማርቆስ በመጋቢት ፳፱ ቀን እሁድ በመንፈቀ ሌሊት ተነሥቷል፡፡

***ውድ ተማሪዎች ጌታችን ፫ መዓልት ፫ ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ የሚለው እንዴት እንደሆነ አብራሩ?***

ምላሹ የዕብራውያንን አቆጣጠር መሠረት ያደረገ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን ሥርዓት ወግና መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ የተጻፈ ነው፡፡ በዕብራውያን ልማድ ሌሊት የሚቆጠረው በዋዜማው ካለው አሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ ከ ፲፩ ሰዓት በፊት ያሉት ሰዓቶች ግን አንድ ሰዓትም ቢሆን እንደ አንድ መዓልትና ሌሊት ይቆጠራል፡፡ ጌታ የተቀበረውም ዓርብ ከ፲፩ ሰዓት በፊት ስለሆነ የተቀበረበት ሰዓት የዓርብን መዓልትና ሌሊት ያጠቃልላል፡፡ ቅዳሜ ሙሉውን ይዞ ከቅዳሜ ፲፩ ሰዓት በኋላ ያለው የእሁድን ሰዓቶች ሞልቶ ፫ መዓልት ፫ ሌሊት ይሆናል፡፡

ሐዋርያትም የትንሣኤው ምሥክሮች በመሆን የክርስትና ሃይማኖት አስፋፉ፡፡ /ሐዋ. ፪፥፲፬-፴፮/፡፡ ትንሣኤውም የወንጌል የመጀመሪያው ሰብከት ሆነ፡፡

«የአባቶቻችን አምላክ እናንተ ከዳችሁ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን አስነሳው… እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮቹ ነን፡፡» እንዲል፡፡ /ሐዋ. ፭፥፳፺-፴፪/

እኛም በኲረ ትንሣኤ /የትንሣኤ መጀመሪያ/ የሆነውን ክርስቶስን ተመልክተን ትንሣኤ ሙታን እንዳለ እናምናለን ተስፋም እናደርጋለን፡፡ ጌታችን በቃሉ እንዲህ ብሏልና፡፡

«ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞትም ይነሣል፤ ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም» /ዮሐ. ፲፩፥፳፭ እና ፳፮/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን አብራርቶ አስተምሯል፡፡

«ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶአል ብለን ለሌላው የምናስተምር ከሆነ እንግዲህ ከመካከላችሁ ሙታን አይነሡም የሚሉ እንዴት ይኖራሉ? ሙታን የማይነሱ ከሆነ ክርስቶስም ከሙታን ተለይቶ አልተነሣም፡፡ ክርስቶስም ከሙታን ካልተነሣ እንግዲያስ ትምህርታችን ከንቱ ነው፤ የእናንተም እምነታችሁ ከንቱ ነው፡፡…አሁን ግን ክርስቶስ ከሞቱ ሰዎች ሁሉ አስቀድሞ ተነሥቷል፡፡…ሁሉ በአዳም እንደሚሞት እንዲሁ በክርስቶስ ሁሉ ህያዋን ይሆናሉ፡፡» /፩ቆሮ. ፲፭፥፲፪-፴፪/

**የጌታችን ትንሣኤ በትንቢትና በምሣሌ**

**ትንቢት፡-**

«እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፣ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው፣ ጠላቶቹንም በኋላቸው ገደለ፡፡» /መዝ. ፸፯፥፷፭/

«እግዚአብሔር ይላል፡- አሁን እነሣለሁ መድኃኒትን አደርጋለሁ በእርሱም እገለጣለሁ፡፡» መዝ. ፲፩፥፭/

**ምሳሌ፡-**

«ዮናስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በአሣ አንባሪ ሆድ እንደነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በምድር ልብ ውስጥ ይኖራል» /ማቴ. ፲፪፥፵/

ምሳሌውም ዮናስ የጌታ፣ ከርሠ አንበሪ /የዓሣ አንበሪ ሆድ/ የመቀበር ነው፡፡

**የጌታ ዕርገት**

ስለጌታችን እርገት ልበ አምላክ ዳዊት አስቀድሞ ይህን የትንቢት ቃል ተናግሯል፡፡

« እግዚአብሔር በዕልልታ፣ ጌታንም በመለከት ድምፅ አረገ» /መዝ. ፵፮፥፩-፭/

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ለሐዋርያት መጽሐፈ ኪዳንን አስተምሯል፡፡ /ሉቃ. ፳፬፥፳፯/ በአርባኛው ቀን እስከ ቢታንያ አውጥቶ "እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" ብሏቸዋ፣ እስከ ፓትርያርክነት ያለውን ማዕረግ በአንብርተ ዕድ ሾማቸው ዐርጓል /ሉቃ. ፳፬፥፵፱ ና ፶/

**የጌታችን ዳግም ምጽአት**

ጌታችን ለሁለት የተቀደሱ ዓላማዎች ወደ ዓላማችን ሁለት ምጽአቶችን እንደ አደረገና እንደሚያደርግ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡፡ «አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ይሽራት ዘንድ አንድ ጊዜ ተገለጠ፡፡ …በኋላ ግን ያድናቸው ዘንድ ተስፋ ለሚያደርጉት ያለ ኃጢአት ይገለጥላቸዋል፡፡» /ዕብ. ፱፥፳፮-፳፰/

የመጀመሪያው ምጽአቱ መከራን ተቀብሎ በሞቱ ሞትን ሽሮ የሰውን ልጅ ለማዳን በፍጹም ትህትና ነው፡፡ ሁለተኛ ምጽአቱ ግን በግርማ መለኮት፣ በክበበ ትስብእት በፍጹም ጌትነት የመጀመሪያውን ምጽአቱን ባልተቀበሉት ላይ ሊፈርድ ነው፡፡

«እነሆ በሰማይና ደመና ይመጣል፣ ዐይን ሁላ ታየዋለች፤ እነዚያም የወጉት ይመለከቱታል፡፡» /ራዕ. ፩፥፯/

እርሱ ለፍርድ ሊመጣ አቅራቢያም ብዙ ምልክቶች ይታያሉ፡፡

- በክርስቶስ ስም የሚያስቱ ይነሳሉ /ማቴ. ፳፬፥፬-፭/
- የጦርነት ወሬ ይነግሣል፣ ሕዝብ በሕዝብ መንግሥትም በመንግስት ላይ ያነሳል /ማቴ. ፳፬፥፮-፯/
- ረሀብ ድርቅ ቸነፈር የምድር መናውጥ ይሆናል /ማቴ. ፳፬፥፲/
- ክርስቶስን የሚያምኑ ለመከራ ይሰጣሉ / ማቴ. ፳፬፥፱/
- ሐሳዊ መሲሕ ይነሳል /ማቴ. ፳፬፥፲፫/

ከዚህ በኋላ ጌታ በታላቅ ግርማ በመላእክት ታጅቦ ይገለጣል፡፡ የተወጋ ጐኑን በጠቅላላ ጸዋትወ መከራ የተቀበለባቸው ምልክቶችን ለሁሉ እንዲታዩ አድርጐ ይገለጣል፡፡ ይኸም በዕለተ አርብ መሥዋዕተ መሆኑን አምነው የተቀበሉት አይፈረድባቸውም ማለት ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታቸው ሁሉ አንጽቷቸዋልና፤ ስማቸውም በሕይወት መጽሐፍ ተጽፏልና፡፡ /ዮሐ. ፩፥፳፱፤ ፩ዮሐ. ፩፥፯፤ ራዕ. ፯፥፲፬፤ ፳፩፥፳፯/፡፡ ያላመኑትና ያልተቀበሉት ግን ለኃጢአታቸው ማስወገጃ ሆኖ የተሰጣቸውን የበጉን መስዋዕት ባለመቀበላቸው ኃጢአታቸው ለዘለዓለም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፡፡ የሞትም ፍርድ ይጠብቃቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ጌታችን በግርማ መለከቱ በክበበ ትስብእት በሉዓላዊ ከብሩ በመጣ ዕለት የሚፈጸሙት ሁለት ነገሮች፡-

፩ኛ. ትንሣኤ ሙታን - የሙታን ሁሉ መነሳት ይሆናል

፪ኛ. ይግባኝ የሌለበት የመጨረሻ መለኮታዊ ፍርድ ይሰጣል

## ፬-፱-፬ የትንሣኤ ሙታን አስረጂዎች በመጽሐፍ ቅዱስ

*ውድ ተማሪዎች በሐዲስ ኪዳን ሳለው መገለጥ እና ስለ ዳግም ምጽዓቱ እግዚአብሔር በብዙ ህበረ አምሳልና ትንቢቶች ቀድሞ ተነግሯል፡፡ በለሰው ልጆች ትንሣኤ እንዳላቸው አስቀድሞ በነቢያቱ አናግሯል፡፡*

*« መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም የምድርንም ፊት ታድሳለህ፡፡» /መዝ. ፻፫፥፴/*

*መንፈስ ቅዱስን ታሳድርባቸዋለህ ታድሰው ይነሳሉ፣ ምዕመናንን በትንሣኤ ዘጉባኤ ታድሳታለህ ሲል ነው፡፡*

*«እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ፡፡» እንዲል፡፡/ራዕ. ፳፩፥፭/*

*«ሙታን ይነሣሉ፤ በመቃብር ያሉም ይድናሉ፡፡»/ኢሳ. ፳፮፥፲፱/*

*«በዚያም ዘመን ስለሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፣ ሕዝብም በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፡፡ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጻፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች እኩሌቶቹ ለዘለዓለም ሕይወት፣ እኩሌቶቹም ለዕረፍትና ለዘለዓለም ጉስቁልና ይነሣሉ፡፡ ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል ከጻድቃንም ብዙዎች እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ያበራሉ፡፡»/ዳን. ፲፪፥፩-፫/*

*የሙታ መነሣት ምሥጢርም እንዴት እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ሲናግር*

*«እነሆ አንድ ምሥጢርን እንግራችኋላሁ፤ ሁላችን የምንሞት አይደለም፡፡ ነገር ግን የኋለኛው መለኮት ሲነፋ ሁላችን እንደ ዓይን ጥቀሻ በአንድ ጊዜ እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና፤ ሙታንም የማይፈርሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን፡፡» /፩ቆሮ. ፲፭፥፶፩-፶፪/*

*ሐዋርያው እንደተናገረ በጌታ ትእዛዝ ሙታንን ለማስነሣት ሦስት ጊዜ የአዋጅ መለከት ይነፋል፡፡*

- *በመጀመሪያው የወደቀው የደቀቀው የፈረሰው የበሰበሰው ሁሉ በአንድ ቦታ ይሰበሰባል፡፡*
- *በሁለተኛው አጥንተና ሥጋ አንድ ይሆናሉ፣ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናሉ*

✝ በሦስተኛው ደጉም ደግነቱን፣ ክፉም ክፉቱን ይዞ እንደ እጀት ተፈልፍሎ እንደ ዘንግ ተመልምሎ ይነሣል፡፡ /ያዕቆብ ዘሥሩግ ቅዳሴ/

መለከትም ሲባል የእግዚአብሔ አዋጅ፣ የመለኮት ትእዛዝ ማለት ነው፡፡

«ጌታችን ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስም የሞቱ ሙታን አስቀድመው ይነሣሉ» /ዮሐ. ፩፥፳፱/

ከላይ እንዳየነው ሙታንን የሚያስነሳ ጌታ ሲሆን በጌታ ትእዛዝ የሞቱት እንዲነሱ የሚያውጀው ደግሞ ቅዱስ ሚካኤል ነው፡፡ /ዳን. ፲፪፥፩-፪ ተመልከት/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ነገር በዘር መስሎ አስተምሯል፡፡ /፩ቆሮ. ፲፭፥፴፭-፵፯ ተመልከት/

## ፬-፱-፭ የዓለም ፍጻሜና የፍርድ ቀን /ትንሣኤ ዘጉባዔ/

*ሙታን ሁሉ ከተነሱ በኋላ የመጨረሻው የፍርድ ሰዓት ይመጣል፡፡ ጻድቃን ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጎናጽፈው ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው ፍጹም የጌታቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው ይነሣሉ፡፡ «ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ» እንደተባለ፡፡ ኃጥአን ደግሞ ጨለማ ለብሰው ጨለማ ተጎናጸፈው አረው ከስለው ከቁራ ሰባት እጅ ጠቁረው ፍጹም አለቃቸው ዲያብሎስን መስለው ይነሣሉ፡፡*

ጻድቃን ትንሣኤ ዘለክበር /የክብር ትንሣኤን/ ኃጥአን ትንሣኤ ዘለኃሣርን /የጥፋት ትንሣኤን/ ይነሣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ጌታ ከመላእክቱ ጋር ወደ ምሥራቅ ይመጣል፡፡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ አንድ ጊዜ ይታያል፡፡ /ማቴ. ፳፬፥፳፯ ና ፳፲/

« የሰው ልጅ በጌትነቱ ቅዱሳን መላእክትን አስከትሎ በሚመጣበት ጊዜ፤ ያን ጊዜ በጌትነቱ ዙፋን ይቀመጣል፡፡ አሕዛብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ እየራሳቸው ይለያቸዋል፡፡ በጎችን በቀኙ ፍየሎቹንም በግራው ያቆማቸዋል፡፡» /ማቴ. ፳፭፥፴፩-፵፮/

*ጻድቃንን በበግ ኃጥአንን በፍየል መስሎ ተናግሯል፡፡*

- በግ ኃፍረቷን በላት ትሠውራለች - ጻድቃንም የራሳቸው ኃጢአት በንሰሐ የወንድማቸውን ኃጢአት በትዕግስት ይሠውራሉና፡፡
- በግ ከዋለበት አይታወቅም - ጻድቃንም ከዋሉበት አይታወቁምና
- ከበግ አውሬ አንዱን የነጠቀው እንደሆነ ይሸሻል ከሸሸም በኋላ አይመለስም “በግ ከበረረ የሰው ልጅ ከተመረረ” እንዲሉ - ጻድቃንም ከባልንጀራቸው አንዱ የሞተ እንደሆነ ይመንናሉ፣ ከመነኑም አይመለሱም
- በግ ኑሮው በደጋ ነው - ጻድቃንም ኑሮአቸው በጸጋ መንግስተ ሰማያት ነው
- ፍየል ትዕቢተኛ ናት ሽቅብ ሽቅብ ትመለከታለች - ኃጥአንም ትዕቢተኞች ናቸውና
- ፍየል ኃፍረቷን በላቷ አትሸፍንም - ኃጥአንም የወንድማቸውን ኃጢአት በትዕግሥት የራሳቸው በንሰሐ አይሰውሩትምና
- ፍየል ከዋለበት ሁሉ ከእህል ከተክል እየገባ ሰውን ሲያሳዝን ይውላል - ኃጥአንም ሰውን ሲያሳዝኑ ይኖራሉና
- ፍየል አንዱን አውሬ የነጠቀው እንደሆነ ለጊዜው ያሸሻል ኋላ ግን ይመለሳል፣ እየነጠቀ ይፈጀዋል - ኃጥአንም ከወገናቸው አንድ የሞተ እንደሆነ መነንን ይላሉ፣ ተመልሰው በርስቱ በጉልበቱ በቤቱ በንብረቱ ሲጣሉ ይገኛሉና፡፡
- ፍየል ኑሮው ቆላ ነው - ኃጥአንም ኑሮአቸው ቆላ ገሃነም ነውና፡፡

ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን ደግሞ በግራው ያቆማል፡፡ ይህም ጻድቃንን በክብር፣ ኃጥአንን በኃሣር ያስነሳቸዋል ሲል ነው፡፡ በሌላም መልኩ፡-

- *ቀኝ ኃያል ነው - ጻድቃንም ለበጎ ሥራ ኃያላን ናቸውና፡፡*
- *ቀኝ ፈጣን ነው - ጻድቃንም ለበጎ ሥራ ፈጣኖች ናቸውና፡፡*
- *ቀኝ ቅን ነው - ጻድቃንም ቅኖች ናቸውና፡፡*
- *ግራ ደካማ ነው - ኃጥአንም በጎ ሥራ ለመሥራት ደካሞች ናቸውና*
- *ግራ ዳተኛ ነው - ኃጢአንም ዳተኞች ናቸውና*
- *ግራ ጠማማ ነው - ኃጢአንም ጠማሞች ናቸውና*

በቀኙ ያሉትን “እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፡፡ ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና፡፡” ይላቸዋል፡፡

በግራው ያሉትንም “እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመልክተኞቹ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ፡፡” ብሎ ከላይ የተዘረዘሩትን በጎ ሥራዎች ስላልፈጸሙ የተፈረደባቸው መሆኑን ይገልጻላቸዋል፡፡

የሚፈረድባቸው የሚያምኑ ብቻ ሳይሆኑ እምነት ኖራቸው በጎ ሥራ ጭምር የሌላቸውም ነው፡፡ በሥራ መካድ አለና፡፡ «እግዚአብሔርን እንደሚያውቁት በግልጥ ይናገራሉ፤ በሥራቸው ግን ይክዱታል»/ቲቶ. ፩፥፲፯/

በሥራ የማይገለጽ እምነት ደግሞ የሞተ ነውና አያድንም፡፡ /ያዕ. ፪፥፲፬-፳፯/

## ፬-፱-፮ ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት

*ውድ የርቀት ትምህርት ተከታታዮች ሶስት መቶ አስራ ስምንቱ ሊቃነ ጳጳሳት በኒቂያ ጉባኤ ድንጋጌ ላይ «የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን፡፡» በማለት ጥቀሰዋል፡፡/ጸሎተ ሃይማኖት/*

በክርስቶስ ላሉ ሁሉ የሚሰጣቸው የዘለዓለም ሕይወት ገነት መንግስተ ሰማያት ነው፡፡ ይህም የዘለዓለም ሕይወት የተገኘው በክርስቶስ መስዋዕትነት ነው፡፡ «ሕይወታችሁ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ያን ጊዜ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ፡፡»/ቆላ. ፫፥፬/

የሕይወት ተስፋችንን ከክርስቶስ ለይተን መመልከት አንችልም፡፡ ትንሣኤ እና ሕይወት እርሱ ነውና፡፡ /ዮሐ. ፲፩፥፳፭/፡፡ በክርስቶስ ያለው ተስፋችን «ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀው መንግስተ ሰማያት» እንደሆነ ነግሮናልና፡፡ /ማቴ. ፳፭፥፴፬/

«አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር አልፈዋልና ቅድስቲቱም ከተማ አዲስቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፤ ለባልዋ እንደ አጌጠች ሙሽራም ተዘጋጅታ ነበር፡፡»/ራዕ. ፳፩፥፩-፪/

ስለዚህች ስለተስፋይቱ ሀገር ውበትና ታሪክና ምሳሌን አስማምቶ ይገልጻል /ራዕ. ፳፩፥፱-፳፩/፡፡ ይህም ሰው በሚገባው ቋንቋና ምሳሌ እንጂ እውነተኛ ገጽታዋና ሁኔታዋ በቃላት ከመገለጥ በላይ ነው፡፡

«ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማው በሰውም ልብና ያልታሰበ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው»/፩ቆሮ. ፪፥፱/

ወደ ቅድስቲቷ ከተማ የሚገቡት በክርስቶስ አምነው፣ በምግባር ጸንተው፣ የዓለምን መከራና ፈተና ድል የነሱ፣ ልብሳቸውን በበጉ ደም ያነጹ ሰውነታቸውን ከኃጢአት የለዩ ናቸው፡፡ /ራዕ. ፳፩፥፯-፯፤ ፩ዮሐ. ፭፥፬-፭፤ ራዕ. ፳፪፥፲፬/

ከቅድስቲቱ ከተማ ውጭ የሚቀሩት ልብሳቸውን ያላጠቡ፣ ማለትም በበጉ ደም ያለነጹ በኃን ሥራ ትተው ክፉውን የሚሠሩ ናቸው፡፡

«በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርሷ ከቶ አይገባም» እንደተባለ፡፡ /ራዕ. ፳፩፥፳፯፤ ራዕ. ፳፪፥፲፫/

የሚገቡበትም፡-

«የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኛዎችም ጣኦትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ውስጥ ነው፣ ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው፡፡»/ራዕ. ፳፩፥፰/

«ሁለተኛ ሞት» የተባለውም ገሃነመ እሳት ነው፡፡ የማይጠፋ እሳት ያለበት የዘለዓለም የሥቃይ ቦታ ነው፡፡ በዚያ ስላሉት፡-

"ለዘለዓለምም እስከ ዘለዓለም በመዓልትና በሌሊት ይሠቃያሉ፡፡" ተብሏል፡፡ /ራዕ. ፳፥፲/

## ፬-፲ የምዕራፉ ማጠቃለያ

*ውድ ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቤተ ክርስቲያን የምስጢረ ምሰሶዎች ስለሚባሉት ስለ አምስቱ አዕማደ ምስጢራት በስፋት ተመልክተናል፡፡ አምስቱ አዕማደ ምስጢር የሚባሉት፡- ምስጢረ ሥላሴ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ቁርባን እና ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን አፈታት ምሥጢር ማለት በምርምር ጥልቀት፣ በእውቀት ብዛት ሊደረስበት የማይችል፣ በሥጋ አእምሮ ሳይሆን በመንፈስ አእምሮ የሚረዱት ረቂቅና ጥልቅ ኀቡዕ /የተሰወረ/ ነገር ማለት ነው፡፡ እነዚህም ምስጢር መባላቸው ከመምህራን ተምረው በልቦና መርምረው የሚያምኗቸው በዓይን የማይታዩ፣ በእጅ የማይጨበጡ ነገሮች የሚነገሩባቸው በመሆናቸው ነው፡፡*

*አዕማድ ማለት ደግሞ ምሰሶዎች ማለት ነው፡፡ እነዚህም ምስጢራት ምሰሶዎች መባላቸው ምሰሶ ቤትን ደግፎ እንደሚያጸና እንዝህም በቤት የተመሰለ ልቡናን ከኑፋቄ /በክህደት ከመውደቅ/ የሚየጸኑ ስለሆነ ነው፡፡*

**ምስጢረ ሥላሴ፡-**

- የሥላሴ አንድነት ሦስትነት የሚነገርበት ምሥጢር ነው፡፡
- ሥላሴ አንድም ሦስት ናቸው፡፡
- አንድነታቸው በህልውና፣ እግዚአብሔር በመባል፣ በመለኮት፣ በአምላክነት፣ በአገዛዝ፣ በሥልጣን፣ በባሕርይ፣ በልብ፣ በቃል፣ በእስትንፋስ እና እነዚህንም በመሳሰሉት ነው፡፡
- ሦስትነታቸው ደግሞ በስም፣በአካል፣ በአካላዊ ግብር፣ በኩነት ነው፡፡
- የስም ሦስትነታቸው አብ፣ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡
- የአካል ሦስትነታቸው፡- ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው፤ ለወልድም ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው፤ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው ማለት ነው፡፡
- የግብር ሦስትነታቸው፡- የአብ ግብሩ ወልድን መውለድ መንፈስ ቅዱስን ማስረጽ ነው፤ የወልድ ገብሩ ከአብ መወለድ ነው፤ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ከአብ መስረጽ ነው፡፡

**ምስጢረ ሥጋዌ፡-**

- ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል፣ በከዊን ስሙ ቃል የሚባለው ወለድ በተለየ አካሉ ሥጋ የመልበሱ ነገር የሚነገርበት ምሥጢር ነው፡፡
- አዳም በምክረ ከይሲ ተታሎ የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሱ ጸጋው ተገፈፈ፤ ባሕርይው ጎሰቆለ፡፡ በዚህም ምክንያት እርሱንና ዘሩን ሁሉ ሞት ገዛቸው፡፡ ከዚህም የሞት ፍርድ ከአምላክ በቀር ሊያድነው የሚችል አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት አምላክ ሰው ሆነ፡፡
- አምላክ ሰው የሆነው በተዋሕዶ ነው፡፡ ይህም ማለት መለኮታዊ አካልና ሥጋዊ አካል፣ መለኮታዊ ባሕርይና ሥጋዊ ባሕርይ በተዐቅቦ /በመጠባበቅ/ አንድ ሆኑ፣ ተዋሕድ፡፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው፡፡

**ምስጢረ ጥምቀት፡-**

- የሥላሴ ልጅነት የሚሰጥበትና የኃጢአት ሥርየት የሚገኝበት ምስጢር ነው፡፡
- ጥምቀት ድኅነትን ያስገኛል፣ የሥላሴ ልጅነትን ያሰጣል፣ ከጌታ ሞትና ትንሣኤ ጋር ያስተባብራል፣ የቤተ ክርስቲያን አባል ያደርጋል፡፡

**ምስጢረ ቁርባን፡-**

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወትን ያደለበት የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ የማዳን ጸጋ የማነገርበት ምስጢር ነው፡፡
- ቅዱስ ቁርባን የሕይወት ምግብ ነው፤ መንፈሳዊ ኃይልን ያድላል፡፡ ሥርየተ ኃጢአትን አሰጥቶ የዘለዓለም ሕይወትንም ያስገኛል፡፡
- ጌታችን በዕለተ አርብ በመስቀል ላይ ለአንዴና ለዘለዓለም ያቀረበውን መስዋዕት ሁልጊዜ ለማግኘት እንድንችል በጸሎተ ሐሙስ ማታ ምሥጢረ ቁርባን መሥርቷል፡፡ /ዕብ. ፱፥፲፩-፲፴/፡፡ ስለዚህ በየጊዜው ስለምንፈጽመው በደል የኃጢአት ሥርየት እንድናገኝ በንስሐ ተዘጋጅተን በየጊዜው የሚቀርበው የቅዱስ ቁርባን መስዋዕት መቀበል ይኖርብናል፡፡

**ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን፡-**

- ሙታን በዓለም መጨረሻ በእግዚአብሔር ሥልጣን ነፍስና ሥጋቸው ተዋሕዶ ጽድቅን የሠሩ ለክብር፣ ኃጢአትን ያደረጉ ለዘለዓለም ቅጣት የሚነሱ መሆናቸው የሚነገርበት ነው፡፡